አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3543 | ቅዳሜ ጥቅምት 8 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# የከተማዋ የዕድገት መሰላል

"የሁለንተናዊ ብልፅግና ተምሳሌት የሆነች ከተማን እየገነባን ነው"

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ

- የመዲናዋ ገቢ በ2010 በጀት ዓመት ከነበረበት 33 ቢሊዮን ብር በ2017 በጀት ዓመት ወደ 233 ቢሊዮን ብር ከፍ ማለቱ ተጠቁሟል
- ግብርን ሳይሸሽጉ መክፈል ጥቅሙ ለራስ መሆኑን ምስጉን ግብር ከፋዮች ተናግረዋል



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ለግብር ከፋዮች የእውቅና ሽልማት በሰጡበት ወቅት

**በመለሰ ተሰጋ**

ግብር የዘመናዊ ከተሞች የደም ሥር ነው፤ ለሀገራት ሁለንተናዊ የከፍታና ዝቅታ መለኪያ በመሆን ስለማገልገሉ ታሪክ ምስክር ነው፡፡ በሰው ልጆች የስልጣኔ ታሪክም የእህል እና የጉልበት መዋጮ ሲያስገብሩ ከነበሩ ጥንታዊ ከተሞች እስከ ዛሬው የዲጂታል ዘመን ድረስ የዘለቀ ገድል አለው ግብር፡፡

በከተሞች መንገዶችን፣ ትምህርት ቤቶችን፣ የውሃ አቅርቦትን፣ የጤና ማዕከላትን፣ የፀጥታና ደህንነት አስጠባቂዎችን፣ ልዩ ልዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን እና መሰል ለሰው ልጆች ሕይወት መጣፈጥ አስፈላጊ የሆኑ የልማት ቅመሞችን ተጠቅሞ የዜጎችን ምቾትና ደህንነት፣ ክብር እና ከፍታን በአስተማማኝ መሰረት ላይ ለማንበር የግብር ድርሻ ወሳኝ ነው፤ ይላሉ

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## ቴክኖሎጂው በገቢ አሰባሰብ ላይ ምን ልዩነት አመጣ?

8




ፎቶ- ከገፀ ድር

በ2017 ዓ.ም በከተማዋ ገቢዎች ቢሮ የተሰበሰበ ገቢ አፈጻጸም የሚያሳይ ቻርት

## የማዕከላቱ ዘወትራዊ አገልግሎት

10



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

በለሚ ኩራ የግብርና ምርቶች ገበያ ማዕከል ግብይት ሲካሄድ

## ጥቅምት፣ ውበት እና ኪነት

12



ፎቶ- ከገፀ ድር

ውበትና ልምላሜ ያሰናኘችው ወርሃ ጥቅምት

# ለከሳሽ ያልተመቸ የፍትሐዊ ተጠቃሚነት መርህ

- ኢትዮጵያ የምትከተለው የጋራ ተጠቃሚነት መርህ የላቀ ውጤት እንዲያስገኝላት ሁሉም ዜጎች በየፊናቸው መተባበር እንዳለባቸው ተጠቁሟል

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**

ኢትዮጵያ የአፍሪካን በርሃማ ስፍራዎች ከዘመን ዘመናት ጥም የሚያረካ ውሃን ብቻ ሳይሆን ነፃነትንም ለዓለም ጥቁር ሕዝቦች ያካፈለች ድንቅ ሀገር ናት፡፡ ለዚህ ደግሞ የዓድዋ ድል ምስክር ነው፡፡ ከቅርብ ዘመን ታሪክም ብንነሳ ከዳርፉር እስከ ኮሪያ የተሻገረ እና በደም የተከፈለ ራስን ብቻ ሳይሆን ጎረቤትንም ሌላውንም፣ ሁሉንም ተጠቃሚ ለሚያደርግ ዕድገትና ሁለንተናዊ ሰላም ቀድሞ የመቆም ገድል አላት፡፡

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በፉክክር እና በትብብር መካከል ሚዛን በመጠበቅ፣ ተቃርኖዎችን

ወደ ገጽ 5 ዞሯል



ፎቶ- ከገፀ ድር

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የኢትዮጵያን የጋራ ተጠቃሚነት መርህ ያረጋገጠ ህያው ምስክር ነው




# የኮንፈረንስ ቱሪዝሙን ዕድሎች እንዴት መጠቀም ይገባል?

- በከተማዋ ከ13 ፓርኮች በተጨማሪ 157 ታሪካዊ ቅርሶችና ሌሎች የቱሪዝም መስህቦች መኖራቸው ተመላክቷል

**በሳህሉ ብርሃኑ**

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሀቢታት (ዩ.ኤን ሀቢታት) ከሁለት ዓመት በፊት የከተሞች ኢኮኖሚያዊ አበርክቶ (The Economic Role of Cities) በሚል ርዕስ ይፋ ያደረገው መረጃ እንደሚያሳየው ከተሞች ከጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት አንፃር ያላቸው ሚና ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡ በተቋሙ መረጃ መሰረት በአሁኑ ወቅት

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

አድራሻ +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ




## ግብርን በታማኝነት በመክፈል በሀገረ ግንባታው የራስን ጡብ ማኖር ይገባል!

አንድ ሀገር በኢኮኖሚ አቅም ለመፈርጠም ለስራ የሚተጉና ሰርተው ካገኙት ላይ የሀገርን ድርሻ በግብር መልክ በታማኝነት የሚከፍሉ ዜጎችን ትሻለች፡፡ የዚህ ምክንያቱ የዜጎች ፍላጎት ሊሟላና የልማት አውታሮች ሊገነቡ የሚችሉት በዋናነት ከግብር በሚሰበሰብ ሃብት በመሆኑ ነው፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በኢትዮጵያ የሚሰበሰበው ገቢ በእጅጉ እየጨመረ ነው፡፡ ለአብነትም በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከ900 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ተሰብስቧል፡፡ በ2018 በጀት ዓመትም በፌዴራል ደረጃ 1 ነጥብ 28 ትሪሊዮን ብር የግብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዷል፡፡ ይህም ዜጎች የግብርን አስፈላጊነትና ጠቀሜታ በውል ተገንዝበው ሀገራዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ መሆኑን ያመላክታል፡፡

ይህ የገቢ ግብር ዕድገት በሀገሪቷ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ ከፍተኛ ልዩነት አምጥቷል፡፡ በተለይም ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ የተከናወኑ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ለዚህ እድገት የአንበሳውን ድርሻ አበርክተዋል፡፡ መንግስት ሲተገብራቸው በቆዩ ገበታ ለሀገር፣ ገበታ ለሸገር እና ገበታ ለትውልድ የተሰኙ መርሃ ግብሮች በመላ ሀገሪቱ የኢኮኖሚ ምሶሶ የሆኑ ልማቶችን አስገኝተዋል፡፡ ለአብነትም ጎርጎራ ኢኮ ቱሪዝም፣ ወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም፣ ቤኑና መንደር፣ ጨበራ ጩርጩራን የመሳሰሉ ግዙፍ ሀብቶች ታማኝነት ግብር ከፋይ ዜጎች በከፈሉት ግብር ጭምር እውን የሆኑ አንጡራ ሀብቶች ናቸው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማም እንደ አንድነት ፓርክ፣ ወዳጅነት አደባባይ፣ የመስቀል አደባባይ መልሶ ልማት፣ እንጦጦ ፓርክ፣ ሳይንስ ሙዚየም፣ የዓድዋ ድል መታሰቢያ፣ አዲስ ዓለም አቀፍ የኮንቬንሽን ማዕከል፣ ግዙፍ የተሽከርካሪዎች ማቆያዎች፣ ፕላዛዎች፣ የገበያ ማዕከላት፣ የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማቶችም እውን የሆኑት ከየግብር ከፋዮች በተሰበሰበ ገቢ ነው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የገቢ እድገትም ከለውጡ ወዲህ እመርታዊ ለውጥ እያስመዘገበ ነው፡፡ በ2010 በጀት ዓመት መጨረሻ 33 ቢሊዮን ብር የነበረው የከተማዋ የግር ገቢ፣ በ2017 በጀት ዓመት ወደ 233 ቢሊዮን ብር አድጓል። የ2017 በጀመት ዓመቱ ገቢ አፈጻጸም ከ2016 በጀት ዓመቱ ጋር እንኳ ሲነጻጸር በ87 ቢሊዮን ብር እድገት አለው፡፡ ይህንን እመርታዊ ለውጥ ለማምጣት ከፍተኛ የሪፎርም ስራዎች መሰራታቸው አስቻይ ሁኔታን መፍጠሩ እንደተጠበቀ ሆኖ የታማኝ ግብር ከፋዮቹ አስተዋፅኦም እንደቀላል የሚታይ አይደለም፡፡

ከተማዋ ብዙ ኃላፊነት ያለባት እንደመሆኑ ልማቷን ማፋጠን እና የነዋሪዎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ጽዳቷና ውበቷ የነዋሪዎችን ብሎም የእንግዶችን ቀልብ ሳቢ ሊሆን ግድ ይለዋል፡፡ አገልግሎት አሰጣጡን ማዘመን፣ ማቀላጠፍ እና በቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ማድረግም ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ከተማዋ የምትሰበስበው ገቢ ወሳኙን ሚና ይጫወታል፡፡

እንደ ሀገር ብሎም በከተማ ደረጃ የተከናወኑ የልማት ስራዎች የቱሪዝም ዘርፉን አጠናክረዋል፤ ለኑሮ የተመቹ ከተሞችን እውን አድርገዋል፤ የትራንስፖርት፣ የጤና፣ የትምህርት እና የንግድ መሠረተ ልማቶች አቅርቦትንም በአስደናቂ ሁኔታ አሳድገዋል፡፡

ባሳለፍነው ሳምንት ለታማኝ ግብር ከፋዮች በፌዴራልና በከተማ ደረጃ እውቅናና ሽልማት ተበርክቷል፡፡ እነዚህ ግብር ከፋዮች የተለያዩ ማበረታቻዎች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ይህም መሰል ግብር ከፋዮችን ቁጥር ለማበራከት እገዛው ትልቅ ነውና ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል፡፡ ግብር ከፋዩም በተመሳሳይ ግብር የሚከፍለው ለራሱ፣ ለልጆቹ እና ለሀገሩ ተጠቃሚነት እንደሆነ በውል ተረድቶ በአግባቡ እና በወቅቱ መክፈል ይጠበቅበታል፡፡ ያለ ግብር ልማት፣ የተቀላጠፈ አገልግሎት እና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ሊመጣ እንደማይችል በመገንዘብ ዜጎች ያለማንም ጎትጓች ሀገራዊ ኃላፊነትን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## ተገቢነት የጎደለው የዋጋ ጭማሪን መከላከል የሁሉም ኃላፊነት ነው

**በኤግል ከስድስት ኪሎ**

የደመወዝ ማሻሻያው ዜና ከተሰማበት ጊዜ አንስቶ በቅጥር ሰራተኛው ላይ የተፈጠረው ደስታና መነቃቃት ቀላል አይደለም፡፡ ይሁንና ከአስደሳቹ ስሜት ጎን ለጎን ስጋትን ይዞ መምጣቱ አልቀረም፡፡ በደመወዝ ማሻሻያው ሰበብ የዋጋ ጭማሪ ይከተል ይሆን? የሚል ስጋት አድሮበታል፡፡

የኑሮ ውድነት በሀገራችን ብቻ ተከስቷል የሚል እምነት የለኝም፡፡ ዓለም አቀፍ ገፅታን መላበስ ከጀመረ ዋል አደር ብሏልና፡፡ በከተማችን ያለው እውነታም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ይህን ችግር ለመከላከልም መንግስት የሸማች ማህበራትን ከማጠናከርና በንግድ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን ለመድፈን የተለያዩ ስራዎችን እየሰራ እንደሚገኝም እሙን ነው፡፡

በተለይ በቅርቡ የተደረገው የደመወዝ ማሻሻያ አንዱ ነው፡፡ ይህን ተከትሎም በፍጆታ እቃዎችና ሸቀጦች ላይ የዋጋ ጭማሪ የሚያደርጉና የህዝቡን ቁስል የሚያባብሱ አንዳንድ ስግብግብ ነጋዴዎች እንዳሉ ታዝበናል። ታድያ ይህን ተገቢነት የጎደለው የዋጋ ጭማሪ ጥረትን መከላከል የሁሉም ኃላፊነት መሆን እንዳበት ይሰማኛል፡፡

እንደ ከተማ ጭማሪውን ምክንያት በማድረግ ሰው ሰራሽ የዋጋ ጭማሪ እንዳይፈጠር በሕገ ወጥ የንግድ እንቅስቃሴ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ መጀመሩ ይበል የሚያሰኝ ተግባር ነው፡፡ እኔ በበኩሌ ይህ እየተወሰደ ያለው የቁጥጥር ስርዓትና እርምጃ አግባብነት ያለው ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም በሸቀጦች ላይ ሰው ሰራሽ የዋጋ ጭማሪ ማድረግ አግባብነት የለውም ብቻ ሳይሆን ስግብግብነትም ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

ምርቶች ላይ አላግባብ የዋጋ ንረት መፍጠር የሚያስተዛዝብ ብቻ ሳይሆን ተጠያቂነትንም የሚያስከትል ጥፋት ነው፤ ኑሮው ከእጅ ወደ አፍ በሆነው የከተማዋ ነዋሪዎች ላይ ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ ማድረግ አይገባም፡፡

በንግድ ስርዓት ላይ በሕጋዊ መንገድ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ነጋዴዎች እንዳሉ ሁሉ በአንጻሩ በሕገ-ወጥ የንግድ ሰንሰለት ውስጥ ሲሳተፉ የሚገኙ መኖራቸውን እና ይህም የግብይት ስርዓቱን የሚፈትን መሆኑን አስረጂ አያስፈልገውም፡፡ በቅርቡ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ክትትልና ቁጥጥር ካደረገባቸው ነጋዴዎች መካከል ከ110 ሺህ በላይ የሚሆኑት ህግ ጥሰው በመገኘታቸው መቀጣታቸውን ይፋ አድርጓል፡፡

በአፍቅሮተ-ነዋይ የታወሩ ስግብግብ ነጋዴዎች ለሠራተኛው ኑሮ ማሻሻያ የተደረገውን የደመወዝ ማሻሻያ ምክንያት በማድረግ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት መሞከራቸው ለማንም የሚበጅ አይደለምና ይታረም በማለት ምክሬን አካፍላለሁ፡፡

ህብረተሰቡም ቢሆን በንግድ እንቅስቃሴው ላይ የሚያጋጥሙ ስርዓት አልበኝነቶችን ዝም ሊል አይገባም፡፡ ይልቁንም ህገ ወጥ እና ስግብግብ ነጋዴዎችን ሲመለከት ማጋለጥ ብሎም የንግድ ሂደቱን ቁጥጥር ከሚያደርጉ አካላት ጋር በመተባበር ህገ ወጥ ድርጊቱን በጋራ በመከላከል የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው እላለሁ፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜልባ ፕሪንቲንግ ፐብሊሺንግ ኤንድ ፓኬጂንግ ሼር ካምፓኒ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ለይላ መሀመድ
አብርሃም ገብሬ
ፋንታነሽ ተፈራ
ሽዋርካብሽ ቦጋለ
ይግለጡ ጓዴ

**ዋና አዘጋጅ**
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# የከተማዋ ... ከገጽ 1 የዞረ

ጀርመናዊው የፖለቲካል ኢኮኖሚ ምሁር ፕሮፌሰር ሪቻርድ ኤ. ሙስግሬቭ እ.ኤ.አ በ1959 የመንግስት ፋይናንስ ጽንሰ-ሐሳብ (Theory of Public Finance) በሚል ርዕስ ባሳተሙት መፅሐፋቸው፡፡

በከተሞች ኢኮኖሚ ላይ ያተኮሩ ከአስር በላይ ጥናታዊ የምርምር መፅሐፍትንና በዓለም አቀፍ ጆርናሎች ላይ የታተሙ የምርምር ፅሑፎችን ያበረከቱት እኚህ ምሁር፣ የመንግስት ፋይናንስ ፅንሰ ሀሳብ አፍላቂዎች መካከል አንዱ ናቸው፡፡ ግብር የከተሞችን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ከፍታ ለማረጋገጥ አስፈላጊ ከሆኑት ወሳኝ ጉዳዮች መካከል ቀዳሚው እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ ግብር የከተሞችን ሕይወት ማስቀጠያ እስትንፋስ፣ ለዘመን ዘመናትም ነፍስ ዘርተው እንዲኖሩ ለዕድገታቸው የሚያስፈልጉ ነገሮችን ማድረሻ የደም ሥር ነውም ይላሉ፡፡

የዓለም ባንክ እ.ኤ.አ ነሐሴ 1977 (The Incidence of Urban Property Taxation in Developing Countries) በሚል ርዕስ ባሰፈረው መረጃ እንደተመላከተው ግብር፣ ለከተሞች ሕልውና ወሳኝ መሆኑን ለማረጋገጥ ቀጣዮቹን አምስት ነጥቦች በአስረጅነት አስቀምጧል፡፡ እነዚህም ቋሚ የግብር ገቢ ከሌለ ከተሞች ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴያቸውን የሚያፋጥኑ ዋና ዋና መሠረተ ልማቶችን ማቅረብ አይችሉም፤ ህዝብን የሚጠቅሙ ኢንቨስትመንቶችን ለማስፋፋትና ለማሳደግ ይቸገራሉ፤ በፍትሐዊነት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ትስስርን ማጎልበት ያቅታቸዋል፤ በገንዘብ አቅምና በሌሎች ምጣኔ ሀብታዊ ጉዳዮች ራስን በራስ የማስተዳደር እና ልዩ ልዩ ችግሮችን የመቋቋም አቅምን ያጣሉ፤ እንዲሁም በግብር ከፋዩ ተሳትፎ በመታገዝ ለሁሉም ምቹ የሆነ አስተዳደራዊ ስርዓትን ለማስፈን ይቸገራሉ፡፡

መረጃው ግብርን በአግባቡ በመሰብሰብ፣ አዋጭና ዘመናዊ አሰራሮችን በመዘርጋት፣ ለግብር ከፋዩ ቀላል አሰራሮችን ተግባራዊ በማድረግ፣ ከትምህርት ቤት ጀምሮ ስለ ግብርና ሀገራዊ ጠቀሜታው ግንዛቤ በመፍጠር እንዲሁም ለምስጉን ግብር ከፋዮች የተለያዩ ድጋፎችን፣ ሽልማቶችን እና ዕውቅናዎችን በመስጠት ሁለንተናዊ ከፍታቸውን ማላቅ ከቻሉ የዓለማችን ከተሞች መካከል ሲንጋፖር፣ ሴኡል እና ቦጎታን በዋቢነት አንስቷል፡፡

በከተሞች ዕድገትና ግብር ዙሪያ የዓለም ታሪክ እና ልምድ እንደሚያሳየው ዜጎች ግብር በታማኝነትና በወቅቱ ሲከፍሉ እና የየአካባቢው መንግስታትም የተሰበሰበውን ግብር በግልፅ እና በብቃት ሲጠቀሙበት ከተሞች በፍጥነት ያድጋሉ የሚሉት በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ ተባባሪ ፕሮፌሰር ይንገስ አለሙ (ዶ/ር) ለዚህም በአጭር ዓመታት ውስጥ ማደግ ከቻሉ ከተሞች መካከል ከደቡብ ኮሪያ ሴኡልን፣ ከሲንጋፖር የሲንጋፖር ከተማን እንዲሁም ከሲዊዲን የስቶክሆልም ከተሞችን ፈጣን ዕድገት በዋቢነት ጠቅሰዋል፡፡



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ለግብር ከፋዮች እውቅና በሰጡበት ወቅት መልዕክት አስተላልፈዋል

አዲስ አበባም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በከፍተኛ ፍጥነት ላይ መሆኗን የተናገሩት መምህር ይንገስ (ዶ/ር) ይህም ከምታገኘው ከፍ ያለ የግብር ገቢ፤ ይህንን ግብርም ለሚገባው መሰረተ ልማት ማዋል በመቻሉ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

ግብርን በታማኝነት መክፈል የበለፀገች ከተማን ለመገንባት መሰረት ነው የሚሉት የምጣኔ ሀብት መምህሩ፣ ሀገር ለስራ የሚተጉና ሰርተው ካገኙት ላይ የሀገርን ድርሻ በታማኝነት ግብር የሚከፍሉ ዜጎች ያስፈልጓታል፡፡ ይህም ዞሮ ዞሮ ለማህበረሰቡ ምቾት የሚሆኑ ልማቶችን ለመገንባት የሚውል ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ አዲስ አበባ ከተማን በዋቢነት ማንሳት እንችላለን፡፡ ይህም ዕድገት ተጠናክሮ እንዲቀጥል መንግስት ከሚያደርጋቸው አሰራርን ቀለል የማድረግ፣ ዕውቅናና ሽልማትን ከመስጠት ባሻገር ማህበረሰቡ ግብሩን በታማኝነት የመክፈል ልምዱን ከፍ ማድረግ እንዳለበትም መክረዋል፡፡

ባሳለፍነው ሐሙስም ጥቅምት 6 ቀን 2018 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ "ግብር ለሃገር ክብር" በሚል መሪ ቃል ከፍተኛ የመንግስት አመራሮች እና ግብር ከፋዮች በተገኙበት የሽልማት እና የእውቅና መርኃ ግብር በአዲስ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከል አካሂዷል፡፡ በዚሁ ዕለት የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ አቶ ቢኒያም ምክሩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የገቢ እድገት ከለውጡ ወዲህ እመርታዊ ዕድገት እያስመዘገበ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ለአብነትም በ2010 በጀት ዓመት መጨረሻ 33 ቢሊዮን ብር የነበረው የገቢ አሰባሰብ በ2017 በጀት ዓመት ወደ 233 ቢሊዮን ብር ማደጉን አስታውሰዋል። የ2017 በጀት ዓመት አፈጻጸም ከ2016 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር በ87 ቢሊዮን ብር እድገት ማሳየቱንም ጠቅሰዋል። ይህንን እመርታዊ ለውጥ ለማምጣት ከፍተኛ የሪፎርም ስራዎች መሰራታቸውን የጠቆሙት አቶ ቢኒያም፣ የገቢ እድገቱ እንዲመዘገብ የከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ ድጋፍ ማድረጉንም ተናግረዋል፡፡

**በከተሞች እድገት፣ በወጣቶች ስራ ዕድል ፈጠራና የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጡ ዘርፎች ለተመዘገቡት ጉልህ ስኬቶች የታማኝ ግብር ከፋዮች ሚና ወሳኝ ነው**

እንደ ከተማ ለታማኝ ግብር ከፋዮች የተደረገውን ዕውቅናና ሽልማት አስመልክቶ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ባስተላለፉት መልዕክትም ከተማዋ ከታማኝ ግብር ከፋዮች በምትሰበስበው ገቢ በአስደናቂ ሁኔታ የገነባቻቸው ሜጋ ፕሮጀክቶች፣ የወንዝ ዳርቻና የኮሪደር ልማት፣ የህዝቡን የኑሮ ጫና ያቀለሉ ስራዎች፣ የተማሪዎች ምገባ እና መሰል ስራዎች ከተማዋን ለቢዝነስ እና ለመኖር የተመቸች ንፁህ፣ ጤናማ አካባቢ እና በዓለም አቀፍ ደረጃም ተመራጭና ተወዳዳሪ እንድትሆን እንዳስቻላትም ገልፀዋል፡፡

በቀጣይ በግብር አሰባሰብ ዙሪያ የአገልግሎት አሰጣጡን ይበልጡን ዲጂታላይዝ በማድረግ፣ በማዘመን እና ተጠያቂነትን በማስፈን ክፍተቶችን እየሞላን፣ ህፀጾችን እያረምን የሁለንተናዊ ብልፅግና ተምሳሌት የሆነች ከተማን እየገነባን ነው ብለዋል ከንቲባ አዳነች አቤቤ።

ለሽልማትና ለእውቅና የበቃችሁ ግብር ከፋዮቻችን ለታማኝነታችሁ ምስጋናዬ የላቀ ነው ያሉት ከንቲባዋ፣ በተለይም የወርቅ እና የፕላቲኒየም ደረጃ ግብር ከፋዮች የዘርፉ አምባሳደሮቻችን በመሆናችሁ በከተማችን በየትኛውም መንግስታዊ አገልግሎት እና ኩነት የቅድሚያ ቅድሚያ እንድትስተናገዱ እና "VIP" ፕሮቶኮል እንዲሰጣችሁ መወሰናችንን ስገልፅ ሌሎችም የእናንተን አርአያነት እንደሚከተሉ በማመን ነውም ብለዋል፡፡

መምህር ይንገስ አለሙ (ዶ/ር) እንደሚሉት እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ከተማ ለምስጉን ግብር ከፋዮች ዕውቅና እና ሽልማት መስጠቱ የበለጠ ግብራቸውን በአግባቡ እንዲከፍሉ፣ ምርትና ምርታማነታቸውን እንዲጨምሩ፣ ሌሎች ምስጉን ግብር ከፋዮች እንዲበራከቱ የሚያነቃቃ እና ለሁሉም ምቹ የሆነች ከተማና ሀገርን ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት የበለጠ የሚያግዝ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

በእውቅናና ሽልማት መርኃ ግብሩ የተገኙት የፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አገኘሁ ተሻገር በበኩላቸው፣ አዲስ አበባ የአፍሪካ ከተሞች ምሳሌ እንድትሆን የከተማ አስተዳደሩ እያደረገ ያለው ጥረት የሚደነቅ ነው ብለዋል፡፡

ሀገርን ከድህነት ለማላቀቅና ልማትን ለማረጋገጥ የግብር ከፋዩ ማህበረሰብ ተቀናጅቶ መስራት አስፈላጊ መሆኑን የጠቀሱት አፈ ጉባኤ አገኘሁ ተሻገር፣ በከተሞች እድገት፣ በወጣቶች ስራ ዕድል ፈጠራና የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጡ ዘርፎች ለተመዘገቡት ጉልህ ስኬቶች የታማኝ ግብር ከፋዮች ሚና ወሳኝ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

በከተማ አስተዳደሩ እውቅናና ሽልማት ከተሰጣቸው ምስጉን ግብር ከፋዮች መካከል ደረጀ አስናቀ ወልደሚካኤል የመድኃኒት አስመጭ አንዱ ነው፡፡ የድርጅቱ ኃላፊ አቶ ደረጀ አስናቀ ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደገለፁት ድርጅታቸው ለአምስት ተከታታይ ዓመታት እውቅናና ሽልማት ተሰጥቶታል፡፡

እንደ ዜጋ ግብርን ሳይደብቁ በወቅቱና በታማኝነት በመክፈላቸው ከከተማ አስተዳደሩ ዕውቅናና ሽልማት ማግኘታቸው ከፍ ያለ ደስታና ለበለጠ ስራ እንዲተጉ መነቃቃትን እንደፈጠረላቸውም አቶ ደረጀ ተናግረዋል፡፡

አቶ ደረጀ እንደሚሉት ግብርን ሳይደብቁ በወቅቱ መክፈል ጥቅሙ ለራስ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በአዲስ አበባ ህዝቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ልዩ ልዩ ልማቶች የተከናወኑት ከምስጉን ግብር ከፋዮች በሚሰበሰብ ገቢ ነው፡፡ በመሆኑም ግብርን ሳይደብቁ በወቅቱ መክፈል ለሁላችንም ተጠቃሚነት፣ ለከተማችን እና ለሀገራችን ሁለንተናዊ ከፍታ ያለው ድርሻ ከፍ ያለ በመሆኑ ሁሉም በወቅቱና በታማኝነት ግብር መክፈል ይኖርበታል፡፡

# የውሃ ውስጥ በረከት

- ንጋት ሐይቅ በተፈጥሯዊ የዓሣ ማምረት ዘዴ ብቻ በዓመት እስከ 10 ሺህ ቶን ዓሣ የማምረት አቅም እንዳለው ተገልጿል



ፎቶ- ከገፀ ድር
በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ላይ የተፈጠረው ንጋት ሐይቅ ከፊል ገፅታ

**በመለሰ ተሰጋ**

“ዓሣ አበላሻለሁ ዓባይ ዳር ነው ቤቴ፤

ዶሮ መረቅማ ከወዴት አባቴ” በሚለው የድምጻዊ አሰፋ አባተ ዜማ ውስጥ በግጥም ስር የተሸሸጉ እልፍ ቁምነገሮች አሉ፡፡ ለዛሬ ሁለቱን እናንሳ። ወንዝ ዳር፣ ሐይቅ ዳር አሊያም ባህር ዳር ... ያለ ሰው፣ ዓሣ አይቸግረውም የሚለው አንዱ ነው። ሌላውና ልብ ልንነው የሚገባው ጉዳይ ደግሞ “ዶሮ መረቅማ ከወዴት አባቴ” የምትለው ስንኝ ውስጥ የተቀመጠው ጭብጥ ነው፡፡ በሆነ ነገር የዶሮ መረቅ ከዓሣ እንደሚበልጥ ይነግረናልና፡፡

በርግጥ በፕሮቲን ይዘታቸው ከፍ ማለት ምክንያት እንደ ዓሣዎቹ ዝርያና ሁኔታ አሊያም እንደ ዶሮዎቹ አይነት አንዱ አንዱን እየተካ ቢበላለጡም ዓሣን የመሰለ ግብዣ ቢያስደስት ነው እንጂ የሚያስቆጭ አይደለም፡፡ ዓሣ መመገብ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው የሥነ ምግብ እና የጤና ባለሙያዎች ደጋግመው ይመክሩናል፤ የተለያዩ ጥናቶችም ይህንን እውነት ይመሰክሩልናል፡፡

ለዚህ ደግሞ ግድቦቻቸውን አሊያም የውሃ ሃብቶቻቸውን ለተለያዩ ጉዳዮች ከመጠቀም ባሻገር ዓሣን በማርባትና በመመገብ ጠንካራ ባህል ያላቸው ሀገራት ስላገኙት ከፍ ያለ ፋይዳ በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ንጋት ሐይቅ ላይ በመንፈስ አረፍ ብለን እንመለከታለን፡፡

በሰሜን ምስራቅ እስያ የምትገኘው ጃፓን በባህር የተከበበች ድንቅ ምድር ናት፡፡ ይህ ደግሞ ዓሣን ከባህላዊ ምግቦቿ አንዱ እንዲሆን አድርጎታል። ጃፓናውያን ዓሣን ‘koi’ ወይም ፍቅር እያሉ ይጠሩታል፡፡ እንደ ጃፓን ቱደይ ዘገባ አንድ ጃፓናዊ በቀን ከ30 ግራም በላይ ዓሣ ይመገባል፡፡

ፖርቹጋል ከአውሮፓ ከፍተኛ ዓሣ ከሚመገቡ ሀገራት መካከል አንዷ ናት። አማካኝ ዓመታዊ ፍጆታ በአንድ ሰው 57 ኪሎ ግራም ነው፡፡ በተመሳሳይ ኖርዌይ ዓሣን በብዛት ከሚመገቡ ሀገራት ተጠቃሽ ናት፡፡ በዓመት በነፍስ ወከፍ ከ50 ኪሎ

> **ሀገራት ግድቦቻቸውን ለዓሣ እርባታ እና የምግብ ፍጆታን በሚሸፍኑ ልማቶች ላይ በስፋት በማዋል የበለጠ ተጠቃሚ ሆነዋል**

ግራም በላይ ዓሣ ለምግብነት ይውላል፡፡ በተለይም በተማሪዎች የምሳ ዕቃ ውስጥ፣ በህሙማን መጠየቂያ ማዕድ ውስጥ እንዲሁም በታላላቅ ብሔራዊ በዓላት በክብር የሚበላ ጣፋጭና ተመራጭ ምግብ ነው፤ ዓሣ፡፡

ይህም ብቻ ሳይሆን ኖርዌይ ዓሣን ኤክስፖርት በማድረግ በዓመት ዳጎስ ያለ ገቢ ታገኝበታለች፡፡ ለአብነትም እ.ኤ.አ. 2024 የባህር ምግቦችን ወደ ውጭ በመላክ 175 ነጥብ 4 ቢሊዮን ኖክ (NOK) ማግኘቷን የኖርዌይ የባህር ምግቦች ምክር ቤት እ.ኤ.አ ጥር 2024 ይፋ ያደረገው መረጃ ያመለክታል፡፡

እንደ ምክር ቤቱ መረጃ ከሆነ ሀገራት የውሃ ሃብታቸውን ለዓሣ እርባታ በመጠቀም ከሚያገኙት ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ ባሻገር ጤናማ፣ ንቁ፣ የፈጠራ ክህሎትን የታደለ እና የተረጋጋ ማህበረሰብ መፍጠር ችለዋል፡፡

ዓሣን መመገብ ባህላቸው ካደረጉ እና በኢኮኖሚና መሰል ጉዳዮች ተጠቃሚ ከሆኑ ሀገራት መካከል ደቡብ ኮሪያ፣ ህንድ እና ቻይናን የመሳሰሉ ሀገራት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በተለይም እንደ ህዳሴ ግድብ ያሉ የንጋት ሐይቅን የመሳሰሉ ግድቦቻቸውን በመጠቀም ለሀገር ውስጥ የምግብ ፍጆታ ብቻ ሳይሆን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ የሆኑ ሀገራትን በዋቢነት ማንሳት እንችላለን፡፡

ግድቦቻቸውን ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫነት፣ ለመስኖ፣ ጎርፍን ለመከላከል፣ ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ ለቱሪዝምና መሰል ነገሮች ከመጠቀማቸው ባሻገር የምግብ ዋስትናቸውን ጭምር ማረጋገጥ የቻሉ ሀገራት እንዳሉ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር ነሐሴ 2020 በታተመው “Water Management for Sustainable Food Production” በተሰኘው መፅሐፍ ላይ ሰፍሯል፡፡

በመፅሐፉ ላይ እንደሰፈረው በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ከመጣው የህዝብ ቁጥርና ፍላጎት አንፃር ዓለም የምግብ ምርትን ከ70 በመቶ በላይ የማሳደግ ፈተና ተጋርጦበታል። በተለይ ዘላቂነት ያለው የምግብ ምርት ለማግኘት ግድቦችን በብዙ መልኩ ለምርትና ምርታማነት መጠቀም ይገባል፡፡

በሌላ በኩልም በምግብ እህል ራስን ከመቻል አንፃር ሀገራት የውሃ ሀብት አስተዳደርና አጠቃቀማቸውን በትኩረት ሊመለከቱ እንደሚገባም በመፅሐፉ ሰፍሯል፡፡ አንዳንድ ሀገራት ደግሞ ግድቦቻቸውን ለዓሣ እርባታ እና የምግብ ፍጆታን በሚሸፍኑ ልማቶች ላይ በስፋት በማዋል የበለጠ ተጠቃሚ እንደሆኑም ተመላክቷል፡፡

ለአብነትም በደቡብ-ምስራቅ ባንግላዲሽ በራንጋማቲ አውራጃ ውስጥ በካርናፉሊ ወንዝ ላይ ያለው የካፕታይ ግድብ እ.ኤ.አ በ1962 የተገነባ ነው። ይህ የካፕታይ ሐይቅ ግድብ 58 ሺህ 300 ሄክታር ይሸፍናል፡፡ 9 ሜትር ጥልቀትና 36 ሜትር ከፍታም አለው። ባንግላዲሽ ከዚህ ግድብ በምታገኘው የዓሣ ምርት በአመዛኙ የሀገር ውስጥ የምግብ ፍጆታዋን ትሸፍናለች፡፡

ለልዩ ልዩ ጉዳዮች የሰራቻቸውን ግድቦች ለዓሣ ምርት ጭምር በመጠቀም ከፍተኛ ለውጥ ካመጡ ሀገራት መካከል ህንድ አንዷ ናት፡፡ የዓለም የምግብ ድርጅት መረጃ እንደሚያመለክተው ህንድ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ 19 ሺህ በላይ ግድቦች አሏት፡፡ በዓመትም 93 ሺህ 650 ቶን ዓሣ በአማካኝ ታመርታለች፡፡ በዚህም ለበርካቶችም የስራ ዕድል ከመፍጠሯና የውጭ ምንዛሬ ጭምር ከማግኘቷ ባሻገር የምግብ ፍጆታዋንም ትደጉምበታለች፡፡

በሌላ በኩል ብራዚል ብዙ ትላልቅ የውሃ ማጠራቀሚያዎች ያሏቸው ትላልቅ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ግድቦች አሏት። በግድቦቹ የተፈጠሩት ሐይቆች ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ሲውሉ 3 ነጥብ 5 ሚሊዮን ቶን ዓሣ በዓመት የማምረት አቅም አላቸው፡፡

ቴላፒያ የተሰኘው ዓሣ ለውጭ ገበያ በጣም ተፈላጊ ሲሆን፣ ብራዚል እ.ኤ.አ በ2021 ወደ 10 ቶን የሚጠጋ ዓሣ ወደ ውጭ ልካለች፡፡ የብራዚል ዓሣዎችን በዋናነት ከሚገዙ ሀገራት መካከል ዩናይትድ ስቴትስ፣ ኮሎምቢያ እና ቻይና መሆናቸውን ሳኦ ፖሎ የሚገኘው የብራዚል አረብ ንግድ ምክር ቤት የዜና ጣቢያ (ANBA) ሰሞነኛ መረጃ ያመላክታል፡፡

በሌላ በኩል ቻይና፣ ኖርዌይ፣ ቬትናም፣ ህንድ፣ ቺሊ፣ ኢኳዶር፣ ታይላንድ፣ አሜሪካ፣ ሩሲያና ኢንዶኔዥያ እ.ኤ.አ በ2024 እና 2025 የዓሣ ምርትን በስፋት ለዓለም ገበያ ያቀረቡ ሀገራት ሲሆኑ ዋና ምንጫቸውም ግድቦቻቸውን በአግባቡ በመጠቀማቸው እንደሆነ ዓለም አቀፉ የንግድ መረጃዎች ምንጭ የሆነው ትሬድ ኢንዴክስ (TradeImeX) እ.ኤ.አ ሚያዚያ 3 ቀን 2024 ይፋ ያደረገው መረጃ ያመላክታል፡፡

ይህንን ሀቅ ይዘን ወደ ራሳችን ስንመለስ ከኢትዮጵያ ፈልቆ ሜዳና ተራራውን ፈልቅቆ፣ ለም አፈሯን እየጠራረገ የሚነጉደው የዓባይን ወንዝ በረከት በመጠቀም ካርቱምና ካይሮን በመሳሰሉ ከተሞች የዓሣ ቋንጣ በርካሽ ይቸበቸባል። አያሌዎችንም ከርሃብ ይታደጋል፡፡

ግብፅ ከዓባይ ወንዝ በየዓመቱ ከ650 ሺህ ቶን ዓሣ በላይ ታመርታለች፡፡ ይህ ከፍተኛ ምርት ዓሣ በተመጣጣኝ ዋጋ ለገበያ እንዲቀርብና የምግብ ዋስትና እንዲረጋገጥ ከፍተኛ ድርሻ አለው። በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ግብፃውያን የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ አስችሏቸዋል፡፡ ይህንን እውነት በዝርዝር መመልከት ካሻዎ የኬኒያ ዕለታዊ ጋዜጣ ቢዝነስ ዴይሊ እ.ኤ.አ ታህሳስ 2020 (River Nile’s innovative fish farms feed millions) በሚል ርዕስ ይፋ ያደረገውን መረጃ ይመልከቱ፡፡

የዓባይን ወንዝ የዓሣ ሀብት እያሰብን ወደ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ስናመራ ብዙ በረከቶችን እናገኛለን፡፡ ይሄውም ከህዳሴው ግድብ መጠናቀቅ ጋር ተያይዞ በአካባቢው 1 ሺህ 680 ስኩር ኪሎ ሜትር ስፋት ባለው መሬት ላይ በአማካኝ 44 ሜትር ጥልቀት ያለውና 74 ቢሊዮን ሜትር ኪዮብ ውሃ የመያዝ አቅም ያለው ሰው ሰራሽ ሐይቅ ተፈጥሯል፡፡

በሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ የግብርና ኮሌጅ የእንስሳት ሳይንስ ትምህርት ክፍል ፕሮፌሰር ዮሴፍ ተክለ ጊዮርጊስ በ2010 ዓ.ም በአፍሪካና በኢትዮጵያ ሐይቆች ላይ ያደረጉት ጥናት እንደሚያመላክተው የህዳሴው ግድብ ሰው ሰራሽ ሐይቅ (ንጋት ሐይቅ) ከስፋቱና ውሃ ከመያዝ አቅሙ አንፃር በተፈጥሯዊ የዓሣ ማምረት ዘዴ ብቻ በዓመት እስከ 10 ሺህ ቶን ዓሣ የማምረት አቅም ይኖረዋል፡፡ በተለይም ዘመናዊ የዓሣ እርባታ ዘዴን በመተግበር የንጋት ሐይቅን ዓሣ የማምረት አቅም ከዚህ በብዙ እጥፍ ማሳደግ እንደሚቻልም መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በእርግጥም እንደ ንጋት ሐይቅ ባሉ የውሃ ሃብቶቻችን ዓሣ የማምረት አቅማችንን በአግባቡ ስንጠቀም፣ የአመጋገብ ባህላችንን ከዓሣ ጋር ስናዛምደው ከላይ እንደ ጠቃቀስናቸው ጃፓን፣ ቻይና እና መሰል ሀገራት ለስራ፣ ለፈጠራ የተጋ እና የተረጋጋ ማህበረሰብን ለመገንባት እና ሀገርን በሁለንተናዊ መልኩ በፅኑ መሰረት ላይ ማንበር እንችላለን።

# ለከሳሽ ... ከገጽ 1 የዞረ

በማስታረቅ የሚጓዝ መሆን እንዳለበት ታምኖበት በዚሁ ስልት እየተሰራ ይገኛል። በተጨማሪም ሀገራዊ ክብርን ያስቀደመ፣ ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ፣ ጎረቤት ሀገራትን ያስቀደመ የውጭ ግንኙነት፣ ቀጣናዊ ትብብርና የኢኮኖሚ ውህደትን ያስቀደሙ ነጥቦች ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራባቸው የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ አንኳር ጉዳዮች ስለመሆናቸው በፖሊሲ ሰነዱ ላይ ሰፍሯል፡፡

ኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት እሳቤ የሚመነጨው ጥቅምን ከማሳደድ ሳይሆን መልካም ትብብርን ከማስቀደም ነው ብላ ታምናለች። በመሆኑም ከሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት የጋራ ተጠቃሚነትን መርህ ባደረገ መልኩ ነው፡፡ በዚህ ስልት አሸናፊ የሆነችባቸው በርካታ ድሎች አሏት፤ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አንዱ ማሳያ ነው፡፡

በተቃራኒው ግብፅ እኔ ብቻ ልጠቀም የምትል ሀገር ናት፤ ይህን በተግባርም አሳይታለች፤ እያንዳንዱ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሙሌት በተደረገ ቁጥር ክስ ስታቀርብ ቆይታለች፤ ኢትዮጵያን በፀጥታው ምክር ቤት በተደጋጋሚ ከስሳ የውይይት አጀንዳ ማሟሻ ስታደርጋት መቆየቷ የሚዘነጋ አይደለም፡፡ አሁንም ከክስ ወደኋላ አላለችም፡፡

በኢትዮጵያ ታሪክ ከትናንት እስከ ዛሬ የዘለቀ ሀብቶችን በጋራ የመጠቀም ቀናኢ አመለካከት አለ፤ ለዚህም ብዙ አብነቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከፍ ብለንም እንደጠቀስነው ለዘመናት ከነ ሙሉ ክብሩ የሚፈስሰውን የዓባይ ወንዝ በጋራ ተጠቃሚነት መርህ አልምታ እውን ያደረገችው የህዳሴው ግድብ ምስክር ነው፡፡

የናይል ተፋሰስ ኢኒሼቲቭ (ኤን.ቢ.አይ) እ.ኤ.አ በ1999 የተቋቋመ ሲሆን፣ በተፋሰሱ አባል ሀገራት መካከል የናይል ወንዝን በጋራ በማስተዋወቅ እና በማስተዳደር ላይ የተመሰረተ ዓላማ ያለው ነው። በመሰረታዊነት የናይል ውሃ 'ፍትሐዊ እና ዘላቂነት ያለው አጠቃቀም' በሚለው መርህ መሰረት የኢኮኖሚ እድገትን፣ ክልላዊ ሰላምን እና የአካባቢ ጥበቃን ለማጎልበት ነው የተመሰረተው። ይህ ደግሞ ዘመናዊና ፍትሐዊ አስተሳሰብን የተከተለ ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርገው የኢትዮጵያ ፅኑ አቋም ጋር የተወዳጀ ነው፡፡

85 በመቶ የሚሆነው የናይል ውሃ ምንጭ የሆነችው ኢትዮጵያ ሁሉንም የተፋሰሱ ሀገራት ተጠቃሚ የሚያደርግ ፍትሐዊ እና ልማት ተኮር የሆነ አጠቃቀምን ትደግፋለች። በመሆኑም የጋራ ኃላፊነት እና የጋራ ተጠቃሚነት መርህን በመደገፍ አንድ ሀገር ብቻ ወንዙን በብቸኝነት ሊቆጣጠር እንደማይገባ ሀገሪቱ አፅንኦት ሰጥታለች ይላል፣ "በዓባይ ተፋሰስ የውሃ መጋራት ተግዳሮቶች፣ ጂኦ ፖለቲካ መቀየር እና የአየር ንብረት ለውጥ።" በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ 2011 በሃይድሮሎጂካል ሳይንስ ጆርናል የታተመ ጥናታዊ ፅሑፍ፡፡

በርግጥም ኢትዮጵያ በአፍሪካ ልማት ላይ ያላት ሚና ምን ያህል ከፍ ያለ እንደሆነ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አንዱ ምስክር ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከጥንታዊ መንግሥቶቿ ጀምሮ እስከ አሁን ያስመዘገበቻቸው ስኬቶች የአፍሪካን የታሪክ ሂደት ባማረ መልኩ በመቅረጽ ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውታለች የሚሉት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአሜሪካና የአውሮፓ ጉዳዮች ተመራማሪ አቶ ሽመልስ ኃይሉ፣ የዓለም አቀፍ የሀገራት ግንኙነት የሚመሰረተው በጋራ ትብብር ወይም በጋራ ፍላጎት ላይ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

የህዳሴው ግድብ የኢትዮጵያን የጋራ ተጠቃሚነት መርህ ያረጋገጠ ህያው ምስክር ነው

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሀገራት ሀብት ስላላቸው ወይም የኢኮኖሚ፣ የኢንዱስትሪና የተለያዩ ነገሮች ስላሏቸው ያላቸውን አቅም ተጠቅመው ሌሎች፣ ላይ ጫና በመፍጠር የማይገባቸውን ጉዳዮች ጭምር ለመውሰድ ወይም ለማግኘት የሚሄዱበት አግባብም እንዳለም የጠቀሱት አቶ ሽመልስ፣ ለዚህም ሲባል ዓለም ፍትሐዊ ናት ተብሎ እንደማይታመን ተናግረዋል፡፡

ዓለም ላይ አንዳንዶች ኢ- ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ግፊት እያደረጉ የሚፈልጉትን ነገር ሲያገኙ ሌሎቹ ደግሞ ፍትሐዊ ዓለም መምጣት አለበት፤ ለዓለም ፍትህ ይገባል፤ የዓለምን ሀብት እኩልና በፍትሐዊ መንገድ በትብብር መጠቀም አለብን ብለው ያስባሉ፤ ያሉት አቶ ሽመልስ፣ የግብፅ እና የኢትዮጵያ ግንኙነትም በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ማየት እንደሚቻል ነው ያስረዱት፡፡

መንግስታት ቢቀያየሩም የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ላይ ጉልህ ልዩነት እንደማይመጣ አውስተው፣ ከእነዚህም አንዱ ዓለም ላይም ሆነ አካባቢያችን ላይ ፍትሐዊ የሆነ ግንኙነት መኖር አለበት የሚለው ነው፡፡ ለአፍሪካ ፍትህ በፀጥታው ምክር ቤትም ሆነ በሌሎች ዓለም አቀፍ መድረኮች ተፅዕኖ ፈጣሪ ተቋማት እና ህብረቶች ውክልና ያስፈልጋታል፤ የጋራ ሀብቶችን በፍትሐዊና በትብብር መጠቀም ይኖርባታል የሚል ፅኑ አቋም እንዳላትም ጠቅሰዋል፡፡

ግብፅ ደግሞ ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ እኔ ብቻ ልጠቀም የሚል አቋም ነው የምታንፀባርቀው የሚሉት አቶ ሽመልስ፣ ለዚህ ደግሞ የዓባይ ውሃ ትልቅ ማሳያ ነው፡፡ ምንም እንኳን 85 በመቶ በላይ የሚሆነው ውሃ ከኢትዮጵያ የሚመነጭ ቢሆንም ያንን በመካድና ዓለምንም በመሸወድ በኢ-ፍትሐዊነት መንገድ ወንዙን ስትጠቀምበት እንደኖረችም አውስተዋል፡፡

የግብፅ ዓላማ ከዚህም በላይ እንደነበር የገለፁት አቶ ሽመልስ፣ የዓባይን ምንጭ ለመቆጣጠር የተለያዩ ጦርነቶችን ኢትዮጵያ ላይ መክፈታቸውን ታሪካዊ ድርሳናት ይመሰክራሉ፤ በተለይም በጉራ እና በጉንደት የከፈቱት ጦርነት በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት ቢጠናቀቁም ዓላማቸው ግን ቀላል አልነበረም ብለዋል።

ከጉራ እና ጉንደት ድሎች በኋላ ግብፅ ኢትዮጵያን በቀጥታ መውጋት እንደማይቻላት በመገንዘብ ውስጣዊ የፖለቲካ ክፍፍሎችን በመጠቀም ኢትዮጵያን ደካማና የተከፋፋለች ሀገር ማድረግ፣ እንዲሁም ዓለም ላይ ያላቸውን የፖለቲካ ተፅዕኖ ተጠቅመው የገንዘብ ተቋማት ለኢትዮጵያ ብድርና የተለያዩ ድጋፎችን እንዳይሰጡ በማድረግ ተፅዕኖ ስታሳድር ቆይታለችም ብለዋል፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ያሉት ሀገራት በአንድ በኩል ለዓለም አቀፍ እውቅና ትብብር ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ተጋድሎ እያደረጉ በሌላ በኩል ደግሞ ውስጣዊ አቅማቸውን በማጠናከር ተፅዕኖዎችን መቋቋም አለባቸው ያሉት አቶ ሽመልስ፣ ኢትዮጵያ በዚህ መንገድ ተጉዛ ውጤት አግኝታለች፤ ለዚህ ማሳያ ከሆኑት መካከል የህዳሴው ግድብ አንዱ ነው፡፡ ይህ ግድብ ኢትዮጵያ የራሷ የሆነውን ሀብት የመጠቀም መብቷን የምታሳይበት ብቻ ሳይሆን ዓለም ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልን ማስፈን እንዳለባት የምትመሰክርበት ድል እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

አቶ ሽመልስ በማብራሪያቸው፣ ግብፅም እየሄደችበት ያለው ኢ-ፍትሐዊ መንገድ መሆኑን ገልፀው፣ ዓለም ላይ ያላትን ተፅዕኖና ስትራቴጂክ ጥቅሟን እንደ ጥሩ አጋጣሚ ተጠቅማ ከሌሎች ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነት ላልተገባ ዓላማ እየተጠቀመች ኢትዮጵያ የራሷንና የጋራ የሆነውን ሀብት እንዳትጠቀም ተፅዕኖ የምትፈጥርበት መንገድ የውሸትና ኢ-ፍትሐዊ የሆነ አካሔድ ነው ብለዋል፡፡

ነገር ግን እንደዚህ አይነት የውሸት አካሄዶች ኢትዮጵያ ውስጧን ባረጋጋች ቁጥርና ብሔራዊ አቅሟን ካጠናከረች አይቀጥሉም ባይ ናቸው፡፡ ለዚህም እስከዛሬ ድረስ የናይል ውሃ ከግብፅ እንደሚነሳ፣ ውሃው ህይወታቸው እንደሆነ፣ ኢትዮጵያ አላግባብ እንደምትጠቀምበት የሚያትት የተሳሳተ ትርክት ለዜጎቿ ስትመግብ ኖራለች፤ ዓለምንም ስታታልል ቆይታለች፤ አሁን ታላቁ የህዳሴ ግድብ መገንባት የዐባይ ወንዝ ምንጭ ኢትዮጵያ መሆኑ ገሃድ ወጣ፤ ይህም ግብፅን በእጅጉ እንዳበሳጫትም ገልፀዋል፡፡

ለወደፊቱም ቢሆን ኢትዮጵያ ስራዎችን እየሰራች የግብፅን ውሸትና ኢ-ፍትሐዊ እንቅስቃሴዎችን ለዓለም እያሳየች ትሄዳለች ያሉት አቶ ሽመልስ፣ ለአብነትም በተደጋጋሚ መድረኮች ለተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት የግብፅን ኢ-ፍትሐዊነት ለዓለም እያጋለጠች እና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተ የልማት ጉዞዋን ዓለም በሚገባ ተረድቶ እንዲደግፋት እያደረገች ቀጥላለች፤ ይህም ተጨባጭ ውጤት እያስገኘ ስለመሆኑ ተናግረዋል፡፡

በተመሳሳይ በአምቦ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ሴኔሳ ደምሴ ግብፆች በቅኝ ግዛት ጊዜ የነበረው ስምምነት ላይ መንጠልጠላቸውን አውስተው፣ ይህ ደግሞ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ላይ የሚያስኬድ አይደለም ብለዋል፡፡

አክለውም፣ በህዳሴው ግድብ ላይ የምታራምደው አቋም በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሚያዋጣና ትክክል ያልሆነ ነው ብለዋል፡፡ በመሬት ላይ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበና በዚህ ክፍለ ዘመን ተግባራዊ ሊሆን የማይችል ብቻ ሳይሆን ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶች ሌሎችን ጎረቤት ሀገሮችን በማይጎዳ መልኩ የመጠቀም መብት ኢትዮጵያ እንዳላት ይዘነጋሉ፡፡ ከዚህ አኳያ ዓባይ ያለው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ኢትዮጵያም ሀብቷን ሌሎችን በማይጎዳ መልኩ እንደፈለገች የመጠቀም መብት ስላላት በተግባርም እያደረገች ያለችው ይህንኑ ነው፡፡ ይህም የጋራ ተጠቃሚነት መርህ የሚታይበት ነው የሚል ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

ኢትዮጵያ የምትከተለው መርህ ሌሎችን በማይጎዳ መልኩ መሆኑን የጠቀሱት መምህር ሴኔሳ፣ የህዳሴው ግድብ በየጊዜው በጎርፍ ለሚሰቃዩት ሱዳኖች እፎይታ ፈጥሯል፡፡ አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ ህግ መርሆችንና የነበሩ ልምዶችን ተከትላ ነገሮችን ከማስኬድ ውጪ ማንንም የመጉዳት ዓላማ ኖሯት አያውቅም። የተፈጥሮ ሃብቷን የመጠቀም መብት አላት፤ ከዚህ አኳያ ግብፅ እያደረገች ያለችው ክስ መሰረተ ቢስ በህግም ያልተደገፈና ወቅቱን ያላገናዘበ ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያ የጀመረችውን ጠንካራ የዲፕሎማሲ መንገድ አጠናክራ መቀጠል አለባት ሲሉ መክረዋል፡፡

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ኢትዮጵያ ቀጣይነት ያለው፣ ለቀጣናዊ ልማትና ለጋራ ብልፅግና ያላትን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው። በታሪክ መንገድ ላይ ወደ ኋላ መለስ ብንልም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ኢትዮጵያ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት መመሥረት ቁልፍ ተዋናይ እንደነበረች እንመለከታለን፡፡ አሁንም አፍሪካ ችግሮቿን በውይይት እየፈታችና ያላትን ሀብት በጋራ ተጠቅማ የድህነትን ቀንበር ሰባብራ ወደ ብልፅግና ማማ ከፍ ትል ዘንድ ኢትዮጵያ ሰላማዊ ለሆነ የጋራ ተጠቃሚነት መርህ ቀናኢ ሆና በተምሳሌትነት መቀጠሏንም ገልፀዋል፡፡

የአፍሪካ ቀንድ ሰላማዊና የተረጋጋ ሁኔታ እንዲኖራት ኢትዮጵያ ከትናንት እስከ ዛሬ በደም የተከፈለ መስዋዕትነትም ከፍላለች፡፡ ይህም ለሰላምና ለፍትሐዊነት የቆመች መሆኑን የሚመሰክር ሀቅ ነው። በተለይም እንደ አልሸባብ ያሉ ታጣቂ ቡድኖች እየፈጠሩ ካሉት የፀጥታ ችግሮች እና በአካባቢው እየታየ ካለው አለመረጋጋት አንጻር በሰላም ማስከበርም ሆነ በኢኮኖሚያዊ ትብብር ኢትዮጵያ ለሶማሊያ ብቻ ሳይሆን ለቀጣናው ሀገራትም ሆነ ለአፍሪካ ጉልህ አበርክቶ እያደረገች ያለች ሀገር እንደሆነችም ጠቁመዋል፡፡

# የኮንፈረንስ ... ከገጽ 1 የዞረ

ከተሞች ከ80 በመቶ በላይ የዓለምን ጥቅል ምርት (Global GDP) ያመነጫሉ። በኢትዮጵያ ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርትም ከተሞች 60 በመቶ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ደግሞ ከ50 በመቶ በላይ ድርሻ እንዳላት መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

እንደ አዲስ አበባ ያሉ ከተሞች ኢኮኖሚያዊ አበርክቷቸው እንዲጨምር ደግሞ የቱሪዝም ሴክተሩ ድርሻ ከፍ እያለ ስለመምጣቱ ይጠቀሳል፡፡ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አጽቀሥላሴ በ6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን የጋራ ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር፣ መንግሥት ባለፉት ዓመታት የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ ትኩረት በመስጠት አዝጋሚ የነበረውን ጉዞ ወደ ጉልህ የእድገት አንቀሳቃሽ ሞተር መለወጥ መቻሉን ተናግረዋል።

ከዚህ ቀደም ከተለመዱ ውስን ጉባኤዎች በእጥፍ የላቁ ዓለም አቀፍ ኩነቶችን በስኬት በማስተናገድ ላይ የምትገኘው አዲስ አበባ በርካታ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶችን በማዘጋጀት ላይ እንደምትገኝም የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ይናገራሉ። ከወራት በፊት የሀገራት መሪዎችን፣ የዓለም አቀፍ ተቋማትን፣ የአየር ንብረት ተመራማሪዎችን፣ ዓለም አቀፍ የሚዲያ አካላትን ጨምሮ ከ25 ሺህ በላይ ታዳሚዎች የተሳተፉበት የአየር ንብረት ጉባኤን እዚህ ጋር በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ እንደሚገልጹትም መዲናዋ በ2017 በጀት ዓመት ብቻ 150 ዓለም አቀፍ ኩነቶችን በከፍተኛ ስኬት ያስተናገደች ሲሆን፣ 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ያህል ጎብኚዎችንም አስተናግዳለች። በዚህም 143 ቢሊዮን ብር ያህል ሀብት ወደ ከተማዋ ኢኮኖሚ ፈሰስ ሆኗል።

ይህ ቁጥር ከአብዛኞቹ የአፍሪካ ሀገራት ዓመታዊ የኮንፈረንስ አዘጋጅነት እጅግ የላቀ ሲሆን፣ በመዲናዋ እንደ አዲስ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከል እውን መሆን ለኮንፈረንስ ቱሪዝም መበራከት ወሳኝ ሚና ተጫውቷል። የዓድዋ ድል መታሰቢያ ግንባታ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ማበርከታቸውም ይገለጻል። ለመሆኑ እንደዚህ አይነት ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን ማስተናገድ ለመዲናዋ ያለው ትርጉም ምንድነው? የሴክተሩ የእሳካሁን እንቅስቀሴዎች ምን ይመስላሉ? የኮንፈረንስ ቱሪዝሙን ዕድሎች እንዴት መጠቀም ይገባል? የሚሉና መሰል ጉዳዮችን መፈተሽ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከአምስት ዓመት በፊት ይፋ ባደረገው መረጃ በዓለም አቀፍ ደረጃ የቱሪዝም ኢንዱስትሪው በቀን ከ3 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ይገኝበታል ይላል፡፡ በተለይም ሴክተሩ በጊዜ ሂደት የወለደውና አዲስ ጽንሰ ሀሳብ የሆነው በምህፃረ ቃል ማይስ (Meeting Incentives & Conference Exhibition) ተብሎ የሚታወቀው ዘርፍ ላይ ሀገራት አተኩረው በመስራት የውጭ ምንዛሪ ገቢያቸውን እያሳደጉበት ስለመሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ኮንፈረንስ ቱሪዝም ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከሚኖረው ቀጥተኛ ፋይዳ በተጨማሪ ኢትዮጵያን ለዓለም በማስተዋወቅ ረገድ ትልቅ ሚና እየተጫወተ እንደሚገኝ የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ፡፡ የቱሪዝም ባለሙያው አቶ እንቁ ሙሉጌታ እንደሚሉትም ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ለቱሪዝም ዘርፍ የተሰጠው ትኩረት እጅግ አመርቂ ነው፡፡ የከተማዋን ገጽታ ማሻሻልና መዝናኛ ቦታዎች የሆኑት እንደ ሸገር ፓርክ፣ አንድነት ፓርክ፣ እንጦጦ ፓርክ እና ወዳጅነት አደባባይ ያሉት ቦታዎች ለእንግዶች የመዝናኛና የመሰብሰቢያ ቦታ በመሆን ለጉባኤው ምቹ ሁኔታ ፈጥረዋል። የእነዚህን ቦታዎች ውበትና አገልግሎት ማሳደግ ተጨማሪ ወጪ እንዲያወጡ ያበረታታል ሲሉም ይገልጻሉ።



ፎቶ- ከገፀ ድር
ጉባኤዎችን በተሳካ ደረጃ ለማሰናዳት አቅም ከሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ ሀብቶች መካከል ጥቂቶቹ

አዲስ አበባ የኮንፈረንስ ቱሪዝም የስበት ማዕከል እየሆነች ስለመምጣቷ የምጣኔ ሀብት መምህር ጉቱ ቴሶ (ዶ/ር) በበኩላቸው ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችንና ዝግጅቶችን የሚያስተናግድ ሀገር፣ በዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲና ኢኮኖሚ መድረክ ተሰሚነቱ ይጨምራል ይላሉ። አያይዘውም የኢንዱስትሪ፣ የቴክኖሎጂ፣ የምርትና የአገልግሎቶች ዓለም አቀፍ ኤግዚቢሽን ሲዘጋጅ፣ የዕውቀት ሽግግርን ያቀላጥፋል። የኢንቨስትመንትና የቢዝነስ አማራጮችን ይከፍታል። የንግድና የገበያ ግንኙነቶችን ለመፍጠር፣ ውል ለመፈራረም፣ ሽያጭና ግዢ ለመጀመር መልካም አጋጣሚዎችን ይፈጥራል ብለዋል።

የኮንፈረንስ ቱሪዝም በተጨባጭ ይዞት የመጣውን ዕደል ጨምረው ሲያብራሩም የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች፣ የእደ ጥበብ ባለሙያዎች እና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከኮንፈረንስ ቱሪዝም ዘርፍ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይናገራሉ።

አዲስ አበባ ከዚህ በፊትም የተለያዩ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን በተደጋጋሚ አስተናግዳለች። ከእነዚህ ልምዶች መረዳት እንደሚቻለው፣ በጉባኤ ወቅት የሚስተናገዱ እንግዶች ለሆቴሎች የገንዘብ ፍሰት ከመፍጠራቸው በተጨማሪ፣ ዘላቂ የንግድ ግንኙነቶች እንዲመሰረቱ ያግዛሉ። በርካታ ሆቴሎች በጉባኤው ላይ ከሚሳተፉ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ኩባንያዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ለወደፊትም እንግዶችን የማግኘት ዕድላቸውን ያሰፋሉ።

ዓለም አቀፋዊ ከሆኑ ስብሰባዎች ጋር ተጣምሮ የሚካሄደው በዚህ የቱሪዝም ዘርፍ በአፍሪካ እንደ ደቡብ አፍሪካ፣ ኬኒያ፣ ሩዋንዳ ያሉ ሀገራት ቀዳሚ ተጠቃሚ ናቸው፡፡ ከሁለት ዓመት በፊት በወጣው መረጃ በሩዋንዳ የስብሰባ፣ ኮንፈረንሶች እና ዝግጅቶች ዘርፍ (MICE) አስደናቂ እድገት ያስመዘገበ ሲሆን፣ ከ150 በላይ ጉባኤዎችን ባስተናገደችበት በዚሁ ዓመት ብቻ ከ91 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ገቢ አግኝታለች ይላል ከሀገሪቱ ቱሪዝም መስሪያ ቤት የተገኘው መረጃ።

ዘርፉ በደንብ ሊሰራባቸው ይገባል ባሏቸው ጉዳዮች ዙሪያ ሀሳባቸውን ያጋሩት ባለሙያዎቹ እንደሚሉት በተለይም ደረጃቸውን የጠበቁ የኮንፈረንስ ማዕከላትን ቁጥር መጨመር፣ የግል ባለሃብቱ በዘርፉ ያለውን ተሳትፎ ማሳደግን እንዲሁም በዘርፉ ያለውን የሰለጠነ የሠው ኃይል እጥረት መቅረፍ ይገባል፡፡ ጨምረውም ጎብኚዎች አስፈላጊ መረጃዎችን ማግኘት የሚችሉበትን ዘመናዊ ስርዓት መዘርጋት እንደሚገባም ያሳስባሉ፡፡

አዲስ አበባ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በቴክኖሎጂ የላቁ እና ለትላልቅ ስብሰባዎች በቂ አቅም ያላቸው አዳራሾችና የሆቴል አገልግሎቶች ሊኖራት ይገባል። ይህ ከተማዋን በዓለም አቀፍ ደረጃ የኮንፈረንስ ማዕከል ያደርጋታል። ከአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ጋር የተሻለ ግንኙነት ያለው ዘመናዊ የትራንስፖርት ሥርዓት መዘርጋት (ታክሲ፣ አውቶቡስ፣ የባቡር መስመር) ያስፈልጋል። እንግዶች በከተማዋ ውስጥ በቀላሉና በፍጥነት እንዲንቀሳቀሱ ምቹ ሁኔታ መፍጠር የግድ ነው።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማዋ ቱሪዝምን ለማሳደግ፣ የለሙ አዳዲስ የቱሪዝም መዳረሻዎችን ለማስተዋወቅ፣ በዚህም "የእግረ-መንገድ ቱሪዝም" (Stopover Tourism) ተጠቃሚነትን ማሳደግ፣ የከተማዋን አዲስ መለያ የሆነውን "new face of Africa"ን ማስተዋወቅን ያካተተ ስምምነት ማድረጋቸው የሚታወስ ነው፡፡

የተለያዩ የገቢ ማሳደጊያ ስትራቴጂዎችን ተጠቅሞ ለኮንፈረንስ ወደ መዲናዋ የሚመጣውን እንግዳ ሀብት በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባ የሚመክሩት አቶ እንቁ ሙሉጌታም፣ ጉባኤው ለሚካሄድባቸው ጥቂት ቀናት ብቻ ሳይሆን ከዚያ በፊት እና በኋላም ገቢን ለማስገኘት መስራት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

አክለውም፣ የቱሪዝም እና የጉብኝት ፓኬጆችን በማዘጋጀት የጉባኤው ተሳታፊዎች ሌሎች የሀገሪቱን የቱሪዝም መዳረሻዎች እንዲጎበኙ ማበረታቻና ማራኪ ጥቅሎችን ማዘጋጀት ይገባል ይላሉ።

በእርግጥም የአዲስ አበባ ከተማ ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ አዲስ አበባ የተለያዩ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች የሚገኙባት ከተማ ናት፡፡ በከተማዋ ካሉ 13 ፓርኮች በተጨማሪ ታሪካዊ ሐውልቶች፣ ሙዚየሞች፣ አደባባዮች፣ ድልድዮች፣ ጥንታዊ ቤቶች፣ አብያተ ክርስቲያናትና መስጊዶችን ጨምሮ 157 ታሪካዊ ቅርሶች በቱሪዝም መስህብነት ተመዝግበው ይገኛሉ፡፡ ኃይማኖታዊ በዓሎች፣ ጋለሪዎች፣ የገበያ ቦታዎች፣ የዕደ ጥበብ ውጤቶችና የባህል ምሽት ቤቶችም ይገኙበታል፡፡

በጉባኤ ማዕከላት አቅራቢያ የእደ ጥበብ፣ የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ የቡና እና የባህል ልብሶች መሸጫ ሱቆች እና ኤግዚቢሽኖች ማደራጀት፣ እንግዶች ለራሳቸውም ሆነ ለቤተሰቦቻቸው ስጦታ እንዲገዙ ማበረታታት፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ከትላልቅ ሆቴሎች እና የኮንፈረንስ አዘጋጆች ጋር የንግድ ግንኙነት እንዲፈጥሩ የሚያስችል መድረኮችን ማመቻቸት እንደሚያስፈልግም የዘርፉ ምሁራን መክረዋል፡፡

እንግዶች በዲጂታል መንገድ ክፍያ እንዲፈጽሙ የሚያስችሉ ሥርዓቶች መዘርጋት (ዓለም አቀፍ የክሬዲት ካርዶችን መቀበል፣ የሞባይል ክፍያ ሥርዓት) በአንድ ቦታ ሁሉንም የቱሪዝም መረጃ እና አገልግሎት (ኢ-ቪዛ፣ የጉብኝት ቦታዎች፣ የሆቴል መያዣ) የሚያገኙበት የሞባይል መተግበሪያ ማዘጋጀት እንደሚገባም አክለው ባለሙያዎቹ መክረዋል።

የ'The growth of Meetings, incentive, conferences and exhibition industry in Africa' ጥናታዊ ጽሑፍ አዘጋጁ ክዋኪ ዶንኮርም እንደሚገልፁት ኮንፈረንስ ቱሪዝም የሚሰጠው ጥቅም የቱሪዝም ገቢ ብቻ አይደለም። የጉባኤውን መድረክ በመጠቀም የኢንቨስትመንት ዕድሎችን ለውጭ ባለሀብቶች ለማስተዋወቅ ያስችላል። እንደ ግብርና፣ ማምረቻ፣ ማዕድን እና አይ.ሲ.ቲ ባሉ ዘርፎች የሚገኙ የልማት ፕሮጀክቶችን ለውጪ ባለሀብቶች ለማስተዋወቅም የሚፈጥረው ዕድል ከፍተኛ ስለመሆኑ ያብራራሉ።

ከዚህ አንጻር ጉባኤዎቹ የዓለም አቀፍ ባለሙያዎችን እና ምሁራንን ወደ አዲስ አበባ ስለሚያመጡ፣ የሀገር ውስጥ ምሁራንና የንግዱ ማህበረሰብ ከአዳዲስ እውቀቶች፣ ቴክኖሎጂዎች እና የተሻሉ አሠራሮች እንዲማሩ ዕድል ይፈጥራል። በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚሰሩ ሰዎች የዓለም አቀፍ አገልግሎት ደረጃዎችን እንዲያሟሉ ስልጠናና ድጋፍ መስጠት ሌላኛው የዘርፉ በረከት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

መረጃዎች እንደሚያሳዩት እ.ኤ.አ በ2024 የዓለም አቀፍ የማይስ ኢንዱስትሪ ገቢ ከ1 ነጥብ 1 ትሪሊዮን ዶላር በላይ እንደነበር ይገመታል። ይህ ገቢ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሲሆን፣ እስከ 2032 ድረስም ወደ 2 ነጥብ 4 ትሪሊዮን ዶላር ሊደርስ እንደሚችል ይገመታል፡፡ እንደ ባንኮክ፣ ዱባይ፣ ኒውዮርክ እና ከአፍሪካም እንደ ጆሃንስበርግ እና ናይሮቢ ያሉ ከተሞች ከኮንፈረንስ ቱሪዝም እና ተያያዥ ከሆኑት የአገልግሎት ዘርፎች ተጠቃሚ ከተሞች ናቸው፡፡

# ምክር ቤቱ በውሎው

- የመኖሪያ ቤት ችግርን ማቃለል ዋና የበጀት ዓመቱ ትኩረት መሆኑን ጠቁሟል
- በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ለ96 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩ ተጠቅሷል
- አዲስ ሹመትም ሰጥቷል

**በደረጀ ታደሰ**

በተጠናቀቀው የ2017 በጀት ዓመት እና ከዚያ በፊት በነበሩት ጥቂት ዓመታት አዲስ አበባ በምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉ በርካታ ሥራዎችን አከናውናለች፡፡ ሥራዋ ከራሷ አልፎ ለሌሎች ከተሞች መነቃቃትን መፍጠር ችሏል፡፡ ከኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት፣ ከሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ከቱሪዝም ኮንፈረንስ ማዕከልነት ጋር በተያያዘ የተከናወኑ ስኬታማ ተግባራት ውጤታቸው መታየት ከጀመረ ውሎ አድሯል፡፡

እንደ ትምህርት እና ጤና ባሉ የማህበራዊ ዘርፎችም የአዲስ አበባ ስኬት በጉልህ የሚታይ ነው፡፡ የዓለም አቀፍ ዕውቅናን ማስገኘት የቻለው የተማሪ ምገባ መርሃ ግብር እንዲሁም "የትምህርት ለትውልድ" ንቅናቄ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ትልቅ አስተዋፅኦ ማድረጉን ቀጥሏል፡፡ በሽታን ከመከላከል ባለፈ አክሞ ማዳን ላይ ያተኮረው ሀገር አቀፍ የጤና ፖሊሲ እንደ አዲስ አበባ መሬት የነካ ሥራ ተሠርቷል፤ እየተሠራም ይገኛል፡፡

የልማት እንቅስቃሴው ህፃናት፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያን እንዲሁም የሀገር ባለውለታዎችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ በብዛት እና በጥራት ተከናውነዋል፡፡ ተጋላጭ የሆኑ ሴቶች በነገዋ የማገገሚያ እና የክህሎት ማዕከል በማሰልጠን ተሳትፏቸው እንዲጨምር ተደርጓል፡፡ እነዚህና መሰል በመዲናዋ የተከናወኑ ተግባራት በሀገር አቀፍ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ በጉልህ የሚጠቀስ ውጤት የተመዘገባቸው ስለመሆናቸው፤ የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት ታዬ አፅቀሥላሴ መስከረም 26 ቀን 2018 ዓ.ም. ለሁለቱ ምክር ቤቶች ባቀረቡት ንግግር ላይ ያነሷቸውን ነጥቦች ማስታወስ ይገባል፡፡

ባለፉት ዓመታት የታዩ ስኬቶችን የሚያስቀጥሉ፣ ጉድለትን የሚሞሉ፣ አዳዲስ እይታን ያካተቱ፣ ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ተግባራትን በተያዘው የ2018 በጀት ዓመት ለማከናወን እንደከተማ ታቅዶ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ ዕቅዶቹ ወደ ተግባር መለወጥ ከጀመሩ አንድ ሩብ ዓመት (ሦስት ወራትን) አስቆጥረዋል። በዚህ ጊዜ ውስጥ የከተማዋ የዕቅድ አፈጻጸም ውጤት ምን እንደሚመስል፤ ጥቅምት 3 ቀን 2018 ዓ.ም. በ3ኛው የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የስራ ዘመን 1ኛ መደበኛ ጉባኤ ላይ ተገምግሟል፡፡ ከምክር ቤት አባላት ለተነሱ ጥያቄዎች፤ በከተማዋ ከንቲባ አዳነች አቤቤ እና በሌሎች የከተማዋ ከፍተኛ አመራሮች ምላሽ እና ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡

ከምክር ቤት አባላት ከተነሱ ጥያቄዎች መካከል፤ "የኮሪደር ልማቱ ውጤታማነትን ነዋሪው እንደወደደው በመጥቀስ፤ ልማቱ ያልደረሰባቸው አካባቢዎች ለማዳረስ የከተማ አስተዳደሩ ምን አቅዷል?" የሚለው ይጠቀሳል፡፡ ለዚህ ጥያቄ ከንቲባ



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ አዳነች አቤቤ ከምክር ቤት አባላት ለተነሳላቸው ጥያቄ ምላሽና ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት

> **በመዲናዋ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ቤቶች ግንባታ መጀመሩ ተጠቁሟል። በበጀት ዓመቱ የሕዝብ ጥያቄ ያለባቸውን መንገዶች የትራፊክ ስታንዳርድን በጠበቀ መልኩ ለማስተካከል ዕቅድ መያዙ ተነስቷል**

አዳነች አቤቤ በሰጡት ምላሽ፤ የልማቱ ፍላጎት ስለመኖሩ በመጥቀስ ሥራው ዕቅድ፣ ከፍተኛ በጀት እና ሌሎች ተያያዥ ነገሮችን የሚጠይቅ በመሆኑ በተያዘው የ2018 በጀት ዓመት የኮሪደር ልማት ተብሎ እንደ አዲስ የሚጀመር ሥራ እንደማይኖር ተናግረዋል፡፡

የከተማ አስተዳደሩ፤ የ2018 በጀት ዓመት ትልቁ ትኩረት የቤት ግንባታ እና የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት እንደሆነ በምክር ቤቱ ተገልጿል፡፡ በመዲናዋ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ቤቶች ግንባታ መጀመሩ ተጠቁሟል፡፡ በበጀት ዓመቱ የሕዝብ ጥያቄ ያለባቸውን መንገዶች የትራፊክ ስታንዳርድን በጠበቀ መልኩ ለማስተካከል ዕቅድ መያዙም ተነስቷል፡፡ ይህ ዕቅድ ተፈፃሚ ሲሆን፤ በኮሪደር ልማቱ የተተገበረውን አካታችነት (የእግረኛ፣ የብስክሌት እና የተሽከርካሪ መንገዶችን) ያሟላ እንደሚሆን ተመላክቷል፡፡ በዕቅድ ከተያዙት የመንገድ መሰረተ ልማት ግንባታዎች መካከል፡- ከኡራኤል ወደ ቦሌ ቪአይፒ የሚያገናኘው መንገድ አንዱ ሲሆን፤ በግንባታ ላይ ይገኛል፡፡

የመረጣቸውን ሕዝብ በማወያየት በመራጮቻቸው የተነሱ ጥያቄዎችን ይዘው በምክር ቤቱ የተገኙ የሕዝብ ተወካዮች ካነሷቸው ጥያቄዎች መካከል ከሥራ ዕድል ፈጠራ ጋር የተያያዘው ይገኝበታል፡፡ "ስልጠና ወስደው የተደራጁ ዜጎችን ወደ ሥራ ከማስገባት፣ የመሥሪያ ቦታ አቅርቦት እና የገበያ ትስስር መፍጠር ላይ ምን እየተሠራ ነው?" በሚል ለተነሳው የምክር ቤት አባላት ጥያቄ በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የሥራና ክህሎት ቢሮ ኃላፊው አቶ ጥራቱ በየነ ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

እንደ አቶ ጥራቱ ማብራሪያ ከሆነ፤ በ2018 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ለ77 ሺ 500 ለሚሆኑ ወጣቶች እና ሴቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ፤ ከ96 ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል። የክህሎት ስልጠና ወስደው የተደራጁ ወጣቶች ወደ ሥራ እየተሰማሩ ነው፤ ይህም ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በ2017 በጀት ዓመት ላይ ተደራጅተው ወደ ሥራ ያልገቡ 1 ሺህ 440 ሥራ ፈላጊዎች መኖራቸውን በበጀት ዓመቱ ማጠናቀቂያ ላይ በማረጋገጥ፤ በዘጠና ዕቅድ ውስጥ በማካተት የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ ሥልጠናውም ሆነ የሥራ ስምሪቱ በመረጃ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ስልጠና የወሰደ እና የተደራጀ እያንዳንዱ ሥራ ፈላጊ የሥራ ዕድል ይፈጠርለታል። አምራቾችን በተለያዩ ኤግዚብሽኖች እና ሁነቶች እንዲሳተፉ በማድረግ ሁለት ቢሊዮን ብር የሚገመት የገበያ ትስስር ተፈጥሯል፡፡ ጥራት ያለውን እና ዓለም አቀፍ ስታንዳርዱን ያሟሉ ምርቶች የሚያመርቱ አምራቾች ወደውጭ ሀገራትም የሚሸጡበት የገበያ ትስስር ለመፍጠር እየተሠራ ነው። ከመሥሪያ ቦታ ጋር በተያያዘ ባለፉት ሦስት ወራት 996 የመሥሪያ ቦታዎች ለአዳዲስ ሥራ ፈጣሪዎች ተሸጋግሯል፡፡ እንደከተማ አስተዳደር በ2018 በጀት ዓመት በአጠቃላይ ለ350 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ እየተሠራ ነው፡፡

በኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ በተደገፈ አግባብ አገልግሎትን ከማዘመን አንፃር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እየተሠሩ ስላሉ ሥራዎች ከንቲባ አዳነች አቤቤ ለምክር ቤቱ አባላት በሰጡት ማብራሪያ እንደጠቆሙት፤ በከተማ ደረጃ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ፈጣን፣ ቀልጣፋና ምቹ በሆነ አግባብ ለተገልጋዩ ተደራሽ የማድረግ ዓላማ ያለው የመሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት በማዕከል እና በቅርንጫፍ ደረጃ ተጀምሯል፡፡ በዚህም በማዕከል 107 እንዲሁም በቦሌ ቅርንጫፍ ደግሞ 96 በድምሩ 2013 አገልግሎቶች ዲጂታላይዝድ ሆነው በኦንላይን እየተሰጡ ይገኛሉ፡፡ በእነዚህ ማዕከላት የተመደቡ ባለሙያዎች 70 በመቶ አዲስ ምሩቅ ሲሆኑ፤ ወደ ሥራው ከመግባታቸው በፊት ተገቢውን ስልጠና ወስደዋል፡፡ ከነባር ሠራተኞች ጋር ተዋህደው እንዲሠሩ በቂ ዝግጅት ተደርጓል፡፡

የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ተደራሽነት ዛሬም የአዲስ አበባ ችግር መሆኑን በማንሳት ለዚህ መፍትሄ ምን እየተሠራ እንደሆነ ማብራሪያ የሚሻ ጥያቄ ከምክር ቤት አባላት ተነስቷል፡፡ ለዚህ ጥያቄም ከንቲባ አዳነች አበቤ በሰጡት ምላሽ እንዳስረዱት፤ ከውሃ አቅርቦት ጋር በተያያዘ ከፍተኛ በጀት በመመደብ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል፤ እየተሠሩም ይገኛሉ፡፡ በ2017 በጀት ዓመት ብቻ በቀን 62 ሺህ ሜትር ኪብ ተጨማሪ የንፁህ መጠጥ ውሃ ማቅረብ ተችሏል፡፡ በግንባታ ሂደት ላይ ያሉት የጭቋላ እና የገርቢ የውሃ ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ ተጨማሪ በቀን 173 ሺህ የንፁህ መጠጥ ውሃ ማቅረብ ያስችላሉ፡፡ ይህም የከተማዋን የውሃ አቅርቦት ችግር የማቃለል አቅም ይኖረዋል፡፡

የመዲናዋን የጤና አገልግሎት የጥራት ደረጃ ከፍ ለማድረግ በትኩረት እየተሠራ ስለመሆኑ ከንቲባ አዳነች አስረድተዋል፡፡ እንደሳቸው ገለጻ፤ በዓለም የጤና ድርጅት መስፈርት መሰረት አዲስ አበባ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን አሟልታለች፡፡ ይህም ሆኖ የጤና ተደራሽነትን ከዚህም በላይ ከፍ ለማድረግ የሕዝብን ጥያቄ ባማከለ መልኩ ምላሽ እየተሰጠ ይገኛል። በ2017 በጀት ዓመት 9 ጤና ጣቢያዎች ተጠናቀው ለአገልግሎት በቅተዋል፡፡ እነዚህ ጤና ጣቢያዎች ከመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል አገልግሎት ጋር ተመሳሳይ የሆነ አገልግሎቶችን መስጠት የሚያስችሉ ናቸው፡፡ በተመሳሳይ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት 13 ሆስፒታሎች ታድሰዋል። የምኒልክ እና የዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታሎችን ጨምሮ በ4 ሆስፒታሎች የማስፋፊያ እና ዕድሳት ሥራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

በክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት እንደከተማ ትልቅ ሥራ መከናወኑ በምክር ቤቱ ተነስቷል፡፡ ከቤት ግንባታ ጋር በተያያዘ ባሳለፍነው የክረምት ወራት የተሠሩ ሥራዎች በማሳያነት የቀረቡ ሲሆን፤ በእነዚህ ጊዜያት 2 ሺህ 300 ቤቶችን ለመገንባት ታቅዶ፤ ከ3 ሺህ 1 መቶ በላይ ግንባታ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# ቴክኖሎጂው በገቢ አሰባሰብ ላይ ምን ልዩነት አመጣ?

- **ቴክኖሎጂን በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ለተሻለ ኢኮኖሚያዊ እድገት መነቃቃት እድል ፈጥሯል**

**በሄለን ጥላሁን**

ዜጎች በመነገድ፣ ቤትና ንብረት በማከራየት፣ ዕውቀታቸውን በመሸጥ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ከሚያገኙት ገቢ ላይ በህግ በተቀመጠው አግባብ ግብር መክፈል ይጠበቅባቸዋል። በሕግና በአሠራር በተቀመጠው መሰረት ግብር መክፈል የሚጠበቅባቸው ግብር ከፋዮች ለመንግስት የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡ ግብር ሰብሳቢው መንግስት ደግሞ የሰበሰበውን የግብር ገቢ ለሀገር ልማትና ዕድገት እንዲሁም ለህብረተሰቡ ተጠቃሚነት የሚያገለግሉ መሰረተ ልማቶችን ይገነባል፤ በፍትሃዊነትም ያዳርሳል፡፡ ፈጣንና ቀልጣፋ የመንግስት አገልግሎትን ያቀርባል፡፡ ትምህርትና ጤናን በጥራት እና በስፋት ያዳርሳል፡፡ የሀገር ሠላምና ሉዓላዊነት ያስከብራል፡፡ ሌሎችንም ሀገራዊ ሥራዎችን ይፈፅማል፤ ያስፈፅማል፡፡

የግብር ሰብሳቢ ተቋማት ከግብር አሰባሰብ ጋር በተያያዘ ድርብ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ አንደኛው ከግብር ከፋዮች ተገቢውን ግብር በወቅቱ የመሰብሰብ ኃላፊነት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ለግብር ከፋዮች ፈጣንና ቀልጣፋ የሆነ አገልግሎት መስጠት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ እየተሠራ ያለውን ሥራ ለመቃኘት እንሞክራለን፡፡

አቶ አብዱላዚዝ ከሊፋ፤ በአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ የኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ ዳይሬክተር ናቸው፡፡ እሳቸው እንደሚያስረዱት፤ ቢሮው የግብር(ታክስ) ገቢ አሰባሰብ ስርዓቱን ለማዘመን በቴክኖሎጂ የታገዘ አሠራርን እየተገበረ ነው፡፡ ለደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉበት በቴክኖሎጂ የተደገፈ (ኢ-ታክስ) ስርዓት፣ የገቢ አሰባሰብ መረጃ መላላኪያ ቴክኖሎጂ (ኢ- ረቨኑ ፕላን) ስርዓት፣ የነጻ ስልክ መስመር 7075፣ የእዳ ክትትል ስርዓት (ኢ- ፔይመንት እና ኢ- ፊሊንግ) ቴክኖሎጂዎች በአገልግሎት ላይ ውለው እየተሠራባቸው ነው፡፡

በተጨማሪም፤ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች የግብር ውሳኔ በ7075 አማካይነት በአጭር የጽሑፍ መልዕክት በስልካቸው እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡ እነሱም በደረሳቸው አጭር የጽሑፍ መልዕክት መሰረት ባሉበት ሆነው ቴሌ ብር፣ ሲ ቢ ኢ ብር፣ ሞባይል ባንኪንግ በመሳሰሉት ዘመናዊ የክፍያ አማራጮች የሚከፍሉበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡

አቶ አብዱላዚዝ አያይዘውም፤ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥን ለመከታተል፣ ለመደገፍ እና ለማሻሻል እንዲቻል ከማዕከል ሆኖ እያንዳንዱን መረጃ በፍጥነትና በጥራት የሚያደርስ የሰርቪላንስ ካሜራ ለአገልግሎት በቅቷል፡፡ ተቋሙ የመደባቸው የቁጥጥር ሠራተኞች ተገቢውን አገልግሎት በሕጋዊና አሠራሩን በጠበቀ መልኩ እንዲሰጡ፣ ግብር ከፋዩ ማህበረሰብም እንዳይጭበረበር እና ላልተገባ ጉዳት እንዳይዳረግ ለእነዚህ የቁጥጥር ሠራተኞች ማንነታቸውን በቀላሉ ለማወቅ የሚያስችል ባር ኮድ የተካተተበት መታወቂያ ተዘጋጅቷል፡፡ እንዲሁም በሂደት ላይ የሚገኙ የቀጥታ ቪዲዮ፣ የድምፅ ማስተላለፍ እና አካባቢን መከታተል ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ ማደረግ መቻላቸው በግብር አሰባሰብ ሂደቱ ላይ ትልቅ አሻራ ስለማኖራቸው ገልፀዋል፡፡

ዓለም አቀፍ የገቢ ግብር እና ልማት ማዕከል (International center for tax and development) የተሰኘው ተቋም በ2020 እ.ኤ.አ ባወጣው መረጃ መሰረት የግብር ከፋይ ቁጥር መጨመር የሀገር ጠቅላላ ገቢን እንደሚያሳድግ ጠቁሟል። ከግብር ከፋዩ ዜጋ የሚሰበሰበው ገንዘብ ለጤና፣ ለትምህርት መስፋፋት እንዲሁም ፍትሃዊ የአኗኗር ዘይቤ እንዲኖር ያግዛል። ይህ መረጃ እንደሚያመላክተው ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ማግስት የግብር አከፋፈል ስርዓትን በአግባቡ ለመተግበር የሚያስችለውን መመሪያ በአስገዳጅ የህግ ማዕቀፍ በማካተት ተግባራዊ ያደረጉት ምዕራባውያኑ አሁን ላይ ለሚታየው ዕድገትና ብልፅግናቸው ቁልፍ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ ዜጎቻቸውም ለምን ግብር እንደሚከፍሉ ጥልቅ ግንዛቤ በመያዝ ያለማንም ቀስቃሽና ጎትጓች በወቅቱ ገቢ የሚያደርጉበትን ዕድል ፈጥሮላቸዋል፡፡

ሀገራት ከግብር የሚሰበሰበውን ገቢ በአግባቡ ለመሰብሰብ እንዲሁም ጥቅም ላይ እንዲውል ለማስቻል የተለያዩ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በማልማት ጥቅም ላይ አውለዋል፡፡ ከዚህ አንፃር በአፍሪካ እንደ ኬንያ፣ ግብፅ፣ ቱኒዚያ እና ደቡብ አፍሪካ የመሳሰሉት ሀገራት ውጤታማ እንቅስቃሴ እያደረጉ ስለመሆናቸው፤ "እ.ኤ.አ በ2025 የተሻለ ሀገራዊ ገቢ ያገኙ 10 የአፍሪካ ሀገራት" በሚል ርዕስ ኤክስፖርት ፎክስ አፍሪካ የተሰኘው ድርጅት ይፋ ያደረገው መረጃ ይጠቁማል፡፡ በመረጃው ላይ እንዳሰፈረው በተለይ ጎረቤት ሀገራት ጠንካራ የኢኮኖሚ መሰረታቸውን የጣሉት ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በግብር አሰባሰቡ ሂደት ላይ ተግባራዊ ማድረግ በመቻላቸው እንደሆነም ተጠቅሷል፡፡




ፎቶ- ከገፀ ድር

በ2017 በገቢዎች ቢሮ የተሰበሰበ ገቢ አፈፃፀም የሚያሳይ ቻርት

ሀገረ ኬንያ ካላት የሕዝብ ቁጥር አንፃር አብዛኛውን ማህበረሰብ ተደራሽ ለማድረግ አይ - ታክስ ስርዓትን ተግባራዊ አድርጋ እየሠራች ትገኛለች፡፡ የአሰራር ስርዓቱ ሙሉ ለሙሉ ትኩረቱን የሚያደርገው በኦንላይን የግብር ከፋዮች ምዝገባ ከማካሄድ አንስቶ የግብር አሰባሰብ ሂደቱን ከወረቀት ንክኪ ነፃ በማድረግ ፤ ለብልሹ አሰራር እንደ ምክንያት የሆኑትን አካሄዶች መዝጋት ላይ ትኩረቱን ያደረገ ነው፡፡ ክፍያዎችንም በእጅ በሚገኙ ስልኮችና ላፕቶፖች አማካኝነት ይፈፅማሉ፡፡

በመዲናችን አዲስ አበባም የገቢ ግብር አሰባሰብ ሂደቱን የተሻለ ለማድረግ በተሠራው ሥራ ተጨባጭ ውጤቶችን ለማስመዝገብ ስለመቻሉ አቶ አብዱላዚዝ አስረድተዋል፡፡ በተለይ ከገቢ ግብር አሰባሰብ ሂደቱ ጋር ከ2010 በጀት ዓመት ጀምሮ በነበሩት የለውጥ ዓመታት የገቢ ዕድገቱ ትልቅ እምርታዊ ለውጥ ለማስመዝገብ መቻሉን ጠቅሰዋል። ለማሳያነትም በ2010 ዓ.ም 33 ነጥብ 4 ቢሊየን ብር ተሰብስቦ የነበረ ሲሆን፤ በ2017 በጀት ዓመት እንደ ቢሮ ከ163 ቢሊየን ብር እንደ ከተማ ደግሞ 233 ቢሊየን ብር መሰብሰቡን አስረድተዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ በ2017 በጀት ዓመት 163 ቢሊዮን ብር ገቢ ሰብስቧል፡፡ ይህ ገቢ ከዓመቱ ዕቅድ አንፃር ብልጫ ያለው ሲሆን፤ አፈፃፀሙ 103 ከመቶ በመሆን ተመዝግቧል፡፡ ከቢሮው ያገኘነው መረጃ እንደሚያመላክተው ባሳለፍነው በጀት ዓመት በየሩብ ዓመቱ የነበረው አፈፃፀም ዕድገት ያሳየ ነበር፡፡ እንደመረጃው ከሆነ በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ቢሮው የሰበሰበው ገቢ መጠን 35 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ነበር። በሁለተኛው ሩብ ዓመት ደግሞ የተረሰበሰበው ገቢ መጠን 76 ቢሊዮን ብር ደርሷል። በሦስተኛው ሩብ ዓመት ወይም በበጀት ዓመቱ ዘጠነኛ ወር ላይ ቢሮው የሰበሰበው ገቢ መጠን 125 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር ደርሷል፡፡ ቢሮው ገቢ የማሰባሰብ ሥራውን በማጠናከር በበጀት

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

## ምን ልርዳዎ?

### በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወደ አዲስ መሶብ ለማስገባት የተለዩ አገልግሎቶች መካከል

**ገቢዎች ቢሮ**

1. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ምዝገባ፣
2. የኢ-ፋይሊንግ ዩዘር ኔምና ፓስወርድ መክፈት፣

**ንግድ ቢሮ የተጣመሩ አገልግሎቶች**

1. አዲስ የንግድ ምዝገባ እና አዲስ የንግድ ሥራ ፈቃድ፣ (በአንድ ላይ)
2. አዲስ የንግድ ምዝገባ፣ አዲስ የንግድ ሥራ ፈቃድ እና የንግድ ስም ምዝገባ (ሦስቱን በአንድ ላይ)

**የንግድ ምዝገባ**

3. አዲስ የንግድ ምዝገባ፣
4. የንግድ ምዝገባ ማሻሻያ፣
5. የንግድ ምዝገባ ምትክ፣
6. የንግድ ምዝገባ ስረዛ፣

**የንግድ ሥራ ፈቃድ**

7. አዲስ የንግድ ሥራ ፈቃድ፣
8. የንግድ ሥራ ፈቃድ ማሻሻያ፣
9. የንግድ ሥራ ፈቃድ እድሳት፣
10. የንግድ ሥራ ፈቃድ ምትክ፣
11. የንግድ ሥራ ፈቃድ ስረዛ፣

**የንግድ ስም**

12. የንግድ ስም ምዝገባ፣
13. የንግድ ስም ማሻሻያ፣
14. የንግድ ስም ምትክ፣
15. የንግድ ስም ስረዛ፣

**የድርጅት ስም**

16. የድርጅት ስም ማጣራት፣

**የመረጃ ምንጭ፡-** የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# የወንዝ እና የወንዝ ዳርቻ ጥበቃ ደንብ አበይት ነጥቦች

ዮናታን አብደላ (ዐቃቤ ህግ)

## መግቢያ

ኢትዮጵያ አሁን ላይ በሰፊው በገጽታ ግንባታ እና የከተማ ውበት ስራዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል እየተሰሩ ይገኛል። ለዚህም ሁነኛ ማሳያ እና ተጠቃሽ የሚሆነው የመንገድ ኮሪደር ልማት ነው፡፡ ሳሎንን አስውቦ ጓዳውን መተው እንዳይሆን ይህን የልማት ስራ ዘርፈ ብዙ ማድረግ በማስፈለጉ ወንዞችን የማልማት እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ይገኛል፡፡ ከዚህም ዓላማ ሰፋ ባለ መልኩ ወንዞች ላይ ከፍተኛ በሆነ ደረጃ እየደረሰባቸው ያለውን ጉዳት እና ብክለት ለመቆጣጠር እንዲሁም አስገዳጅነት ይኖረው ዘንድ በህግ ታቅፎ ይገኛል፡፡

በፌደራል ደረጃ የትኛውንም የውሃ አካል አጠቃቀም እና ዳርቻዎችን እርቀት ለመወሰን በ2017 በረቂቅ ደረጃ ለ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ እና ሂደት ላይ ያለ ነው፡፡ ይህም ረቂቅ ከወንዝ በተጨማሪ ኩሬ፣ ሃይቅ፣ ጠበብ ብለው በውሃ የተሸፈኑ ስፍራዎችን እና ባህርን የሚያጠቃልል እና በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ላይ የተፈጻሚነት ወሰን ያለው ነው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ፀድቆ ወደ ሥራ የገባው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017 በቀጣይም ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል እና የከተማው የአስተዳደር አካላት በመቀናጀት ተፈጻሚነቱን የሚያረጋግጡ ይሆናል፡፡



የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017 ተፈጻሚነቱን ለማረጋገጥ ከግለሰብ እስከ አስተዳደር አካላት የሚሰሩ ሲሆን፤ አስፈጻሚ አካላት በቅንጅት የሚሰሩ ይሆናል

### ወንዝን ጨምሮ አካባቢን የመጠበቅ አስፈላጊነት ጽንሰ ሀሳብ /መላምት /theory/

ይህ መላምት ወይም ሀሳብ የሚለይልን ተፈጥሮን ወይም አካባቢን ወንዝንም ጨምሮ የሚደረግላቸውን ጥበቃ አስፈላጊነት ለምን እንደሆነ ለመለየት የሚረዳ ነው፡፡ ሁለት አይነት ሃሳቦች በአካባቢ ጥበቃ አቀንቃኞች እና ተሚጋቾች ይሰነዘራሉ ፡-

1ኛ ፡- ተፈጥሮን የምንጠብቀው ለሰው ልጅ ካላቸው ጥቅም የተነሳ ነው የሚሉ ሲሆን አንትሮስንተሪክ በሚል ቱዮሪ ስያሜ የሚታወቁ ናቸው ፡፡

ምሳሌ፡- የወንዝን ብክለት የምንከላከለው ወንዞች ለሰው ልጅ ለመስጠት፣ ሲጠባበቁ ካላቸው ውበት እና ንጽህና መጠጥ እንዲሁም የሰውን አዕምሮ የሚያድሱ በመሆናቸው ነው፡፡

2ኛ፡-- ተፈጥሮን የምንጠብቀው ለሰው ልጅ ካላቸው ፋይዳ ሳይሆን እራሳቸውን ችለው መብት ስላላቸው እና መጠበቅ ስላለበቸው ብቻ ነው፡፡ ይህም ማለት ለሰው ልጅ ጥቅም ኖሯቸው አልኖራቸው መጠበቅ አለባቸው በማለት የሚሟገቱ ናቸው፡፡ ይህን ቲዮሪ አቀንቃኞች ኢኮሴንተሪክ የሚል ስያሜ ያላቸው ናቸው፡፡ የሀገራችን የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ወንዝን ጨምሮ ከማን አንጻር ማለትም ከአካባቢ አንጻር ወይስ ከሚሰጡት ጥቅም አንጻር መሆኑን ከተለያዩ ህጎች እንጻር የሚዳሰስ ይሆናል።

### የደንብ ቁጥር 180/2017 መውጣት አስፈላጊነት

የደንብ ቁጥር 180/2017 መውጣት አስፈላጊነት በሁለት አይነት መንገድ ተከፍሎ የሚታይ ነው፡-

### ወቅታዊ ወይም አፋጣኝ ምክንያት

ወንዞች አሁን ላይ በሰው ሰራሽም ይሁን በሌላም ምክንያት መጠናቸው እና ጥራታቸው ላይ ጉዳት እየደረሰ እንዲሁም ውሃን የመያዝ እና እንዳይደርቁ የሚከላከሉ የእጽዋት አይነቶች መመናመናቸው በተጨማሪም በከፍተኛ ብክለት የአካባቢን ገጽታ እያጠፉ በመሆናቸው ነው፡፡

### መሰረታዊ (መነሻ) ምክንያት፡-

ሁሉም ሰው ንጹህና ጤናማ አካባቢ የመኖር መብት ከሰብዓዊ መብቶች በሶስተኛነት ደረጃ የሚመደብ ( 3rd generation right ) በመሆኑ እና ይህም በሕገ-መንግስታችን አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 1 እዉቅና/ጥበቃ (recognition) ያገኘ መብት ነው። ታድያ መንግስትም ይህን መሰረታዊ የዜጎች መብትን የማስከበር ግዴታ ያለበት በመሆኑ እና አስገዳጅነት እንዲኖረው በማይፈጽሙ አካላት ላይ ተመጣጣኝ ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ ሊያስወስድ የሚችል ዝርዝር የህግ ማዕቀፍ በማስፈለጉ ይህ ደንብ ወጥቷል፡፡

- **ክልከላ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017 በውስጡ መቆጣጠር ያስችላል ተብሎ የሚጣሉ ክልከላ እና ቅጣት አስቀምጧል። በዋናነት መኖሪያ ቤቶች፣ ከአምራች ድርጅቶች እና ከተቋማት የሚጣሉ የትኛውም አይነት ደረቅ ቆሻሻ፣ ኬሚካል፣ የሚለቀቁ የሽንት ቤት ፍሳሽ እና የትኛውም አይነት ያልተጣራ ፍሳሽ ወደ ወንዝ ወይም ከወንዝ ጋር ወደተያያዙ መስመሮች መልቀቅ እንዲሁም በወንዝ 30 ሜትር ወሰን ውስጥ የትኛውንም ከመዝናኛ እና የአካባቢ ልማት ውጪ ያለ ግንባታ ማካሄድ የተከለከለ ነው፡፡ ይህም በደንቡ አንቀጽ 7 መሰረት የተደነገገ ነው።

- **ቅጣት**

### አስተዳደራዊ እርምጃ

የጉዳቱን መጠን እና የመክፈል አቅምን ታሳቢ በማድረግ ለግለሰብ እና ለተቋም በመለየት የተለያዩ ቅጣቶች እንደተቀመጡ የደንቡ አንቀጽ 17 ያሳያል። የተቋሙን ፍቃድ መሰረዝ፣ ማሸግ፣ ድርጊቱን የማስቆም ጉዳት ደርሶም ከሆነ ወደ ነበረበት እንዲመለስ ማድረግ ተካተዋል፡፡

### የገንዘብ ቅጣት

እንደየጥፋቱ አይነት ከ 1,000 እስከ 400,000 ብር ድረስ የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት

### ከውል ውጭ የመነጨ ቅጣት

በወንዞች ብክለት ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው በብክለቱ ምክንያት ጉዳት እንደደረሰበት በማስረዳት ለደረሰበት ጉዳት ካሳ የመጠየቅ መብት አለው፡፡

### የወንጀል ቅጣት

በ1997 የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 17 መሰረት ወንዝን ሆን ብሎ የበከለ ወይም የመረዘ እስከ 15 ዓመት ድረስ ጽኑ እስራት የሚተላለፍበት ሲሆን በቸልተኝነት ከሆነ እስከ 6 ወር የሚደርስ የእስር ቅጣት እንደሚተላለፍበት ይደነግጋል፡፡

### አስፈጻሚ ባለድርሻ አካላት

የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017 ተፈጻሚነቱን ለማረጋገጥ ከግለሰብ እስከ አስተዳደር አካላት የሚሰሩ ሲሆን፤ አስፈጻሚ አካላት በቅንጅት የሚሰሩ ይሆናል፡፡ ለአብነት ያህል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ዉበትና አረንጎዴ ልማት ቢሮ፣ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ የደንብ ማስከበር ባለስልጣን፣ የአዲስ አበባ ከተማ መንገድ ባለስልጣን ሲኖሩ ወደፊትም በትስስር እና ቅንጅት ስምምነት ባለድርሻ ሆነው የሚገቡትን ይጨምራል፡፡

# የማዕከላቱ ዘወትራዊ አገልግሎት

- መንግስት ባቋቋማቸው የገበያ ማዕከላት የሚፈፀሙ ግብይቶች በመደበኛው ከሚቀርበው የፍጆታ ምርት ዋጋ ከ15 እስከ 20 በመቶ ቅናሽ ያለው መሆኑ ተጠቁሟል

**በፋንታነሽ ተፈራ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኑሮ ውድነትንና የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት በከተማዋ የመግቢያ በሮች የግብርና ምርቶች ማከፋፈያ የገበያ ማዕከላትን ገንብቶ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረጉን የዝግጅት ክፍላችን ቅኝት ባደረገባቸው ማዕከላት ያነጋገርናቸው ነጋዴዎችና ሸማቾች አስተያየታቸውን ሰጥተውናል፡፡

ወይዘሮ ወርቂ ሙሉአለም የለሚ ኩራ የግብርና ምርቶች ገበያ ማዕከል አትክልትና ፍራፍሬ ሲሸምቱ ነው ያገኘናቸው፡፡ በማዕከሉ የሸመቱት ሽንኩርት፣ ቲማቲም፣ ካሮት እንዲሁም ጎመን የአቅርቦት ችግር እንደሌለው እና ዋጋውም ውጭ ከሚሸጠው ጋር ሲነፃፀር የ10 እና 15 ብር ቅናሽ እንዳለው ነግረውናል፡፡

መንግስት የገበያ ማዕከላትን በየአካባቢው መገንባቱ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቶልናል፡፡ ከመኖሪያ አካባቢያችን ሳንርቅ በቅርበት በፈለግነው ሰዓት ትኩስ ምርት መሸመት አስችሎናል፤ እንደዚህ አይነት ማዕከል በየአካባቢው በብዛት ቢገነቡ ህብረተሰቡን የበለጠ ተጠቃሚ በማድረግ የኑሮ ውድነቱን ለማቃለል አጋዥ ናቸው ሲሉም ሃሳባቸውን አጋርተዋል፡፡

ሌላኛዋ፤ የግብርና ምርቶች የሆኑትን ጤፍ፣ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ምርቶችን ደግሞ ዘይትም ሆነ ዱቄት ከማዕከሉ እንደሚሸምቱ የነገሩን ወይዘሮ ሃያት አብደላ ናቸው፡፡ ወይዘሮዋ እንደሚሉት ማዕከሉ ስራ ከጀመረ ጀምሮ ጤፍ የሚገዙት ከማዕከሉ መሆኑን ነው፡፡


ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል
በለሚ ኩራ የግብርና ምርቶች ገበያ ማዕከል ግብይት ሲካሄድ

"አንደኛ ደረጃ ጤፍ በኪሎ ከ120 ብር እስከ 125 ብር እንገዛለን፡፡ ከማዕከሉ ውጭ ግን የ125 ብሩ ጤፍ እስከ 140 ብር ነው የሚሸጠው፡፡ በማዕከሉ የምፈልገውን ጤፍ መርጬ ገዝቼ እሄዳለሁ እጥረት ኖሮ ሳልገዛ የተመለስኩበት ጊዜ የለም፡፡ ዋጋውም ቢሆን ከውጭው ጋር በአንድ ኪሎ ላይ ከ10 እስከ 15 ብር ልዩነት አለው፡፡ ይህ ደግሞ ትልቅ ልዩነት ነው። ሌሎች እንደ እኔ አይነት ሸማቾች በቅናሽ በማዕከሉ እንዲሸምቱ እላለሁ" ሲሉ ማዕከሉ ከሚያመጣቸው ምርቶች ተጠቃሚ ቢሆኑ ይላሉ፡፡

በማዕከሉ በኢንዱስትሪ ምርቶች ላይ ተሰማርተው ያገኘናቸው ወይዘሮ ፍሬህይወት ሽመልስ ናቸው፡፡ "ወደ ማዕከሉ ከተቀላቀልን ጀምሮ በበዓላት ወቅት በተለየ ሁኔታ የፍጆታ እቃዎች እንደ ዘይት፣ ዱቄት፣ ስኳር፣ ቡና፣ በርበሬ እንዲሁም ጤፍና ጥራጥሬዎች የማህበረሰቡም ፍላጎት በዚያው ልክ ስለሚጨምር በብዛት እናስገባለን፡፡ ጤፉ የራሳችን ምርት ነው፤ ሌሎች ሸማቾች መጥተው አጥተው የሚመለሱት ምንም ነገር የለም፡፡ ዋጋውም ቢሆን ለበዓላት ወቅት የይርጋ ጨፌ ቡና 950 ብር፣ በቅርብ ጊዜ ወደ ማዕከሉም ስለመጣን በራሳችን ትራንስፖርት እና ምርት ስለሆነ የተጋነነ የዋጋ ጭማሬ አልታየም። በበዓላት ሰሞን በሚሸጥበት ዋጋ ነው አሁን እየተሸጠ ያለው፡፡ ይህ ደግሞ የማህበረሰቡን ፍላጎት ያማከለ እና ውጭ ላይ ከሚሸጠው ዋጋ ቅናሽ ነው" ይላሉ፡፡

አንዳንድ ከሚመጡበት ቦታ ከሚጨምሩ እንደ ስኳርና ቡና በስተቀር ዘይት መቀነስ እንጂ ጭማሬ አላሳየም፤ ጤፍ ደግሞ በበዓሉ ተመሳሳይ ዋጋ በኪሎ ከ110 ብር እስከ 125 ብር እየተሸጠ ይገኛል፡፡ ማህበረሰቡም ደስተኛ ሆኖ ነው የሚሸምተው፡፡

ከራሳችን ጥቅም ይልቅ የህዝቡን ጥቅም ነው የምናስቀድመው የሚሉት ነጋዴዋ፤ በዚህ አጋጣሚም ማህበረሰቡ ከማዕከሉ ውጭ ያለውን ገበያ ጠይቆ ወደ ማዕከሉ መጥቶ ግብይት እንዲፈፅም ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ሌላኛው በማዕከሉ በአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ላይ የተሰማሩት አቶ መርከብ ገብረ እግዚአብሔር ናቸው። ሽንኩርት፣ ድንች፣ ጎመን፣ ቲማቲም እና የመሳሰሉ አትክልቶችን እንዲሁም ፓፓያ፣ አቮካዶ፣ ብርቱካንና የመሳሰሉትን ፍራፍሬዎች እንደሚሸጡ ገልፀው ዋጋቸውንም በተመጣጣኝ ሁኔታ እንደሚያቀርቡ አንስተዋል፡፡ ይህንንም በምሳሌነት ውጭ ላይ አቮካዶ እስከ 40 ብር፣ ኤልፎራ ቃሪያ እስከ 120 ብር እየሸጥን ነው ብለዋል፡፡

ምርቶች እንደ አገባባቸው ሊቀንሱና ሊጨምሩ እንደሚችሉ የነገሩን አቶ መርከብ፤ ለበዓላት ሰሞን ገብተው የነበሩ ምርቶች በተሸጡበት ዋጋ በአሁኑ ወቅት እየተሸጠ ይገኛል፡፡ ምርት ከማሳ እንዲሁም የእነሱ ምርት ካልደረሰ ከተመረቱበት ቦታ ስለሚያመጡ ትኩስ እና ዋጋውም ተመጣጣኝ መሆኑን ነው የነገሩን፡፡

የማዕከሉ ስራ አስኪያጅ አቶ ምህረቱ ቀና በበኩላቸው፤ ላለፉት እንቁጣጣሽና መስቀል በዓላት ቀጥታ ከማሳ የተለያዩ ምርቶችን በሰፊው እንዲገቡ በማድረግ ሸማቹ ማህበረሰብ ትኩስ ምርቶችንና ውጭ ላይ ከሚሸጠው ዋጋ ቅናሽ በሆነ መንገድ እንዲሸምት የማድረግ ስራዎች መሰራታቸውን ነግረውናል፡፡

ማዕከሉም የተቋቋመበት ዋና አላማ፤ ውጭ ላይ ካለው ገበያ በቀነሰ ዋጋ በመሸጥ ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ማድረግና ገበያውን ማረጋጋት ነው። ቅናሹም ከ15 እስከ 20 በመቶ ነው፡፡ በማዕከሉ ለበዓላት ሰሞን የነበረው ዋጋ እና አቅርቦት ልዩነት የለውም ያሉት ስራ አስኪያጁ፤ ምርቶች በበዓላት ሲሸጡበት በነበረው ዋጋ እና አዳዲስ ምርት ሲገባ ደግሞ እየቀነሰ እንደሚሸጥ አንስተዋል፡፡

በበዓላት ወቅት የነበረው አቅርቦትና የዋጋ ተመጣጣኝነት ቀጣይነት እንዲኖረው ከአቅራቢዎች ጋር በመነጋገር ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ መሆኑን የነገሩን አቶ ምህረቱ፤ በየቀኑ የፍጆታ እቃዎቹ በተለጠፈላቸው ዋጋ መሸጣቸውን እንዲሁም ጥራታቸውን ለማረጋገጥ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎች ይሰራሉ ብለዋል፡፡

ማህበረሰቡም ከውጭ ያለውን ዋጋ በማነፃፀር ከሩቅ ቦታዎች ሳይቀር በመምጣት ሁሉንም የፍጆታ ምርቶች ሸምቶ በመሄዱ ረገድ በፊት ከነበረው አንፃር ተጠቃሚው እየጨመረ መጥቷል። ብዙ ሰዎችም የሚስተናገዱበት ሆኗል ሲሉ በበዓላት ወቅት የነበረው ዝግጅት የሁልጊዜ መሆኑን ነግረውናል፡፡

ሌላኛው የዝግጅት ክፍላችን ቅኝት ያደረገበት የገበያ ማዕከል የአቃቂ ቃሊቲ የግብርና ምርቶች የገበያ ማዕከል ነው። በማዕከሉ ሽንኩርት፣ ድንች፣ ካሮትና ቃሪያ የመሳሰሉትን አትክልቶች ሲሸምቱ ያገኘናቸው ወይዘሮ አስቴር ካሳ፤ "ማዕከሉ ከተቋቋመ ጀምሮ ግብይት እፈፅማለሁ ለበዓላት ሰሞን የነበረው ዋጋም ሆነ አቅርቦት እስከ አሁን እንደቀጠለ ነው፡፡ እንዲያውም ሽንኩርትና ቃሪያ ከበዓላት በኋላ ቅናሽ ነው፡፡ በተለየ ሁኔታ ቃሪያ በግማሽ ቀንሷል፡፡ በበዓላት ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ቀን ቢሆን ተወደደ ከተባለ እንኳን ውጭ ሱቆች ላይ ከምንገዛው ከ20 ብር ያላነሰ በእያንዳንዱ እቃ ላይ ቅናሽ ኖሮት እንሸምታለን፡፡ በዚህም ከማዕከሉ ውጭ ሌላ ጋር ሸምቼ አላውቅም" ሲሉ ነው የነገሩን፡፡

የወይዘሮ አስቴርን ሃሳብ የሚጋሩትና በማዕከሉ ሸቀጣ ሸቀጥ እንደ ምስር፣ አጃ፣ ዘይት እና ስኳር ሲሸምቱ ያገኘናቸው ወይዘሮ ፀሐይ ሰይድም በማዕከሉ ብዙ ጊዜ እንደሚሸምቱ ነው የገለፁልን፡፡ ጤፍም እንደ ደረጃው ከ110 ብር ጀምሮ እስከ 125 ብር እንደሚሸምቱ ገልፀው፤ "አትክልትና ፍራፍሬን ጨምሮ ሁሉንም የሚያስፈልጉኝን ነገሮች እየመጣሁ እገዛለሁ፡፡ ለአዲስ ዓመት እና ለመስቀል የነበሩ ግብዓቶች አሁንም አሉ፤ ምንም የተለየ ነገር የለውም፡፡ ዋጋቸውም ከቲማቲም እና ስኳር ውጭ የጨመረ እቃ የለም" ሲሉ ውጭ ከሚሸጠው ጋር የዋጋም ሆነ የጥራት ልዩነት መኖሩን ነው ያጫወቱን፡፡

አቶ ጌቱ ሰይፉ በአቃቂ ቃሊቲ የግብርና ምርቶች የገበያ ማዕከል ከማሳቸው በማምረት በማዕከሉ ከሚሸጡ ነጋዴዎች መካከል አንዱ ናቸው፡፡ በማዕከሉ በቂ የምርት አቅርቦት መኖሩን ጠቁመው፤ የተለያዩ የግብርና ምርቶች ለአብነት ከፍራፍሬ አቮካዶ፣ ፓፓያ፣ ሃባብ፣ ሙዝ፤ ከአትክልት ድንች፣ ቃሪያ፣ ቲማቲም፣ ካሮት፣ ዝንጅብል፣ ሽንኩርትና ሌሎችንም ምርቶች ለሸማቾች ውጭ ላይ ከሚሸጠው በቅናሽ ዋጋ እያቀረቡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

"በበዓላት ወቅትም በተለይ ለአዲስ ዓመት አቅርቦትም ሆነ የዋጋ ተመጣጣኝነት ነበረ፡፡ እነዚህ ለበዓላት የቀረቡ ምርቶች እንዲሁም ዋጋቸው ከበዓላቱም በኋላ እንደቀጠለ ነው። የሽንኩርት፣ ቃሪያ እና ድንች ዋጋ በወቅቱ ይሸጡበት ከነበረው ዋጋ ቅናሽ አሳይተዋል፡፡ ምርቶቹን ከጉራጌ ዞን ከማሳችን ስለምናመጣቸውም የአቅርቦት ችግር አልገጠመንም፡፡ ዋጋችንም ቢሆን ውጭ ላይ ከሚሸጠው መንግስት ባወጣልን ተመን መሰረት ነው የምንሸጠው፤ አንዳንድ ጊዜ እንዳይበላሽ ከፈራንም ከተመኑ በታች ቀንሰን እንሸጣለን" ሲሉ በማዕከሉ የምርት አቅርቦትም ሆነ የዋጋ ጭማሬ እንደሌለ ገልፀው፤ የአካባቢው ነዋሪዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ መልዕክታቸው ነው፡፡

በማዕከሉ በጥራጥሬና ሸቀጣሸቀጥ ንግድ ላይ የተሰማሩት ደግሞ ወይዘሮ ረሂማ ሙክታር ናቸው፡፡ እንደ ምስር፣ አተር፣ አጃ፣ የኢንዱስትሪ ምርቶች ዘይት፣ ዱቄት፣ ስኳር እና ሌሎችንም ግብዓቶች ለህብረተሰቡ እንደሚያቀርቡ ነግረውናል፡፡ እነዚህ የፍጆታ ምርቶች ከስኳር በስተቀር ለበዓላት ሰሞንም በተሸጡበት ዋጋ እየተሸጡ ይገኛሉ፡፡

ዋጋቸውም ውጭ ላይ ከሚሸጠው እዚህ የምንሸጠው ቅናሽ ነው፡፡ ለዚህም ማህበረሰቡ በጥራትም በዋጋም እንዲሁም በአቅርቦትም ሁሉም በተሟላበት ማዕከላችን መጥተው እንዲሸምቱ አሳስባለሁ ብለዋል፡፡

በማዕከሉ በእንስሳት ተዋፅኦ (አይብ፣ አሳ፣ ዶሮ፣ እንቁላል) ንግድ ላይ የተሰማራችው ወጣት ሃና ተሻለም

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# የመዲናዋ ጥበባዊ መረጃዎች

**በአብርሃም ገብሬ**

የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች እና አዳዲስ ኪነ ጥበባዊ ሥራዎች ባለፉት ቀናት በመዲናዋ አዲስ አበባ ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም የተለያዩ ጥበባዊ መሰናዶዎች ይደረጋሉ፡፡ ከተሰናዱ ዋና ዋና ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች መካከል የሙዚቃ ዝግጅት፣ የመጽሐፍት ውይይት፣ የሥዕል አውደ ርዕይ፣ የቴአትር መርሃ ግብር እና ሌሎች መሰናዶዎች ይገኙበታል፡፡ ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡




ፎቶ- ከገፀ ድር

በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

## መጽሐፍት

ዛሬ 'ቀይ አንበሳ' በተሰኘው መጽሐፍ ላይ ውይይት ይደረጋል፡፡ ቀይ አንበሳ የተባለው መጽሐፍ በዋናነት ከ1928 እስከ 1933 ዓ.ም. ድረስ በቆየው የጣሊያን ወረራ ላይ ያተኩራል፡፡ የመጽሐፉ ደራሲ ኮረኔል አልኸንድሮ ዴል ባዬ የተባሉ ኩባዊ ሲሆኑ፣ በወቅቱ የኢትዮጵያ የጦር ሚኒስቴር ምኒስትር ከነበሩት ራስ ሙሉጌታ ይገዙ ጋር አምባላጌ የዘመተ በጎ ፈቃደኛ መኮንን ናቸው። መጽሐፉ የጣሊያን ጦር በኢትዮጵያ አርበኞች ላይ የፈጸመውን ግፍና መከራ፣ የኢትዮጵያ አርበኞች በጦር ሜዳ ያደረጉትን ተጋድሎ፣ በጊዜው የነበረው የኢትዮጵያውያን አኗኗርና ማህበራዊ መስተጋብርን የሚመለከቱ አስገራሚ መረጃዎችን የያዘ ነው፡፡

'ቀይ አንበሳ' የጣሊያን ወረራን በሚመለከት የአይን እማኝ በነበሩ የውጭ የጦር መኮንኖች ከተጻፉ መጽሐፍት መካከል ከ'የሃበሻ ጀብዱ' ቀጥሎ የሚጠቀስ ተወዳጅ መጽሐፍ ነው ሊባል ይችላል፡፡ ዛጎል የመጽሐፍ ባንክ ባሰናዳው በዚህ የመጽሐፍ ውይይት ላይ፣ መጽሐፉን ከስፔን ቋንቋ ወደ አማርኛ ቋንቋ የተረጎሙት ተርጓሚ ተስፋዬ መኮንን ባይለየኝ (ዶ/ር) በተጋባዥነት ይቀርባሉ፡፡ ውይይቱ ዛሬ ቅዳሜ ከ8:00 ሰዓት ጀምሮ ይደረጋል፡፡ የውይይቱ አዘጋጅና አቅራቢ ደራሲ እንዳለጌታ ከበደ ሲሆን፣ ውይይቱ የሚካሄድበት ቦታ ደግሞ በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (FSS.) አዳራሽ ውስጥ ነው፡፡ አድራሻው ቀበና፣ የካቶሊክ ኪዳነምሕረት ትምህርት ቤት ፊት ለፊት፣ ባማ ሕንጻ አጠገብ ይገኛል፡፡

'ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት' የተሰኘው መጽሐፍ ለንባብ በቃ፡፡ በዶ/ር አስቴር ሙሉ የተጻፈው ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያ የተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ የሚገኙ የትውን ጥበባት ውጤቶችን የተዳሰሰበት የምርምር ሥራ ነው ተብሏል፡፡ ደራሲዋ በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ የፎክሎርና ስነጽሑፍ መምህርት እና ተመራማሪ ሲሆኑ፣ ያዘጋጁት ይሄ መጽሐፍ በሃገረሰባዊ ትውን ጥበባት የምርምር ዘርፍ ውስጥ ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑም ከመጽሃፉ ጀርባ አስተያየታቸውን ያሰፈሩት ዘሪሁን አስፋው (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ገልጸዋል፡፡ መጽሐፉ በተለያዩ የመጽሐፍት መደብር ውስጥ ይገኛል ተብሏል፡፡

## ሙዚቃ

በሞሰብ የሙዚቃ ማዕከል ውስጥ የሙዚቃ ዝግጅት ይደረጋል፡፡ ነገ እሁድ ጠቅምት 9 ቀን 2018 ዓ.ም. ሶሻል አዲስ ከሞሰብ የሙዚቃ ማዕከል ጋር በመተባበር ያሰናዱት የሙዚቃ ዝግጅት ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት ጀምሮ ይቀርባል፡፡ እንዲሁም በመጪው ማክሰኞ ጥቅምት 11 ቀን 2018 ዓ.ም. ልዩ የመሰንቆ ምሽት ከ10 በላይ ተወዳጅ የመሰንቆ ተጫዋቾች የሚገኙበት ዝግጅት ከምሽቱ 1 ሰዓት ጀምሮ ይቀርባል ተብሏል፡፡ ሙዚቃው የተሰናዳበት አድራሻ ደግሞ ከ24 ወደ ለም ሆቴል በሚወስደው መንገድ ከሲድራ ሆቴል ከፍ ብሎ መሆኑ ታውቋል፡፡

## ሥዕል

የአንጋፋው ሰዓሊ ወርቁ ማሞ ልጅ በሆነችው በወጣቷ ሰዓሊ ገብርኤሏ ወርቁ ማሞ የተዘጋጁ የሥዕል ሥራዎች የሚቀርቡበት "ከልብስ ባሻገር" የሥዕል አውደ ርዕይ ከዛሬ ጀምሮ ለዕይታ ክፍት ይሆናል፡፡ ይህ የሥዕል አውደ ርዕይ በአርታዊ የሥዕል ማሳያ ውስጥ ለዕይታ እንደሚበቃ ኢቨንት አዲስ ሚዲያ ዘግቧል፡፡ አውደ ርዕዩ እስከ ፊታችን ጥቅምት 29 ቀን 2018 ዓ.ም በእይታ ላይ ይቆያል ተብሏል።

በሌላ መረጃ ደግሞ፤ የአእምሮ ጤና ላይ ያተኮረ የሥዕል አውደ ርዕይ በመታየት ላይ እንደሚገኝ ተጠቁሟል፡፡ የአእምሮ ጤና ላይ ትኩረት ያደረጉ የሥዕል ሥራዎች የቀረቡበት "Art inspired by mental health" በተሰኘ የሥዕል አውደ ርዕይ ላይ ሲሆን፤ ቦታውም ስድስት ኪሎ በሚገኘው በገብረክርስቶስ ደስታ ዘመናዊ የሥነ ጥበብ ሙዚየም ውስጥ ነው። በስዕል አውደ ርዕዩ ላይ የቀረቡ የጥበብ ሥራዎች፤ የአዕምሮ ጤና ትልቅ ትኩረት እንደሚሻ የሚያስገነዝቡ ናቸው ተብሏል፡፡ በዚህ አውደ ርዕይ የሠዓሊ ሶሎሜ ጌታቸው እና የሠዓሊ አለማየሁ ደረሰ ሥዕሎች ቀርበዋል፡፡ አውደርዕዩ ዛሬ ይጠናቀቃል ተብሏል፡፡

## ቴአትር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ፡፡ '12ቱ እንግዶች' የተሰኘው ቴአትር ቅዳሜ 8:30 ሰዓት በብሔራዊ ቴአትር ቤት ይታያል፡፡ 11፡30 ሰዓት ደግሞ 'ባሎችና ሚስቶች' የተሰኘው ቴአትር በዚያው በብሔራዊ ቴአትር ይታያል፡፡ እሁድ በ8፡30 ሰዓት ደግሞ 'ንጉሥ አርማህ' ቴአትር፣ እንዲሁም 'እምዩ ብረቷ' የተሰኘው ቴአትር ደግሞ በዚሁ በብሔራዊ ቴአትር 11፡30 ሰዓት ላይ ይታያል፡፡

በሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ደግሞ እሁድ በ8:00 'የደመና ዳንኪረኞች' የተሰኘው ቴአትር ይታያል፡፡ በተጨማሪም በቀጣይ ቀናት በብሄራዊ ቴአትር የሚታዩት ማክሰኞ በ11፡30 'ሶስቱ አይጦች'፣ ረዕቡ በ11፡30 'የቅርብ ሩቅ' ቴአትር፣ ሐሙስ ቀን 11:30 'ሽምጋይ' ቴአትር፣ አርብ በ11፡30 'የሕይወት ታሪክ' በብሄራዊ ቴአትር ለጥበብ አፍቃሪያን ለዕይታ ይቀርባሉ፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን፤ ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሠራርና መልስ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡ በመጀመሪያ ክብ በግራ በኩል ያለው ነጠላ ቁጥር በመሃል ባለው ክብ በስተቀኝ ካለው ነጠላ ቁጥር ጋር እንደምራለን፡፡ ደምረን የምናገኘው ውጤት ደግሞ በመሃል ክብ ውስጥ በስተቀኝ ያሉት ሁለት አሃዞች መምጣት ይኖርበታል፡፡ ከዚያ ደግሞ በመጀመሪያ ክብ ላይ የቀረው ብቸኛ ቁጥር በስተቀኝ ክብ ውስጥ ከቀረው ብቸኛ ቁጥር ጋር እናባዛለን፡፡ ደምረን እና አባዝተን ያገኘናቸው ቁጥሮች በመደዳ ስናስቀምጣቸው የሚመጣው ውጤት የመሃልኛው ክብ ሦስቱ አሃዞች መምጣት ይኖርበታል፡፡ ለአብነትም የመጀመሪያ ረድፍ ላይ ያለው ክብ የጥያቄ አሠራርና መልሱን አብረን እንስራው። 7 + 8 = 15 ይሆናል፡፡ 2 x 4 = 8 ይሆናል፡፡ ከዚያ በኋላ ያገኘናቸው ቁጥሮች በመደዳ በዚህ መልክ እንደረድራቸዋለን፤ 158፡፡ በዚህ መሰረት የጥያቄውን ትክክለኛ አሠራርና መልስ የምናገኘው፡፡ ይሄን መነሻ




በማድረግ የጥያቄው መልስ 127 ይሆናል፡፡ አሰራሩ ደግሞ 9 + 3 = 12 ይሆናል፡፡ 7 x 1 = 7 ይሆናል፡፡ መደዳ ስንደረድራቸው 127 ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት የጥያቄው ትክክለኛ መልስ 127 ይሆናል፡፡

## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# ጥቅምት፣ ውበት እና ኪነት

**በአብርሃም ገብሬ**

ወራት ልክ እንደ ሰዎች ሁሉ ልዩ ባህርያትና መገለጫዎች አሏቸው፡፡ ይሄ ልዩ መገለጫቸው አንድም ከተፈጥሮ ጋር ባላቸው መስተጋብር ክሱት ይሆናል፡፡ አንድም በወራቱ ውስጥ የሚታዩ መልከ-ብዙ ተፈጥሯዊ ኩነቶች በሰዎች ህይወት ላይ በሚፈጥሩት አዎንታዊና አሉታዊ ገጽታ ይመሰረታል፡፡ ለአብነትም ስለ ክረምት ወራት ስናስብ ወደ አዕምሯችን ከሚመጡ ኩነቶች መካከል አንዱ ዝናብ ነው፡፡ ዝናቡን ተከትለው የሚመጡት ጭጋግ፣ ቅዝቃዜ፣ ደመና፣ ጭቃ፣ ወንዝ ሙላት... የዚህ የክረምት ዋና ዋና መገለጫዎች ናቸው፡፡

እነዚህ ተፈጥሯዊ ኩነቶች ደግሞ በሰዎች ዘወትራዊ የሕይወት እንቅስቃሴ ላይ የሚፈጥሩት ተጽዕኖ አለ፡፡ እንዲሁም ከበጋ ወራት የተለየ ድባብና አዕምሯዊ ሁኔታም (ሙድ) በሰዎች ስሜት ላይ ይፈጥራሉ፡፡ ሰዎች ከሚፈጠርባቸው ድባብና የስሜት ሁኔታ በመነሳት ስለ ወራት መገለጫ ባህርያት ይሰጣሉ፡፡

ኢትዮጵያውያንም ለመፀው፣ ለበጋ፣ ለፀደይና ለክረምት ወራት የተለያዩ ስሜቶች አሏቸው፡፡ በተለይ የክረምቱን ማለፍ የሚያውጀው የመስከረም ወር መምጣትን በከፍተኛ ጉጉትና ተስፋ ይቀበሉታል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ዘመን የሚለወጠው በዚህ ወር ነው፡፡ እንደ መስቀልና ኢሬቻ ያሉ የአደባባይ በዓሎች በደስታ የሚከበሩትም በዚህ ወር ነው፡፡ ልጆች ወደ ትምህርት ቤት የሚመለሱትና እንደ ፍርድ ቤት ያሉ መንግስታዊ ተቋማት ስራቸውን እንደገና የሚጀምሩትም በዚሁ ወር ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን አዳዲስ ዕቅዶችን በመወጠን በአዲስ ሃይል የሚነሳሱትም የመስከረም ወር ድባብን መነሻ በማድረግ ነው፡፡

ምድርም ከወርሃ መስከረም ጀምራ ማሸብረቅ ትጀምራለች፡፡ መስኮች አደይ አበባ ይለብሳሉ፡፡ በክረምት ዝናብ የሞሉ ወንዞች መጉደል ይጀምራሉ፡፡ የደፈረሱ ወንዞችም መጥራት ይጀምራሉ፡፡ ሰማይ ለፈትል እንደተዘጋጀ ጋቢ ትነጣለች። ይህች የመስከረም ድባብ ወደ ወርሃ ጥቅምት ስትሸጋገር ተፈጥሮ ይበልጥ ተውባና ተኳኩላ ትታያለች፡፡ ውበቷ ልክ እንደ ሙሽሮች የፊት ገጽ ይፈካል። መስኮች በአረንጓዴ ያጌጣሉ፡፡ አበቦቹ በየቦታው ፍንድቅድቅ ብለው ተስፋን ያዜማሉ፡፡ ይሄ ድባብ ደግሞ በሰዎች ስሜት ላይ ቀጥታ የመጋባት ሃይል አለው፡፡ በሀገራችን በተለያዩ የኪነጥበብ ሥራዎች ውስጥ ጎልተው የሚሰሙ ዜማዎችና ስንኞች የዚህ ስሜት ነጸብራቅ ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ እኛም በዚህ አጭር ጽሑፍ በኢትዮጵያ አውድ ወርሃ ጥቅምትን በኪነ ጥበብ ሥራዎችና በህዝባዊ ሥነ-ቃሎች እንዴት እንደተገለጹ በጨረፍታ ልናስቃኛችሁ ወድደናል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

ውበትና ልምላሜ ያሰናኘችው ወርሃ ጥቅምት

## የአበቦች ሙዚቃ በጥቅምት

የባህል፣ የሰላምና የኪነ ጥበብ ተመራማሪው ወሰን ባዩ (ዶ/ር) ከወርሃ ጥቅምት ጋር በተያያዘ ለዝግጅት ክፍላችን ሃሳባቸውን አጋርተዋል፡፡ ኢትዮጵያውያን ጥቅምትን ከውበትና ከተስፋ ጋር አስተሳስረው እንደሚረዱት ያጫወቱን ወሰን ባዩ (ዶ/ር)፣ በመስከረም የጀመረው አበባ ሙሉ በሙሉ የሚፈካበት ቡቃያው ወደ እሸት የሚያድግበት ጊዜ በመሆኑ በማህበረሰቡ ውስጥ ጥቅምት ከተስፋና ከልምላሜ ጋር ተያይዞ ይወሳል፡፡ ወርሃ ጥቅምት በእሸት፣ በአበባ፣ በውበትና በተስፋ እንደሚመሰልም ተመራማሪው አጫውተውናል፡፡ ጥቅምትን መነሻ ተደርገው የተቀነቀኑ ዜማዎች፣ የተገጠሙ የግጥም ስንኞችና ማህበረሰባዊ ሥነ ቃሎች በአብዛኛው ከውበት፣ ከልምላሜና ከተስፋ ጋር እንደሚተሳሰሩም አጫውተውናል፡፡

በሀገራችን ለፍቅር፣ ለሀገር፣ ለቤተሰብና ለናፍቆት በርካታ ሙዚቃዎች ተሰርተዋል። ስለ ወርሃ መስረከም እና አዲስ ዓመትም እጅግ በርካታ ሙዚቃዎች ተቀንቅነዋል፡፡ ስለ ወርሃ ጥቅምት እና አበባ ከተሰሩ ሙዚቃዎች ውስጥ ደግሞ የአንጋፋው ሙዚቀኛ ነዋይ ደበበ “የጥቅምት አበባ” የተሰኘው ዘመን አይሽሬ ዘፈን በቀዳሚነት ይጠቀሳል። ሙዚቀኛው በዚህ የጥበብ ሥራው ጥቅምትን ህያው አድርጓታል፡፡ ወርሃ ጥቅምትን ከአበባና ከፍቅር ጋር አሰናኝቶ ዘመን ተሻጋሪ ጥዑም ዜማ አስደምጦናል።

“የጥቅምት አበባ፤ የጥቅምት አበባ፤
የጥቅምት አበባ ነሽ አሉ፤
አወድሸው አካሌን በሙሉ።
የጥቅምት አበባ፤ የጥቅምት አበባ፤
የጥቅምት አበባ ለሽታ
ለኔ ግን ጣልሽብኝ ትዝታ...”

እያለ ለተናፋቂዋ ፍቅሩ ያዜምላታል፡፡ በዚህ ውብ ሙዚቃ የጥቅምት አበባ የማትረሳ እና ሁልጊዜም የምትታወስ መሆኗን፣ የፍቅር ትዝታም እንደዛው መሆኑን ያቀነቅናል፡፡

ድምጻዊ ነዋይ ደበበ የናፈቃት ልጃገረድ እንደ ጥቅምት አበባ መላ አካሏን ታውዳለች፡፡ መንፈስን ታድሳለች። የናፈቃትን ውቧ አበባን ለመጎብኘት ‘እንደ ቢራቢሮ ክንፍ አውጥቼ ልምጣ ወይ?’ በማለት መናፈቁን ያዜምላታል። በሙዚቃው ከፍቅሩ ጋር ጠጋ ብሎ ለመወያየት ማረፊያ መፈለጉንም ያወጋናል፡፡

...“ማረፊያ አለ ወይ ፍቅርዬ
እንዳዋይሽ ሚስጥር ጠጋ ብዬ
የጥቅምት አበባ ነሽ
አካል ሰው ነይ ናፈኩሽ
ውበት መአዛሽ ለሽታ
ፍኪልኝ ልቤ ያግኝ ደስታ...“

በማለትም ጥቅምትና አበባን፣ እንዲሁም ፍቅርን በማዋሃድ በጥቅምት ወር ብቻም ሳይሆን በየትኛውም ወር እና ዘመን ተደማጭና ተወዳጅ ሙዚቃን አበርክቷል፡፡

ድምጻዊው ፍቅርና የጥቅምት አበባን፣ አንዱ ተወዶ አንዱን መጥላት እንደማይቻል፣ ተፈጥሮም በሃሴት፣ ተፈቃሪዋ ልጃገረድም በውበት የተሞላች መሆኗን በዘፈኑ አንጸባርቋል፡፡

## ጥቅምትን በሥነ ጽሑፍ

ጥቅምትና አበባ፣ ጥቅምትና ውበት፣ ጥቅምትና ተስፋን ካሰናኙ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች መካከል አንዱ የሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህን “እቴቴ ዱብራ አሮም” የተሰኘው ግጥሙ ይገኝበታል። በዚህ ግጥም ውስጥ የጥቅምትን ወር ውበት፣ ናፍቆትና እሸት እጅግ ድንቅ በሆኑ ቃላትና ስንኞች ገልጾታል፡፡

“...ተግ ሲል ያንቺ ሽውታ
ብኸ ሲል እንደ አድባር ጥሪ፣ እንደተርብ ቅርስ ሽታ
እንደ እሳት ዳር ተረት ግርሻ፣ እንደ እንቆቅልሽ ትውስታ
የጥቅምት እሸት አወደን፣ ነቃ ደሞ ያንቺ ትዝታ...
አውድማው ተንተረከከ
ሰንበሌጥ ተንተረከከ
ነይ አከርማ እንነቃቀል
ከወንዛችን ሾላ ጠለል
ነይ ጢሎሽ እንንጠላጠል
መስኮቻችን ሰብሎቻችን፥ ግጦሾቻችን አባቱ
የእቴቴ ላሞች አጋቱ
በሮቻችንም አጓሩ፣ ኮርማዎቻችንም ነቁ
ጊደሮቻችን ለጥቃት፣ ለይዘታ ለክብደት በቁ
የሁዳድ ድርቆሽ ሰፈር፣ ጥገቶቻችን ቦረቁ...

እያለ ጥቅምትን ስዕላዊ በሆነ፣ ወቅቱን በሚያስናፍቅና በትዝታ በሚያስረቀርቅ ቅኔ ከይኖታል፡፡

ጥቅምት በግጥም ብቻም ሳይሆን በአባባል እና በአጠቃላይ ፎክለርንም የሚገለጽ ወር ነው፡፡ ከአባባሎች ውስጥ በጣም ታዋቂው “በጥቅምት አንድ አጥንት” የሚለው ነው፡፡ የጥቅምት ወር ከልምላሜ ፀጋው በተጨማሪ በማለዳው ውርጭ፣ በምሽቱ ቅዝቃዜና በለሊቱ ቁርም ጭምር በደንብ ይታወቃል። እንዲሁም ቀን ቀን የሚወጣው ጠንከር ያለ ፀሐይም ሌላኛው የጥቅምት ወር መገለጫ ነው።

በተጨማሪም “የጥቅምት ማር፣ እሸት ይሸታል እጃችሁ
ያ’ገሬ ወጣቶች ተማሩ እባካችሁ፤

የሚለው ሥነ ቃልም የጥቅምት ወርን ከሚያስታውሱ፣ ወሩ የማርና እሸት ወቅት መሆኑን ከሚያመላክቱ ሥነ ቃሎች ውስጥ ተጠቃሽ ነው፡፡ ልክ ውብና ማራኪ፣ በተፈጥሮ ጸጋዎች እንደተሞላው ወርሃ ጥቅምት ሁሉ፤ ወጣቶችም ልዩ ስሜት ያላቸው፣ ደስ የሚሉ፣ በተስፋ የተሞሉ፣ መማር እና መመራመር እንዳለባቸውም የሚመክር አባባል ነው፡፡

ካህሳይ ገብረእግዚአብሔር የተባሉ ጸሐፊ በ2007 ዓ.ም ለንባብ ባበቁት፣ “ኅብረ ብዕር (የብዕር ዘመራ)” በተሰኘው መጽሐፋቸው ላይ እንደገለጹት ደግሞ ወርሃ ጥቅምት አዕዋፋት፣ ፍራፍሬ እና ጥራጥሬ እንደ ልባቸው እየተመገቡ በጋራም በተናጠልም የሚዘምሩበት፣ የቤት እንስሳት በየቃርሚያው የተረሳ እሸት በመብላት የሚሰበሰቡበት ወር መሆኑን ጽፈዋል፡፡

> “ከእሸት እና አበባ በተጨማሪ ጥቅምት የማር ወርም ነው፡፡ ‘ማርን መቁረጥ በጥቅምት’ የሚለው የሀገራችን ሥነ ቃል ለዚህ ማሳያ ነው”

እዚህጋ ማስታወስ የሚያስፈልገው ኢትዮጵያ ሰፊ መልክዐ ምድር፣ የተለያየ የአየር ንብረት ያላት እንደመሆኗ እሸት በተለያየ ጊዜም ሊኖር ይችላል፡፡ ለአብነትም በሀገራችን ቆላማ አካባቢዎች እሸት የሚደርሰው ከነሐሴ ወር አጋማሽ ጀምሮ ነው፡፡

ከእሸት እና አበባ በተጨማሪ ጥቅምት የማር ወርም ነው፡፡ “ማርን መቁረጥ በጥቅምት” የሚለው የሀገራችን ሥነ ቃል ለዚህ ማሳያ ነው ይላሉ፤ ደራሲ ካህሳይ ገብረእግዚአብሔር በመጽሐፋቸው፡፡ በእርግጥ ማር ከጥቅምት ሌላ በህዳርም ሆነ በሌሎች ወራት ይቆረጣል፡፡ ታዲያ ግን ከህዳር ሆነ ከሌሎች ወራት ማር ይልቅ የጥቅምት ማር መድኃኒትነት እንዳለው ይታመናል፡፡ በገጠራማው የኢትዮጵያ አንዳንድ አካባቢዎች ማር በተመቸ ቀን ብቻ አይቆረጥም፡፡ ከጥቅምት አጋማሽ በኋላ የአበባ ወቅት የሚያበቃበት፣ ቦታውን ለፍሬ የሚያስረክብበት ቀን ነው ተብሎ በሚታመንበት ሰሞን ማር መቁረጥ የተለመደ መሆኑንም ደራሲ ካህሳይ በመጽሐፋቸው አስፍረዋል፡፡

በአጠቃላይ ጥቅምት ኪነ ጥበባዊ፣ ፎክሎራዊ፣ ተፈጥሯዊና ሌሎችንም መልኮች የያዘ ነው፡፡ በዚህም የጥቅምት ወር በተለያዩ አካባቢዎች በሚኖሩ የሀገራችን ማህበረሰቦች ዘንድ ልዩ ስፍራ የሚሰጠውም ነው፡፡ በውበቱ፣ በልምላሜውና ተስፋን በመቸሩ ምክንያት ወርሃ ጥቅምት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተወዳጁ ወር ሆኗል፡፡

## የጠዋት ፀሐይ

# ተማሪዎች የትምህርት ግብዓቶችን ማግኘታቸው ምን ስሜት ፈጠረባቸው?

**በለይላ መሀመድ**

ልጆች እንዴት ከረማችሁ? ትምህርት እንዴት ነው? “አሪፍ ነው” እንደምትሉ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ልጆች ውጤታችሁ እጅግ በጣም ጥሩ እንዲሆን የትምህርት ግብዓት አሟልቶ መማር ዋነኛው ነው አይደል? እናንተስ የትምህርት ግብዓት ተሟልቶላችኋል? በመሟላቱ ምን ተሰማችሁ?

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየዓመቱ ለመንግስት ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቁሳቁስ እና የተማሪ የደንብ ልብስ ያቀርባል፡፡ ዘንድሮም በ2018 የትምህርት ዘመንም ለተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ እና የተማሪዎች የደንብ ልብስ አቅርቧል፡፡ እኛም በዛሬው ዕትማችን በመህል ግንፍሌ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲሁም በመስከረም ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመሄድ በትምህርት ቤቶቻቸው በኩል የቀረበው የትምህርት ቁሳቁስ እና የትምህርት የደንብ ልብስ መሰጠቱ በተማሪዎቹ ላይ የፈጠረውን ስሜት፣ በትምህርታቸው ጎበዝ እንዲሆኑ ምን እገዛ እንዳደረገላቸው ተማሪዎችንና ርዕሰ መምህራንን አነጋግረናል፡፡

ስሜ ተማሪ እድላዊት ድረስ ይባላል። በመህል ግንፍሌ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የ4ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ። ትምህርት ቤታችን ደብተር፣ መጽሐፍ እና የደንብ ልብስ ሰጥቶናል። መጽሐፍ የተሰጠኝ ክረምት ላይ ስመዘገብ ነው፡፡ ደብተር ደግሞ ትምህርት እንደተጀመረ ነው፡፡ በዚህም በጣም ደስተኛ ነኝ። በተለይ መጽሐፍ ቀድሞ መሰጠቱ የ4ኛ ክፍል ትምህርት ምን እንደሚመስል ቀድሜ በማንበብ እንዳውቀው አድርጎኛል። አዲስ የደንብ ልብስ ስለተሰጠኝም ደስ ብሎኛል። እነዚህ የትምህርት ቁሳቁሶች ተሟልተው መሰጠታቸው በትምህርቴ ጎበዝ እንድሆን ያደርገኛል፡፡

ተማሪ የማሪያም ኃይለእግዚአብሄር እባላለሁ። የምማረው በመህል ግንፍሌ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። የ4ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ። ከትምህርት ቤቴ በቂ የሆነ ደብተር፣ ሁሉም አይነት መጽሐፍት ተሰጥቶኛል። እነዚህ የትምህርት ቁሳቁሶች ተሰጥተውኝ መማሬ ደስታን ፈጥሮልኛል፡፡ ሁሉም ስለተሟላልኝ በትምህርቴ ጥሩ ውጤት እንደማመጣ እተማመናለሁ፡፡

በመህል ግንፍሌ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የመማር ማስተማር ምክትል ርዕሰ መምህር ቅርስነሽ የማነብርሀን በሰጡት አስተያየት፤ “መንግስት ለተማሪዎች ግብዓት ማሟላቱ ተማሪዎች የበታችነት ስሜት ሳይሰማቸውና ሳይሳቀቁ እንዲማሩ አድርጓቸዋል፡፡ ተማሪዎች ‘ደብተር አልተሟላልኝም፤ ደንብ ልብስ አልተገዛልኝም፡፡’ ሳይሉ እየተማሩ ይገኛሉ፡፡ በዚህም የሚያረፍድና የሚያቋርጥ ተማሪ የለም፡፡ የተማሪዎች ውጤትም ተሻሽሏል፡፡ በትምህርት ቤትም የመማር ማስተማር ሂደቱ ጥሩ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ይህ በመንግስት የተጀመረው የቁሳቁስ ድጋፍ ከመምጣቱ በፊት አንዱ ጥሩ ለብሶ ሲመጣ ሌላው የተቀደደ ልብስ ስለሚለብስ ተማሪዎች ላይ የሥነ ልቦና ጫና ያሳድር ነበር። የደንብ ልብሱ ልጆች እኩል ሆነው እንዲታዩ ያደርጋቸዋል፡፡ ተማሪዎችም ትምህርታቸው ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው እንዲማሩ እድል ፈጥሮላቸዋል” ብለዋል፡፡



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል
አስተያየት የሰጡ ተማሪዎች

ስሜ ተማሪ እሌኒ ይዘልቃል ይባላል። በመስከረም ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ8ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ ደብተር፣ መጽሐፍ እና የደንብ ልብስ በነጻ ተሰጥቶኝ መማር መቻሌ ደስተኛ አድርጎኛል፡፡ የተሻለ ውጤት ለማምጣትም ከፍተኛ እገዛ ያደርግልኛል፡፡ በተለይም መጽሐፍ የተሰጠኝ ክረምት ላይ በመሆኑ በክፍል ውስጥ በሚሰጠው ትምህርት ላይ በጥሩ ሁኔታ እንድሳተፍ አግዞኛል። በተጨማሪም የ8ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናን በስኬት ለማለፍ እንደሚጠቅመኝ አምናለሁ፡፡

ቀደም ሲል እስከ 5ኛ ክፍል ድረስ የተማርኩት በግል ትምህርት ቤት ነበር። የደረጃ ተማሪ አልነበርኩም። ደብተር፣ መጽሐፍ እና የደንብ ልብስ በግላችን እንገዛ ስለነበር ብዙውን ጊዜ ቤተሰቦቼ ማሟላት ይቸገሩ ነበር በተለይም በመጽሐፍ ረገድ የሚገዙልኝ የተወሰኑትን የትምህርት አይነቶች ብቻ እንጅ ሁሉም አይገዛም ነበር፡፡ የመንግስት ትምህርት ቤት መማር ከጀመርኩ ወዲህ ግን ሁሉንም መጽሐፍ በማግኘቴ የደረጃ ተማሪ ሆኛለሁ፡፡ ወደ መንግስት ትምህርት ቤት ከመጣሁ ጀምሮ መጽሐፍ ክረምት ላይ ስለሚሰጡን በደንብ እየተዘጋጀሁ እንዳልፍ አድርጎኛል፡፡

ተማሪ ቃለአብ አየለ በተመሳሳይ በመስከረም ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ8ኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡ እሱም የሚከተለውን አስተያየት ሰጥቷል፡፡ ሁሉንም የትምህርት ቁሳቁሶች ተሰጥቶኝ በመማሬ ትምህርቴ ላይ የተሻለ መረዳት እንዲኖረኝ ጠቅሞኛል፡፡ ከስር ከስር መጽሐፍ ውስጥ ያሉ መልመጃዎችን እየሠራሁ በመሄድ ጥሩ ውጤት ለማምጣት እየጣርኩ ነው። መጽሐፍ ለማጥናት በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ በመንግስት ትምህርት ቤት መማር ከጀመርኩ ወዲህ የደረጃ ተማሪ ለመሆን በቅቻለሁ፡፡

የመስከረም ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ርዕሰ መምህር ዳዊት ጉባው በበኩላቸው፤ በመንግስት በኩል እየተደረገ ያለው የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ ተማሪዎች ትምህርታቸው ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ በማድረግ ለትምህርት ጥራት ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል፤ እያበረከተም ነው፡፡ በተለይም በበጀት ዓመቱ ግብአቶች ቀድመው በመምጣታቸው ተማሪዎች በጥሩ ዝግጅት ትምህርታቸውን እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡ መጠነ ማቋረጥም ቀንሷል፡፡

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ግንዱ ወደ ላይ ባላው ወደታች**

**መልስ፡-** ለ. ሰው

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ከነጭ ቆዳ ቆሻሻ የሚያወጣ**

ሀ. ላጲስ
ለ. መጥረጊያ
ሐ. መወልወያ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ፡፡**

**ከተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ**

# የኮሌጁ የአዳዲስ ሰልጣኞች ቅበላ ዝግጅት

- **በትምህርትና ስልጠና ዓመቱ 1 ሺህ 698 አዳዲስ ሰልጣኞችን ለመቀበል ተዘጋጅቷል**

**በለይላ መሀመድ**

እድሜ ጠገቡ የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ከተቋቋመ ከ100 ዓመታት በላይ ሆኖታል፡፡ በሚያዝያ 19 ቀን 1917 ዓ.ም ተመርቆ የተከፈተውና በኢትዮጵያ የዘመናዊ ትምህርት ስልጠና ታሪክ ቀደምት ስፍራ ካላቸው ተቋማት ውስጥ የሚመደበው የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ብዙዎችን የቀለም ቀንድና የሙያ ባለቤት እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ ከተቋቋመበት ግዜ እና ካለው እድሜው በተለያዩ ዘርፎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ዜጎች በማስተማርና በማሰልጠን ኢትዮጵያ በተለያዩ ወቅቶች ለነበሯት የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማኅበራዊ ጉዳዮች ምላሽ የሚሰጡ ባለሙያዎችንም አፍርቷል፡፡




ፎቶ- በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ

ሰልጣኞች በሰለጠኑበት የሙያ መስክ የተግባር ልምምድ ሲያደርጉ

ኮሌጁ ዛሬም ኃላፊነቱን ከመወጣት አልቦዘነም፡፡ አሁንም ለብዙዎች ሠርተው ከዕውቀታቸው እና ክህሎታቸው እንዲቋደሱ የሚጠበቅበትን ያለስስት እየቸረ ይገኛል፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ሙያን መሰረት ያደረገ ትምህርትና ስልጠና ለማህበረሰቡ የማዳረስ ዓላማን አንግቦ ብዙዎችን የሙያ ባለቤት ለማድረግ ብርቱ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። ኮሌጁ ትኩረቱን ገበያው የሚፈልገው የሙያ መስኮች ላይ በማድረግ በተግባር እና በንድፈ ሀሳብ የተደገፉ ዘርፈ ብዙ የስልጠና አይነቶችን ሲሰጥ ቆይቷል፤ በመስጠት ላይም ይገኛል፡፡

የዘንድሮ የ2018 የትምህርት ዘመን የትምህርትና ስልጠና እቅዱ ምን እንደሚመስል የዝግጅት ክፍላችን በኮሌጁ የሬጅስትራር ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ስመኝ ሚደቅሳን አነጋግሯቸዋል። እንደ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ገለጻ፤ ኮሌጁ የቴክኒክና ሙያ ዘርፎች ላይ አተኩሮ ማሰልጠን የጀመረው ከ1994 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ጀምሮ ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ የሙያ መስኮች በመደበኛ፣ በቅዳሜና እሑድ እንዲሁም በአጫጭር ስልጠናዎች በርካታ ሙያተኞችን አሰልጥኖ አስመርቋል። ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸው፣ ለአካባቢያቸውና ለሀገራቸው የሚጠቅሙ ዜጎችም ሆነዋል።

የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ በ2018 በጀት ዓመት በ10 የስልጠና ዘርፎች አዳዲስ ሰልጣኞችን ለመቀበል ቅድመ ዝግጅት እያደረገ ይገኛል። እነዚህም የስልጠና መስኮች በሥነ ጥበብ (ኤስቴቲክስ)፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በአውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ፣ በቴክስታይል እና ጋርመንት፣ በኤሌክትሪካል ኤሌክትሮኒክስ፣ በሆቴል ሰርቪስና ቱሪዝም፣ በኮንስትራክሽን፣ በቢዝነስና ፋይናንስ፣ በእንጨትና ብረታ ብረት ቴክኖሎጂ እንዲሁም በከተማ ግብርና የሙያ ዘርፎች ናቸው። እነዚህ የሙያ ዘርፎችም በውስጣቸው 43 የሚጠጉ ንዑስ የስልጠና ክፍሎች አሏቸው፡፡

ስልጠና ከሚሰጥባቸው የሙያ መስኮች መካከል ሥነ ጥበብ (ኤስቴቲክስ) በከተማ ደረጃ ከሚገኙ መሰል ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች በተለየ የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ብቸኛው የስልጠና ማዕከል ነው። በዚህ ሙያ ብቸኛ የስልጠና ማዕከል የሆነበት ምክንያት በዘርፉ ሰፊ ልምድ በማካበቱና ለስልጠናው ምቹ በመሆኑ ነው፡፡ ኮሌጁ በዚህ በኪነ ጥበብ ዘርፍ እንደ ከተማና ሀገር አልፎ ተርፎም በዓለም እውቅናን ያገኙ በርካታ አርቲስቶችን አፍርቷል፡፡ ከእነዚህ መካከል፤ ድምፃዊ እሱባለው ይታየው፣ አርቲስት ዳንኤል ተገኝ፣ ኤሊያስ ሽታሁን እና ሌሎችንም አፍርቷል፡፡

እንደ ጽህፈት ቤት ኃላፊው ገለጻ፤ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ የአዳዲስ ሰልጣኞች ቅበላ የሚያደርግባቸውን የስልጠና ዘርፎችንም ለማስተዋወቅ የተለያዩ አማራጮችን ተጠቅሞ እየሠራ ይገኛል። ከእነዚህም መካከል ብሮሸር እና ባነር በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ግንዛቤ እየተፈጠረ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ለመሰልጠን ፍላጎት ኖሯቸው ወደ ኮሌጁ ለሚመጡ ሰልጣኞች፤ ስለኮሌጁ እና ስለሚሰጣቸው የስልጠና ዘርፎች በባለሙያዎች የተደገፈ ዝርዝር ገለጻ ይሰጣል፡፡

ብቃት ያላቸውን ሰልጣኞች ለማፍራት ይቻል ዘንድ ከስልጠና ቁሳቁስና ብቁ አሰልጣኞችን ዝግጁ ከማድረግ አንጻር የዝግጅት ክፍሉ ለጽህፈት ቤት ኃላፊው ላነሳላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ አዲስ ብቻ ሳይሆን የነባር ተማሪዎችንም የስልጠና ሂደት የተሻለና ብቁ ለማድረግ የተግባር ስልጠና መስጫ ቦታዎች ወይንም ወርክ ሾፖች ዝግጅት ምንጊዜም ትኩረት ተሰጥቶት ይሰራል፡፡ በዚህ የትምህርት ዘመንም ይኸው ተግባር በትኩረት ተከናውኗል፡፡ በኮሌጁ ያሉ የተግባር ስልጠና መከታተያ ቦታዎች (ወርክ ሾፖች) በአስፈላጊ ማሽንና ግብዓት የተሟሉ ናቸው፡፡

> በስልጠናው ብቃት ያላቸው ዜጎችን በማፍራት ረገድ በወርክ ሾፖቹ ጥገና የሚያስፈልጋቸውን ማሽኖች የማስጠገንና ለስልጠና የሚያገለግሉ ግብአቶችም የማሟላት ሥራ እየተሠራ ነው

በስልጠናው ብቃት ያላቸው ዜጎችን በማፍራት ረገድ በወርክ ሾፖቹ ጥገና የሚያስፈልጋቸውን ማሽኖች የማስጠገንና ለስልጠና የሚያገለግሉ ግብአቶችም የማሟላት ሥራ እየተሠራ ነው፡፡ በየትኛውም አይነት የስልጠና ዘርፍ የሚሰጡ ስልጠናዎች ተግባር ተኮር በመሆናቸው እያንዳንዱን ግብአት ማሟላት አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ ቴክስታይል ጋርመንት የስልጠና ዘርፎች ላይ ጨርቆችን በዲዛይን ቆራርጦ ለመስፋት የሚያገለግሉ ማሽኖች እንደ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ያስፈልጋሉ። ይህንን ማሽን ኮሌጁ ለማሟላት እየሠራ ነው። የማሰልጠኛ ቁሳቁስና ወርክ ሾፖች ዝግጁ ከማድረግ ባለፈም ብቃት ያላቸው አሰልጣኞች በኮሌጁ አሉ። በሁሉም የስልጠና ዘርፎች ላይ የሚገኙ አሰልጣኞች ለአሰልጣኝነት የሚያበቃ የተሟላ የትምህርት ዝግጅት አላቸው። በተጨማሪም የብቃት ማረጋገጫ ሲኦሲ ተፈትነው ያለፉና ብቁ የሆኑ ናቸው፡፡

የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በ2018 የትምህርት ዘመን አዳዲስ ሰልጣኞችን ለስልጠና የመቀበል አቅሙ 1 ሺህ 698 እንደሆነ በኮሌጁ የሬጅስትራር ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ስመኝ ሚደቅሳ ተናግረዋል፡፡ እንደሳቸው ገለፃ፤ ኮሌጁ ወደ ተግባር የሚገባው ከከተማ አስተዳደሩ በሚሰጠው እቅድ መሰረት በመሆኑ እቅዱ እስኪመጣ ድረስ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡ ኮሌጁ ቅበላ የሚጀምረው የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውጤት ከወጣ በኋላ የቴክኒክና ሙያ መግቢያ ውጤት ከስራና ክህሎት ሚኒስቴር ሲለቀቅ ነው፡፡

የጽህፈት ቤት ኃላፊው አክለው እንዳብራሩት፤ በዘንድሮው የትምህርትና ስልጠና ዘመን በኮሌጁ የሚሰጡ የስልጠና መርሃ ግብሮች በሦስት አይነት መልኩ የሚቀርቡ ናቸው፡፡ እነዚህም በቀን፣ በማታ እንዲሁም ቅዳሜና እሑድ በሚል የተከፋፈሉ ናቸው፡፡ በ2018 የትምህርትና ስልጠና ዘመን ምዝገባ የሚከናወነው በኦንላይን ሲሆን፤ ምዝገባው ሳይስተጓጎል እንዲካሄድ የሚያደርግ ሲስተም በልጽጓል፡፡ ማንኛውም የስልጠና ፍላጎት ያለው ግለሰብ እቤቱ ሆኖ በስልኩ የኮሌጁ ዌብሳይት ላይ በመግባት መመዝገብ የሚችልበትን ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡

በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የሚሰጠውን ስልጠና ደረጃ በተመለከተ አቶ ስመኝ እንደተናገሩት፤ ለሰልጣች የሚሰጠው የስልጠና ደረጃው እንደየስልጠና ዘርፎቹ የሚለያይ ቢሆንም፤ ስልጠናው ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ አምስት ድረስ በመስጠት ብቁና ተወዳዳሪ ሰልጣኞችን የማፍራት ሥራ ይሠራል፡፡ ለምሳሌ ከቴክስታይል ጋርመንት የስራ ክፍል መካከል በፋሽን ዲዛይን የስልጠና መስክ ከደረጃ ሁለት እስከ ደረጃ አምስት ድረስ ነው የሚሰጠው፡፡

ኮሌጁ ወጣቶችን የተለያዩ የሙያ ባለቤት እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ ያለውን አበርክቶ ምንድነው? ስንል የጽህፈት ቤት ኃላፊው አቶ ስመኝን ጠይቀናቸዋል። በምላሻቸውም፤ በከተማዋ በተለያዩ የልማት ስራዎች ለአብነትም በኮሪደር ልማቱ በርካታ በኮሌጁ የሰለጠኑ ዜጎች ተሳትፈዋል፡፡ ሰልጣኞች ኢንተርፕሪነር ሆነው በግላቸውና ተደራጅተው እንዲሰሩ ኮሌጁ ለማበረታታት በግቢው ሼዶች ይሰጣቸዋል፡፡ በሚሰጣቸው ሼዶችም ራሳቸውን የበለጠ አብቅተው እንዲወጡና ውጪ ሲወጡ የበለጠ ተዋዳዳሪ የሚሆኑበትን እድል ማመቻቸት በመቻሉ በልማት ስራዎች ላይ ተሳታፊ መሆን የቻሉት፡፡

የጽህፈት ቤት ኃላፊው፤ ረጅም እድሜና ሰፊ ልምድ ያለው ተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ሰልጣኞችን ተቀብሎ ለማሰልጠን ዝግጅቱን አጠናቅቋል። ጥራት ባለው መልኩ የሙያ ባለቤት ለመሆን የምትፈልጉ ሰልጣኞች ኑ ሰልጥኑ ሲሉም መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# በአዲስ መልክ እየተገነባ ያለው የፍል ውሃ - አሮጌው ቄራ መንገድ



ከመንገዶች ባለስልጣን

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ እየሰራቸው ካሉ  የፍል ውሃ - አሮጌው ቄራ መንገድ  እና ከአምባሳደር ቴአትር ወደ አራት ኪሎ አካባቢ ለሚጓዙ አሽከርካሪዎች አቋራጭ መንገድ ስራ በከፊል

**ሳምሶን ዮሐንስ (ከመንገዶች ባለስልጣን)**

የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን በመንገድ እና ተያያዥ መሰረተ ልማቶች ግንባታ፣ ጥገናና አስተዳደር የከተማችንን ህዝብ ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ የሚገኝ ተቋም ነው፡፡ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የከተማዋን መንገዶች ለትራፊክ ፍሰት ምቹ ለማድረግ ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል ነባር መንገዶችን መልሶ በማሻሻል የመገንባት ሥራ ተጠቃሽ ነው፡፡

በተያዘው በጀት ዓመት 214 ነጥብ 51 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን መንገድ ለመገንባት በዕቅድ ይዞ እየሰራ የሚገኘው ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በአሁኑ ወቅት እየገነባቸው ካሉ የመንገድ ፕሮጀክቶች መካከል የፍልውሃ - አሮጌው ቄራ መንገድ ይገኝበታል፡፡ ይህ መንገድ ከአምባሳደር ቴአትር ወደ አራት ኪሎ አካባቢ ለሚጓዙ አሽከርካሪዎች አቋራጭ መንገድ ሆኖ ለዘመናት ሲያገለግል የኖረ ነው፡፡ በተጨማሪም ከጥቁር አንበሳ እና ከዋናው ፖስታ ቤት አካባቢ ወደ አራት ኪሎ ለሚያልፉ ተጠቃሚዎች ሲያገለግል ኖሯል፡፡ ከፍል ውሀ አካባቢ ተነስቶ ወዳጅነት ፓርክን ወደ ቀኝ፣ አልማ ጋራዥን ወደ ግራ በመተው በንግድ ማተሚያ ቤት በኩል የሚያልፈው ይህ መንገድ፤ አራት ኪሎ ቱሪስት ሆቴል አሊያም ደግሞ ወደ ታላቁ ቤተ-መንግስትና ፓርላማ ለመጓዝ የሚያስችል ነው፡፡

ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ በመልሶ ግንባታ ደረጃ እየገነባው የሚገኘው ይህ ነባር መንገድ 1 ነጥብ 5 ኪሎ ሜትር ርዝመት እና በአማካኝ ከ20 እስከ 30 ሜትር የጎን ስፋት የሚሸፍን ሲሆን፤ የተሽከርካሪ መተላለፊያ የአስፋልት መንገድ፣ የብስክሌት እና የእግረኛ መንገዶችን የሚያካትት ነው፡፡

“ቀደም ሲል የነበረው የፍል ውሀ አሮጌ ቄራ መንገድ፤ ጠባብና የእግረኛ መንገድ ያልነበረው በመሆኑ በአካባቢው በሚደረግ የትራፊክ እንቅስቃሴ ላይ መጨናነቅ ይስተዋል ነበር” የሚሉት በአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ ኢንጅነር ቢንያም አለማየሁ፤ በአዲስ መልክ የሚገነባው መንገድ፤ ከዋናው መንገድ በተጨማሪ የብስክሌት እና የእግረኛ መንገድ ባካተተ መልኩ የሚገነባ መሆኑን ነው የተናገሩት ፡፡

“አሮጌው መንገድ ከ7 ሜትር የማይበልጥ ስፋት የነበረው ሲሆን እግረኛውም ተሽከርካሪውም በአንድ ላይ ይስተናገድበት የነበረ ነው፡፡ አሁን ላይ ዋናው መንገድ ከ20-30 ሜትር ስፋት እንዲኖረው ተደርጎ እየተሰራ መሆኑ ለየት ያደርገዋል” ብለዋል፡፡

ኢንጅነር ቢንያም፤ የመንገድ ፕሮጀክቱ በሁለት ምዕራፍ ተከፍሎ የሚገነባ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ “የመንገዱ ግንባታ በሁለት ምዕራፍ ነው የሚካሄደው። በ2017 ዓ.ም የተጀመረውና ከአልማ ጋራዥ እስከ ውዳሴ ያለው 600 ሜትር ርዝመትና 20 ሜትር ስፋት ያለው የመንገዱ ክፍል የመልሶ ግንባታ ሥራ እየተከናወነ ሲሆን አሁን ላይ በከፊል የአስፋልት ሥራ ተጠናቅቋል፡፡

በ2017 በጀት ዓመት የካቲት ወር የተጀመረው የፕሮጀክቱ የመጀመሪያ ክፍል መልሶ ግንባታ በአዲሱ የበጀት ዓመት ጥር ወር ላይ ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ እንደ ኢንጅነር ቢንያም ገለፃ ፕሮጀክቱ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ ከፍል ውሀ ወደ አራት ኪሎ እና አካባቢው ለሚጓዙ አሽከርካሪዎች ምቹ አማራጭ መንገድ በመሆን የትራፊክ ፍሰቱን የተሳለጠ ያደርገዋል፡፡

በአካባቢው መንግስታዊ ተቋማት የሚገኙ ሲሆን፤ ሪልስቴት የሚገነቡ ድርጅቶችም የመኖሪያ ህንፃዎችን እየገነቡ ነው፡፡ የመንገዱ ቀድሞ መሰራት ሪልስቴቶቹ ተጠናቅቀው ነዋሪዎች በሚገቡበት ወቅት በአካባቢው የተሳለጠ የትራፊክ ፍሰት የሚኖር በመሆኑ ለአካባቢው ነዋሪዎች ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥርም ነው የገለፁት፡፡

ከትራፊክ ፍሰት አንፃር መንገዱ ከለገሀር ወይም ከብሔራዊ አካባቢ ተነስቶ ወደ ፒያሳ ከሚወስደው መንገድ ጋር ትይዩ በመሆኑ በዋናው መንገድ ላይ የትራፊክ መጨናነቅ በሚፈጠርበት ጊዜ አማራጭ መንገድ ሆኖ የሚያገለግል ይሆናል፡፡

እስካሁን ከተጠናቀቀው የአስፋልት መንገድ በተጨማሪ 320 ሜትር የአፈር ቆረጣ ገረጋንቲ ሙሌት የተካሄደ ሲሆን፤ 160 ሜትር የሳይክልና የመሮጫ ትራክ፣ 160 ሜትር ሰብቤዝና ቤዝ ኮርስ ሥራ እንዲሁም 200 ሜትር ለውሀ፣ ለቴሌኮም እና ኤሌክትሪክ መስመሮች የሚያገለግል ፒፒሲ የመቅበር ሥራ ተከናውኗል፡፡

በሌላም በኩል የእግረኛ መንገድ ዝግጅትና ግራናይት የማንጠፍ ሥራ እንዲሁም የዝናብ ውሃ መፋሰሻ መስመር ቱቦ ቀበራ፣ የከርቭስቶን ስራ፣ የማንሆል ክዳን፣ የሰቤዝና ቤዝ ኮርስ ስራዎች በመከናወን ላይ መሆናቸውንም ኢንጅነር ቢንያም ይናገራሉ፡፡

ከፍል ውሀ - አሮጌ ቄራ የሚካሄደውን የመንገድ መልሶ ግንባታ ፕሮጀክት የመጀመሪያው ክፍል በተሻለ ፍጥነት እና ጥራት በማከናወን በተያዘው በጀት ዓመት ጥር ወር ላይ ለማጠናቀቅ እየሰራን ነው የሚሉት ኢንጅነር ቢንያም በአሁኑ ወቅት ግንባታው እየተፋጠነ መሆኑን ነው የሚናገሩት፡፡

የመንገዱ ግንባታ ሲጠናቀቅ ከፍል ውሃ ወደ አራት ኪሎና አካባቢው ለሚጓዙ አሽከርካሪዎች አቋራጭና አማራጭ መንገድ በመሆን የሚያገልግል ይሆናል፡፡ በእዚህ አካባቢ ያሉ የሪልስቴት አልሚዎች የመንገድ ጥያቄ እንደነበራቸው የሚያስታወሱት ኢንጅነር ቢንያም “የከተማ አስተዳደሩ በአንድ በኩል በየአካባቢው ያለውን የመንገድ ጥያቄ ከመመለስ አንፃር በሌላም በኩል አማራጭ መንገዶችን በመገንባት በዋና መንገዶች ላይ የሚፈጠረውን መጨናነቅ ለመቀነስ አቅዶ የገባበት ሥራ በመሆኑ የባለስልጣን መ/ቤቱ ከፍተኛ አመራሮችን ጨምሮ ለፕሮጀክቱ ትኩረት በመስጠት ሥራዎችን እየሠራን ነው፤ ይሄ መንገድ ተሰርቶ ሲጠናቀቅ አጠቃላይ የአካባቢውን ሁኔታ የሚለውጥ ይሆናል”ብለዋል፡፡

**ከፍል ውሃ- አሮጌው ቄራ የሚካሄደውን የመንገድ መልሶ ግንባታ ፕሮጀክት የመጀመሪያው ክፍል በተሻለ ፍጥነት እና ጥራት በማከናወን በተያዘው በጀት ዓመት ጥር ወር ለማጠናቀቅ እየተሰራ ነው**

“የመንገድ ግንባታው መጠናቀቅ ለህብረተሰቡ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው የጎላ ነው” የሚሉት ኢንጅነር ቢንያም ከከተማ ህዝብ ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ የሚመጣውን የመንገድ መሠረተ ልማት ጥያቄ ለመመለስ እና በከተሞች ውስጥ ቀልጣፋ የትራፊክ እንቅስቃሴ እንዲኖር ለማስቻል የሚተገበር የተቀናጀ የከተማ ፕላን ወሳኝ አካል መሆኑንም ነው የገለፁት፡፡

ከፍል ውሀ ተነስቶ እስከ አልማ ጋራዥ የሚደርሰው ሁለተኛው የፕሮጀክቱ ክፍል፤ የመጀመሪያው ምዕራፍ እንደተጠናቀቀ ግንባታው ይጀምራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ መንገዶች ምቹና ዘመናዊ ሆነው መገንባታቸው የተገልጋዩን ህብረተሰብ የመሰረተ ልማት ጥያቄ ከመመለሳቸው በተጨማሪም በአካባቢው የከተማችንን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በማሳደግ ረገድ የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑን የሚናገሩት እንጂነር ቢንያም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ይህንን ፕሮጀክት በተቻለ ፍጥነት በማጠናቀቅ ለአገልግሎት ክፍት ለማድረግ እየሰራ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

# ከበጎ ልብ የሚፈልቅ በጎነት

## “በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ጥሩ ተሳትፎ ያለው ሰው ጤናማ ህይወትን ለመምራት አያዳግተውም”

የስነ ልቦና አማካሪ ማስረሻ ገ/መድህን (ዶ/ር)

**በሄለን ጥላሁን**

ወይዘሮ አልማዝ ገብረየስ ይባላሉ፡፡ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 ነዋሪ ናቸው። እድሜያቸውም በሃምሳዎቹ መጀመሪያ አካባቢ ነው፡፡ በማህበራዊ ኃላፊነቶች ላይ በንቃት የመሳተፍ ልምድም አላቸው፡፡ የትራፊክ እንቅስቃሴን በማስተናበር ሥራ ላይ ያዘወትራሉ፡፡ ለዚህ ምክንያታቸው ደግሞ፤ በተለምዶ ሽሮሜዳ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ የሚገኘው እንጦጦ አምባ ትምህርት ቤት ፊት ለፊት የደረሰ አስከፊ የትራፊክ አደጋ የፈጠረባቸው ስሜት ነው፡፡

በሽሮ ሜዳ እና በአካባቢው ላይ የሚንቀሳቀሱ እግረኞች እና አሽከርካሪዎች የትራፊክ ህግና መርህን በጠበቀ እና ስነ ምግባርን በተላበሰ ሁኔታ የመንገድ መሰረተ ልማትን እንዲጠቀሙ በሚያደርጉት የበጎ አድራጎት ሥራ አበረታች ግብረ መልስ እንደሚሰጧቸው ወይዘሮ አልማዝ ይናገራሉ፡፡ ታዛዥ እንደሚሆኑላቸው ጭምር ገልፀዋል። በኮሪደር ልማት አማካኝነት የተለዩ የእግረኛ፣ የሳይክል እንዲሁም የመኪና መንገዶች ለአገልግሎት መብቃታቸው የትራፊክ እንቅስቃሴው ወደ ጥሩ መስመር እንዲገባ አድርጓል፡፡ በእነዚህ መሰረተ ልማቶች ሁሉም እንደየፈርጁ አውቆ እንዲጠቀምባቸው እና የእለት ተዕለት ልምድ እንዲያደርገው የበኩላቸውን ኃላፊነት እየተወጡ እንደሚገኙ ጭምር አብራርተዋል፡፡

ወይዘሮ አልማዝ በዚህ አገልግሎታቸው ከጉለሌ ክፍለ ከተማ የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ዕውቅና ተሰጥቷቸዋል፡፡ ይህ ዕውቅና ለበለጠ አገልግሎት አነሳስቶአቸው ሠላሳ የሚሆኑ በጎ ፍቃደኛ ተማሪዎችንና ወጣቶችን በማሰባሰብ፣ አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ እና ስልጠና እንዲወስዱ በማመቻቸት በክረምቱ ወቅት እንዲያገለግሉ ማድረጋቸውንም ገልፀዋል፡፡

“ከማህበረሰቡ የሚሰጠን አስተያየት እንድንበረታታ እና በይበልጥ እንድንሠራ ያደርገናል” የሚሉት ወይዘሮዋ፤ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ቅድሚያ መስጠትን እንደመርህ በመያዝ የሚተገብሩት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ዋና የአስፋልት መንገድ መሻገር የሚፈልጉ አካል ጉዳተኞችን የተለየ ድጋፍ በማድረግ እያስተናገዱ ሲሆን ከእነዚህ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚያገኙት ምላሽ እና ምርቃት ከስጋ አልፎ ነፍስ ድረስ የሚዘልቅ መሆኑንም አልሸሸጉም፡፡

“በጎነት ለራስ የሚከፈል መስዋዕትነት ነው፡፡ እኛም አቅማችን ሲከዳን፣ ጤናችን ሲጓደል ቤታችንን የሚያቃናልን፣ መንገድ የሚያሻግረን ያስፈልገናል፡፡ የምንሠራው ሥራ የሚያስገኝልን የህሊና እርካታ እንዲህ በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም፡፡ ልክ ቤታችን ገብተን አረፍ ስንል፣ ያሳለፍነውን በጎ ቀን በማሰብ ፈገግ ብለን እንድናመሽ፤ አዳራችንም ሰላማዊና የደስታ እንዲሆን ይረዳናል” ሲሉ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ያለው ፋይዳ በዋጋ የማይተመን መሆኑን አብራርተዋል፡፡


ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል
የትራፊክ እንቅስቃሴ በማስተናበር ስራ የተሰማሩ በጎ ፍቃደኞች በስራ ላይ

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ነዋሪ የሆነው ወጣት ለማ ታደሰ፤ በተለያዩ የበጎ ፍቃድ ሥራዎች ላይ ተሳትፎ የማድረግ ልምድ አለው፡፡ በተለይ በቤት እድሳት ላይ ላለፉት አራት ዓመታት ጉልበቱን ሳይሰስት ተሳትፏል፡፡ እሱ በተሳተፈባቸው በጎ ሥራዎች አማካኝነት 16 የሚሆኑ የአቅመ ደካማ ቤቶች ዕድሳት ተደርጎላቸው ለተጠቃሚዎች መተላለፋቸውን ያስታውሳል፡፡ ይህንን መሰል ተግባር ላይ በመሳተፉ ከፍተኛ የሕሊና እርካታ እንደሚሰጠው ጠቁሟል።

ወጣት ለማ እንደገለፀው፤ በ2017 የክረምት የበጎ ፈቃድ መርሃ ግብር ሙሉ ጊዜውን የአቅመ ደካሞችን ቤት በማደስ፣ በትራፊክ ማስተናበር እንዲሁም በደም ልገሳ መርሃ ግብር ላይ ለመሳተፍ ችሏል። በበጋ መርሃ ግብር ላይ እንዲሁ ይህንኑ ተግባር አጠናክሮ ለመቀጠል ተዘጋጅቷል። በጎ ተግባር በመስራት ውስጥ የሚገኘው የህሊና ሰላም የትኛውንም ተግባር ከውነን ከምናገኘው እርካታ በእጅጉ የላቀ ነው፡፡

በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ ሲሳተፍ ያገኘነው አዳጊ እድሜው በአስራዎቹ መጀመሪያ ላይ የሚገኝ ነው። ሳንድሮ ቢንያም ይባላል፤ በማይ ሊትል ጂ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የ5ኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡ ስድስት ኪሎ አካባቢ በትራፊክ ማስተናበር እና በአረንጓዴ ተክሎች እንክብካቤ ላይ ጥሩ ተሳትፎ ያደርጋል፡፡ የዘንድሮውን ክረምትም በዚሁ መርሃ ግብር ነው ያሳለፈው፡፡ በበጋው መርሃ ግብር እንዲሁ ከትምህርት ቤት መልስ ከቀኑ 10 ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽት 12 ሰዓት ድረስ እግረኞች በእግረኛ መንገድ እንዲጓዙ እና ለሳይክል ተብሎ በተለዩ ስፍራዎች ላይ እንዳያቋርጡ የማድረግ ሥራ ይሠራል፡፡

በእድሜ ገፋ ያሉ አባቶችን እና እናቶችን እንዲሁም አካል ጉዳተኞችን በሚያሻግርበት ወቅት የተለያዩ ምርቃቶችን እንደሚመርቁት ተናግሯል። በተለይ “ትምህርትህን ይግለፅልህ፤ ያሳድግህ፤ ለትልቅ ደረጃ ያብቃህ” የሚል ምርቃት ሲቀበል በእጅጉ ደስታ እንደሚፈጥርለት ነግሮናል፡፡

አስተያየት ሰጪዎቹ አገልግሎቱን በሚያከናውኑበት ጊዜ ምርቃት እንደሚያገኙ የተናገሩትን የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎችም ያጠናክሩታል፡፡ ለዚህ የወጣት ቢንያም የሺጥላ አስተያየት ሁነኛ ማሳያ ነው፡፡

ወጣት ቢንያም፤ ነዋሪነቱ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 ነው፡፡ ከሽሮ ሜዳ ወደ ስድስት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ የሚወስደውን መንገድ ብዙ ጊዜ ይጠቀማል፡፡ የአይን ብርሃኑን ያጣ ሲሆን ከቤት ሲወጣ ብዙ ጊዜ የሚያሳስበው መኪና መንገድ እንዴት እንደሚያቋርጥ ነው። ታድያ የመኪናውን መንገድ ለማቋረጥ የሚቸገርባቸው ጊዜዎች ቢኖሩም፤ በጎ ፍቃደኞች በቦታው ላይ ካሉ ይህ ስጋቱ እና መቸገሩ እንደሚቀረፍለት ተናግሯል። ብዙን ጊዜ ለእንቅስቃሴ በሚጠቀምበት ከስድስት ኪሎ ሽሮሜዳ ያለው የመንገድ መስመር ላይ በጎ ፍቃደኞች ወይም በጎነትን የተላበሱ ሠዎች ስለማይጠፉ፤ መንገድ ለመሻገር መፈለጉን በነገራቸው ቅፅበት እገዛቸውን እንደሚያደርጉለት ገልጿል፡፡ በበጎ ተግባር ላይ የተሰማሩ ሰዎች ለኛ አካል ጉዳተኞች ሁነኛ መፍትሄ ሆነውልናልም ብሏል፡፡

“መንገድ በማቋርጥበት ወቅት በሚያደርጉልኝ እገዛ ምክንያት ልቤ እርፍ ይላል፡፡ ለዚህም በምላሹ እኔን እንዳሳረፉኝ እግዚያብሔር እነሱንም በቸገራቸው ነገር ላይ እረፍት ያለው ነገር እንዲሰጣቸው እመርቃቸዋለሁ” ብሏል፤ ወጣት ቢኒያም፡፡ እነርሱ የሚሠሩት በጎ ሥራ ውጤታማ እንዲሆን ሌላውም ታዛዥ እና ቀናኢ መሆን እንዳለበትም መልዕክቱን አስተላልፏል፡፡

ለመሆኑ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ላይ የሚሳተፉ በጎ ፍቃደኞች በሚከውኑት ተግባር ምን አይነት የስነ ልቦና ፋይዳ ያገኛሉ? ስንል ለስነ ልቦና አማካሪ ማስረሻ ገ/መድህን (ዶ/ር) ጥያቄ አንስተናል፡፡

እሳቸው በምላሻቸው እንዳብራሩት፤ “አንድ ሰው ማህበረሰብን የሚጠቅም ስራ በሰራው ልክ ወደር የሌለው የአእምሮ እርካታ እንዲጎናፀፍ እድል ይፈጥርለታል። በጎ ሥራ አልያም ማህበረሰቡን የሚጠቅም ሥራ ለመሥራት እራስን ዝግጁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አንድ ሰው አቅሙ እንደፈቀደለት በገንዘብ መደገፍ ባይችል እንኳን በጉልበቱ ማገዝ ይችላል። የአቅመ ደካሞችን ቤታቸውን ከማደስ በዘለለ የአረጋውያንን ጽዳት በመጠበቅ እና መሰል ስራዎች ማህበረሰቡን የሚጠቅም ስራ መሥራት ይቻላል፡፡

ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ወጣቶች ብዙ ጊዜያቸውን በአልባሌ ቦታዎች ላይ በመገኘት፣ እራሳቸውን እና ቤተሰባቸውን በማይጠቅም ተግባር ላይ ያሳልፋሉ። ምን አልባትም ዓመታትን በትምህርት አሳልፈው ቤተሰብ ብሎም ሀገር ከእነርሱ ብዙ በሚጠብቅበት ወቅት መልሶ ተረጅ የሚሆኑበት ሁኔታ ይታያል፡፡ ይህ ደግሞ ኪሳራ አለው” የሚሉት ማስረሻ (ዶ/ር)፤ በተቻለ መጠን ትምህርት ካለቀ በኋላ ሥራን ሳይንቁ ተግቶ መሥራትን ከመልመድ በተጨማሪ ወገንን በማሰብ በበጎ ፍቃድ ተግባራት ላይ መሠማራት ይገባል፡፡ ይህን ማድረግ መቻል ደግሞ ጥቅሙ ለራስ ጭምር መሆኑን መገንዘብ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡

“በበጎ ተግባራት ላይ መሳተፍ በዋናነት የሚያስገኘው ጥቅም የህሊና እርካታ ነው። በተለይ አንድ ሰው በእንደዚህ ባለ ተግባር ላይ ጥሩ ተሳትፎ ካለው ጤናማ ህይወትን ለመምራት አያዳግተውም። በአካባቢው ላይ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ጥሩ አመለካከትና መልካም እይታ እንዲያዳብር ያግዘዋል፡፡ ጤናማ የሆነ የህይወት መርህ እንዲኖረው ከማድረግ በዘለለ ደስተኛነት የታከለበት የእለት ተእለት እንቅስቃሴ እንዲያደርግ ያግዘዋል” ሲሉ ገልፀዋል፡፡

“ህብረተሰቡን የሚጠቅም ስራ መስራት ከተወሰኑ አካላት ብቻ መጠበቅ የለበትም” የሚሉት ማስረሻ (ዶ/ር)፤ በተለይም ማህበረሰባዊ ኃላፊነት ለመንግስት አልያም ለባለሀብቶች ብቻ የሚተው ተግባር አይደለም፡፡ “ገንዘብ ስለሌለኝ ይህ የእኔ ኃላፊነት አይደለም” ብሎ መተው ሳይሆን “እጄ ላይ ያለው ምን አይነት አቅም ነው” ብሎ ማጤን እንደሚያስፈልግም ገልፀዋል፡፡

ማህበረሰቡን የሚጠቅም ተግባር ለመከወን ትውልድ ላይ መስራት እንደሚገባ የሚናገሩት ማስረሻ (ዶ/ር)፣ ልጆች የቤተሰባቸውን ፈለግ ተከትለው ያድጋሉ፡፡ መልካም ስራ እየሰራ ሰዎችን እየረዳ ህይወቱን የሚኖር ወላጅ ልጆቹም ሲያድጉ ያንኑ ፈለግ ተከታዮች ይሆናሉ። ለምሳሌ ያክል አንድ ወላጅ ልጁን ለማዝናናት ሲወጣ መንገዱ ላይ የተቸገረ ሰው ሲያገኝ አቅሙ በፈቀደ መርዳትን ማበረታታት ይገባዋል፡፡ መስጠትን ባህሉ ያደረገ ልጅ ሲያድግ ሊያዳብር የሚችለውም ይህንኑ መልካምነት እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

ወጣቶች የማህበራዊ ሚድያ አጠቃቀማቸውን በመቀነስና ጠቃሚ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ጥሩ ተሳትፎ በማድረግ ሀገራችን አሁን ላይ የጀመረችውን የልማት ጉዞ እውን የማድረግ ኃላፊነት እንደሚጠበቅባቸውም ሃሳባቸውን አጋርተዋል፡፡

## ምክር... ከገጽ 7 የዞረ

ማስጀመር ተችሏል። ከዚህ ውስጥ ከ2 ሺህ 500 በላይ የሚሆኑት ግንባታቸው አጠናቆ ለአቅመ ደካሞች፣ ለሀገር ባለውለታ የመከላከያ ሠራዊት አባላትና ለሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ሰጥቷል፡፡

የኑሮ ውድነትን ለመከላከል ከተማ አስተዳደሩ የተለያዩ ተግባራትን አከናውኗል፤ እያከናወነም ይገኛል፡፡ የቅዳሜና እሁድ ገበያዎችን አስፋፍቷል። የሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራት አገልግሎት እንዲሻሻል ከፍተኛ ድጋፍ አድርጓል፡፡ በሁሉም የከተማዋ መግቢያ በሮች ግዙፍና ዘመናዊ የግብይት ማዕከላትን በመገንባት አምራችና ሸማች በቀጥታ የሚገናኙበትን ዕድል ፈጥሯል። መሠረታዊ የፍጆታ ምርቶች ለሸማቹ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲደርሱ 14 ቢሊዮን ብር ድጎማ አድርጓል፡፡ በዓላትን ምክንያት በማድረግ ከ15 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች ማዕድ ተጋርቷል፡፡

የትራንስፖርት አገልግሎትን ለማሻሻል ከለውጡ በኋላ በነበሩት ዓመታት ሰፊ ሥራዎች መሠራታቸው በከንቲባ አዳነች አቤቤ ለምክር ቤቱ ማብራሪያ ከተሰጠባቸው ጉዳዮች አንዱ ነው። በተለይ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎትን ለማሻሻል እና የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን ተደራሽነት ለማሳደግ የተሠራው ሥራ ውጤታማ መሆኑን ከንቲባዋ ገልጸዋል፡፡ እንደሳቸው ማብራሪያ፤ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎትን ለማሳደግ ከ1 ሺህ 600 በላይ አውቶብሶች በአገልግሎት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 100 በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ አዳዲስ እና ዘመናዊ አውቶብሶች በተጠናቀቀው 2017 በጀት ዓመት ወደ ሥምሪት ገብተዋል፡፡ የመኪና ማቆሚያን በተመለከተ፤ ከለውጡ በኋላ በአዲስ አበባ ብቻ ከ150 በላይ አዳዲስ የመኪና ማቆሚያ ተርሚናሎች ተገንብተዋል። በአንድ አመት ተኩል ጊዜ ውስጥ ብቻ 35ሺህ ተሽከርካሪዎችን በአንድ ጊዜ ማቆም የሚስችል የመኪና ማቆሚያዎች ለአገልግሎት ክፍት ሆነዋል፡፡ በዚህም ህዝቡ በፀሀይ፣ በዝናብ፣ በመፀዳጃ አገልግሎት እጦት የሚደርስበት እንግልት ተቃሏል፡፡

ከኪነ ጥበብ ዕድገትና መስፋፋት እንዲሁም ኪነጥበብን ለበጎ ዓላማ ከመጠቀም ጋር ተያይዞ እንደከተማ አስተዳደር እየተሠራ ስላለው ሥራ ከምክር ቤት አባላት ለተነሳ ጥያቄ ምላሽ የሰጡት ከንቲባ አዳነች፤ የዜጎችን አስተሳሰብ ለመቅረፅ፣ የወል ትርክትን፣ ብሔራዊነትን እና ተግባቦትን ለማሳደግ ጉልህ ሚና የሚጫወተውን ኪነ ጥበብ የመደገፍ ተግባር ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል፡፡ በከተማዋ ያለውን ሰፊ የኪነ ጥበብ ፍላጐት ለማሟላት እንደ ሌሎች የልማት ሥራዎች ሁሉ ለኪነ ጥበቡም ሰፊ ትኩረት መሰጠቱን አብራርተዋል። በመዲናዋ ያሉ ነባር የኪነጥበብ ማዕከላትን (ሲኒማ አምፒር፣ ሜጋ አንፊ ቴአትር፣ ብሔራዊ ቴአትር እና አገር ፍቅር) በዘመናዊ መልኩ የማደስ እና የማሻሻል ሥራ መከናወኑን አስታውሰዋል፡፡ በተጨማሪም፤ መጪውን ትውልድ ታሳቢ ያደረጉ እና ተሰጥኦን ወደ ተግባር መቀየር የሚያስችሉ ከ110 በላይ ፕላዛ እና 50 አንፊ ቴአትር መከወኛዎች ተሠርተው ለአገልግሎት መብቃታቸውን ተናግረዋል። ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የቴአትር እና የሲኒማ ኮምፕሌክሶች በአዲስ ተገንብተው ለአገልግሎት በቅርቡ መብቃታቸውን አንስተዋል፡፡

በተጠናቀቀው የ2017 በጀት ዓመት የተሻለ አፈፃፀም ላሳዩ ተቋማት ዕውቅናና ሽልማት በመስጠት እንዲሁም ሹመት በማፅደቅ 3ኛው የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የስራ ዘመን 1ኛ መደበኛ ጉባኤ ተጠናቋል፡፡ በማጠናቀቂያውም የአዲስ ሚዲያ ኔትወርክን ጨምሮ ለዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት፣ የመሬት ማስለቀቅ እና ካሳ ጉዳዮች አቤቱታ ሰሚ ጉባኤ፣ ለስነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን እንዲሁም ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ዕውቅና ተሰጥቷል፡፡ አቶ ኃፍታይ ገ/እግዚአብሔርን የአዲስ አበባ ከተማ ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ በማድረግ ሾሟል፡፡

## ቴክኖሎጂ ... ከገጽ 8 የዞረ

ዓመቱ መጨረሻ ላይ የሰበሰበውን ጥቅል ገቢ 163 ቢሊዮን ብር አድርሷል፡፡

እንዲህ ያለውን የገቢ እቅድ አፈፃፀም ዕድገት ማሳካት የተቻለበትን ምክንያት ዳይሬክተሩ ሲያስረዱ፤ ያልተነኩ የገቢ መሰረቶችንና አቅሞችን በመለየት ገቢን አሟጦ ለመሰብሰብ ጥረት በመደረጉ፣ የታክስ ከፋዩ ሕብረተሰብ የህግ ተገዢነት ግንዛቤ ደረጃው ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱ፣ በገቢ ሰብሳቢው ተቋሙ የነበሩ በተለይም የአደረጃጀት፣ የአሠራር፣ የቴክኖሎጂና የሰው ኃይል አቅም እያደገና እየተሻሻለ በመምጣቱ ነው ብለዋል፡፡

"ቴክኖሎጂን በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ለተሻለ ኢኮኖሚያዊ እድገት መነቃቃት እድል ይፈጥራል" የሚሉን አቶ አብዱላዚዝ፤ ሀገራችን የጀመረቻቸውን በቴክኖሎጂ የተደገፈ አሠራር ተጠናክሮ መቀጠል ለነገ የሚባል ተግባር አለመሆኑን ተናግረዋል፡፡ በተለይ ጳጉሜ 5 ቀን 2017 ዓ.ም. ተመርቆ ለአገልግሎት የበቃው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ለመዲናዋ ነዋሪዎች ሁሉን አቀፍ አገልግሎት በአንድ ቦታ እንዲያገኙ ያግዛቸዋል፡፡ በማዕከሉ ግንባር ቀደም አገልግሎት ከሚሰጡ ተቋማት መካከል አንዱ የሆነው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮም ሙሉ ዝግጅቱን አጠናቅቆ ወደ ስራ መግባቱን ጠቅሰዋል፡፡

አንድና ከዚያ በላይ አገልግሎቶችን በአንድ ማዕከል መስጠት መቻል ባለጉዳዮችን ካለምንም እንግልት ጉዳያቸውን እንዲፈፅሙ ያስችላል። በተለይም ደግሞ እንደ አዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓታችንን በቴክኖሎጂ ማስደገፍ መቻሉ ትልቅ አበረታች ተግባር ያደርገዋል፡፡ አንድ ባለሙያ በመስኮት ሆኖ ባለጉዳዮችን በምን አይነት ቀልጣፋ አገልግሎት ለማስተናገድ ችሏል የሚለውን የስታንዳርድ መለኪያ አለ፡፡ ይህ አሠራር ውጤታማነት እንዲረጋገጥ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል፡፡

መዲናችን አዲስ አበባ እለት ተዕለት የምታሳየው ለውጥ፤ አይደለም በሀገር ውስጥ የሚኖረውን ዜጋ ቀርቶ የውጭ ሀገራት እንግዶቻችንን ጭምር አስገርሟል፡፡ በተለይም አዲስ አበባን የሚመጥኑ ፕሮጀክቶች በተፈለገው ሰዓት ተጠናቅቀው ለተጠቃሚዎች ክፍት የመሆናቸው ሚስጥር ደግሞ ታማኝ ግብር ከፋዮቿ ብሎም በጎ ፍቃደኛ ባለሃብቶቿ ገቢ የሚያደርጉትን ገንዘብ ተከትሎ ነው፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ አብዛኛው ቴክኖሎጂዎቻችን በሀገር ውስጥ ባለሙያዎቻችን የለሙ መሆናቸውን ተከትሎ ለአሰራር ሂደቱም ቢሆን ትልቅ እፎይታን ፈጥሯል፡፡ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም መቻል በተጨባጭ ያስገኘውን ውጤት በተመለከተ አቶ አብዱላዚዝ እንዳስረዱት በአግባቡ የተተነተኑ መረጃዎችን ለማቅረብ ተችሏል። ግልፅኝነትና ተጠያቂነት የታከለበት የአሰራር ስርዓትን በመከተል ሌብነትና ብልሹ አሰራርን ለማስቀረት የቻለ ሪፖርት እንደየፈርጁ አዘጋጅቶ ለማቅረብ ስለመቻሉ ተገልጿል፡፡ ግብር ከፋዩ ማህበረሰብ በታማኝነት ግብር ለመክፈል ፍላጎት ማሳየት ችሏል፡፡

በተሠሩ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች አማካኝነት ግብር የምከፍለው የሀገር ፍቅር ስሜት ስላለኝ ነው እንዲሉ ለማድረግ ተችሏል፡፡ የተለያዩ የልማት ስራዎችን ከዳር ለማድረስ የታማኝ ግብር ከፋዩ ሚና እጅግ የላቀ ያደርገዋል፡፡ ከሃብት አንፃር ለወረቀት ይወጣ የነበረውን ወጪ በማስቀረት ወረቀት አልባ አገልግሎትን እንደ ባህል በመውሰድ የተሰራው ስራ እጅግ አስደሳች ያደርገዋል፡፡

በተጨማሪም ማህበረሰባችን ካለምንም መንገላታትና ጊዜ ማባከን ወዲያው ጉዳዩን ጨርሶ እንዲንቀሳቀስ ያግዘዋል፡፡ በተለይ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት የአሠራር ወጥነት፣ ፍጥነትና ወጪ ቆጣቢነትን በማስፈን ከለውጡ ሂደት ጋር የሚመጣጠን የገቢ አቅምን እንደሚፈጥር ለማስተዋል ስለመቻሉ አቶ አብዱላዚዝ ለዝግጅት ክፍላችን አስረድተዋል፡፡

## የማዕከላቱ ... ከገጽ 10 የዞረ

በበዓላት ወቅት የነበረው ግብይት አሁንም እንደቀጠለ እና በአቅርቦትም ይሁን በዋጋ ላይ ችግር እንደሌለ ገልፀ፤ በተለየ ሁኔታ እንቁላል ውጭ ላይ ከ22 እስከ 25 ብር ሲሸጥ እኛ ጋ በ18 ብር እየሸጥን እንገኛለን ስትል ቅናሽ እንዳለው ተናግራለች፡፡

በማዕከሉ እየተካሄደ ያለውን የስራ እንቅስቃሴና በበዓላት ወቅት የነበረው ለፍጆታ ምርቶች የተሰጠው ትኩረት በሁሉም ጊዜያት ተጠናክሮ እንደቀጠለ ማብራሪያ የሰጡን የማዕከሉ ስራ አስኪያጅ ወይዘሮ ብሩክታይት መብራቱ ናቸው፡፡ የገበያ ማዕከሉ የኑሮ ውድነቱን ለማቃለል፤ የዋጋ ንረቱን ማረጋጋትን ዓላማ አድርጎ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

በማዕከሉ ከሰብል ምርት ጤፍ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ሩዝ፣ ከጥራጥሬ ምስር፣ አተር፤ ከአትክልት ጎመን፣ ድንች፣ ሽንኩርት፣ ቃሪያ፣ ቲማቲም፤ ከፍራፍሬ አቮካዶ፣ ማንጎ፣ ፓፓያ፣ ሙዝ እንዲሁም የኢንዱስትሪና የእንስሳት ተዋፅኦዎችን በየአይነቱ በማዕከሉ እንደሚቀርቡና ህብረተሰቡ ተጠቃሚ መሆኑን ገልፀዋል።አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የሰብል ምርቶችን በአከፋፋይ አርሶ አደሮች ከማሳ በቀጥታ በበቂ ሁኔታ ወደ ማዕከሉ መምጣት መቻሉ ትኩስ እንዲሆን ከማድረጉም በተጨማሪ የደላላ ሰንሰለት ስለሌለው ውጭ ላይ ከሚሸጠው ከ15 እስከ 20 በመቶ ቅናሽ አለው፡፡

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ በሚልከው የዋጋ ተመን መሰረት ይለጠፋል፤ ግብይቱም በተመኑ መፈፀሙንና አለመፈፀሙን በምን ያህል ዋጋ እንደሆነ በማየት እንዲሁም ሸማቹ ገዝቶ ሲወጣ በስንት ገዛህ ብሎ በመጠየቅ የክትትልና ቁጥጥር ስራ ይሰራል፡፡

ማዕከሉ ያለበት አካባቢ ከዋናው አስፓልት ገባ ያለ በመሆኑ ሁሉም ማህበረሰብ እንዲያውቀውና ተጠቃሚ እንዲሆን ግቢው ውስጥ ኤግዚቢሽን በማድረግ እና ከክፍለ ከተማው ጋር በመሆን የማስተዋወቅ ስራ ሲሰራ መቆየቱን ነግረውናል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ፍስሀ ጥበቡ በበኩላቸው፤ በከተማዋ መግቢያ በሮች ተከፍተው አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የግብርና ምርቶች ማከፋፈያ የገበያ ማዕከላት የኑሮ ውድነቱን ጫና በመቀነስ፣ ገበያን በማረጋጋትና በመቆጣጠር ሚናቸው ከፍ ያለ ነው፡፡

**በከተማዋ መግቢያ በሮች ተከፍተው አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የግብርና ምርቶች ማከፋፈያ የገበያ ማዕከላት የኑሮ ውድነቱን ጫና በመቀነስ፣ ገበያን በማረጋጋትና በመቆጣጠር ሚናቸው ከፍ ያለ ነው**

ማዕከላቱ ማህበረሰቡ በዕለት ተዕለት የሚጠቀማቸውን የፍጆታ ምርቶች የደላላን ሰንሰለት በማስቀረት ሸማችና አምራቹን በቀጥታ በማገናኘት ትኩስ እንዲሁም በጥራትና በተመጣጠነ ዋጋ ምርቶቹን ሸማቹ ጋር እንዲደርሱ የሚያደርግ ነው፡፡

በማዕከላቱ የሚፈፀሙ ግብይቶች በመደበኛው ከሚቀርበው የፍጆታ ምርት ዋጋ ከ15 እስከ 20 በመቶ ቅናሽ በማድረግ ነው ለማህበረሰቡ እየቀረበ ያለው፡፡ በበዓላት ወቅት የፍጆታ ምርቶች ፍላጎት ስለሚጨምር ግብረ ሃይል በማደራጀት አቅርቦቱም እንዲጨምር ይደረጋል እንጂ ዓመቱን ሙሉ የሚካሄደው የግብይት ስርዓት ተመሳሳይ ነው፡፡ በበዓላት ወቅት የሚደረገው አቅርቦት ቀጣይነት እንዲኖረው እና ዋጋውም በወጣለት ተመን መሰረት ግብይት እንዲካሄድ ዓመታዊ እቅድ ታቅዶ በየጊዜው የገበያ ጥናት በማድረግ ነው የሚሰራው፡፡

አጠቃላይ የግብይት ሂደቱ ጤናማ እንዲሆን እና ሸማችና አምራቹ በተረጋጋ መንገድ ግብይት እንዲፈፅም አላስፈላጊ የሆኑ የዋጋ ንረቶች እንዳይከሰቱ፣ እጥረት በሚያጋጥምበትም ወቅት ምርቶች ከየትኛው አካባቢ ሊኖሩ እንደሚችሉ ቦታው ድረስ በመሄድ ጭምር የገበያ ጥናት በማድረግ መረጃ በማደራጀት እጥረት ካለ በልዩ ሁኔታ ወደ ከተማዋ እንዲገቡ የማድረግ ስራ ይሰራል፡፡

ዓመቱን ሙሉ የአቅርቦት ስራ ሲሰራ ክትትልና ቁጥጥርም አብሮ እንደሚደረግ የነገሩን አቶ ፍስሃ፤ አምራቾች በሚገቡት ውል መሰረት ከስርዓት፣ ከዋጋ እንዲሁም በቂ ምርት ይዘው መግባታቸውን መከታተል ስራ ይሰራል፡፡ በዚህ መሰረትም ይህንን ተግባራዊ ባላደረጉት ላይ በ2017 ዓ.ም 108 በሚሆኑ አምራቾች ላይ ከማስጠንቀቂያ እስከ ከገበያ ትስስር እስከማስወጣት እርምጃ ተወስዷል ብለው፤ ወደፊትም የክትትልና ቁጥጥር ስራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ነግረውናል፡፡

# የጎዳናው አርበኞች

- በከተማዋ በ2017 ዓ.ም የክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በመንገድ የትራፊክ ማስተናበር መርሃ ግብር 8 ሺህ 475 በጎ ፍቃደኞች መሳተፋቸው ተመላክቷል

**በይግለጡ ጓዴ**



ፎቶ- በገነት ወንድሙ

በጎ ፍቃደኛ ወጣቶች ከ5 ኪሎ ወደ 6 ኪሎ በሚያመራው መስመር የትራፊክ ፍሰትን ሲያስተናብሩ

"ዜጋ በጎ ሲሆን ሀገር በጎ ትሆናለች" የሚለው አባባል ስለበጎነት ከተነገሩ ወርቃማ አባባሎች መካከል ተጠቃሽ ነው። ክፍያ፣ ቀብድና ወለድ የማይጠየቅበት በጎነት በእርግጥም ከግለሰብና ከቤተሰብ ተሻግሮ ሀገርን የማቅናት ጉልበት ያለው ተግባር መሆኑ እሙን ነው፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በርካቶች በበጎ ፍቃድ አድራጎት ተግባር ላይ እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ባለቅን ልቦች መካከል ወጣት ሀያት መሐመድ አንዷ ነች። ወጣቷ በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ላይ የተሰማራችው ድንገት ከደረሰባት ጉዳት በኋላ ሲሆን፣ "በእኔ የደረሰ በሌሎች እንዳይደርስ በማሰብ ነው የበጎ ፍቃድ አድራጎትን የተቀላቀልኩት" ትላለች፡፡

ወጣት ሀያት ተወልዳ ያደገችው በአዲስ አበባ ከተማ በተለምዶ አራዳ ጊዮርጊስ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ ነው፤ ባደገችበት አካባቢ በትምህርቷ ጎበዝ፣ በታታሪነቷና ሰዎችን በመርዳት ትታወቃለች፡፡ ታድያ ገና በወጣትነት እድሜዋ ያላሰበችው መጥፎ አጋጣሚ በህይወቷ ይደርስባታል፤ ከእለታት በአንዱ ቀን የተለመደ የእለት ተግባሯን ለመከወን በወጣችበት መንገድ ስቶ በመጣ ተሽከርካሪ ጉዳት ደረሰባት፡፡ ድንገት በደረሰባት በዚህ የመኪና አደጋም ለአካል ጉዳት ትዳረጋለች፡፡

ወጣቷ በእግሯ ላይ የደረሰውን ጉዳት በህክምና ስትረዳ ቆይታ ከህመሟ ስታገግምና ወደ መደበኛ እንቅስቃሴዋ ስትመለስ በቅድሚያ ያደረገችው የበጎ ፍቃደኝነት ስራ ላይ መሰማራት ነበር። በእሷ የደረሰው አደጋ በሌሎች እንዳይደርስ የበኩሏን አስተዋፅኦ ለማድረግ ለራሷ ቃል መግባቷን የምታስታውሰው ወጣቷ፣ ክረምት ከበጋ በተለያዩ የበጎ ፍቃድ ስራዎች እየተሳተፈች ስለመሆኗ ታስረዳለች፡፡

ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ተሳትፎ እያደረገች እንደምትገኝ የምትገልጸው ወጣቷ፣ በመንገድ ትራፊክ ማስተባበር፣ የአቅመ ደካሞችን ቤት በማደስ፣ በደም ልገሳና መሰል የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች ላይ ትሳተፋለች፤ የአካባቢዋ ማህበረሰብም ተሳትፎ እንዲያደርጉ ታስተባብራለች፡፡

ወጣት ሀያት ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጋር በነበራት ቆይታ "የአንድን ሰው ህይወት መታደግ መቻል አንድ ቤተሰብ እንደማትረፍ ይቆጠራል" ብላለች፡፡ አቅመ ደካማ ሰዎችን መንገድ በማሻገር ውስጥ የሚገኘው የህሊና እርካታ በቃላት የሚገለፅ አይደለም፤ ሌሎች ወጣቶችም ወደዚህ የበጎ ተግባር በመግባት ተሳትፎ ቢያደርጉ መልካም ነው ስትል አክላለች፡፡

የሶስት ልጆች እናት የሆኑት ሌላኛዋ በጎ ፈቃደኛ ወይዘሮ ብዙአየሁ ገረሱ እናትነት እና የቤት ውስጥ የስራ ጫና ሳይበግራቸው የአካባቢያቸውን ህብረተሰብ ሲያገለግሉ ይውላሉ፡፡ ልጅ የማሳደግ ድርብ የእናትነት ኃላፊነት ጫናን በመቋቋም በ5 ኪሎ ቅድስተ ማሪያም ቤተ ክርስቲያን አካባቢ የመንገድ ትራፊክ የማስተባበር ሰራዎችን እየሰሩ ያገኘናቸው ወይዘሮ ብዙአየሁ የቤት ውስጥ ስራቸውን ከመከወን ጎን ለጎን ባላቸው ትርፍ ጊዜ ህብረተሰቡን ለማገልገል በማሰብ በበጎ ተግባር ላይ ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡

"በጎነት አንዴ በውስጥ ሰርጾ ከገባ ልትተው አትችልም" የሚሉት ወይዘሮ ብዙአየሁ፣ ሁሉም ወጣቶች በበጎ ፈቃድ ስራ ላይ ተሳትፎ በማድረግ የሰዎችን ህይወት መታደግ ይገባቸዋል ባይ ናቸው።

የትራፊክ አደጋ የበርካቶችን ህይወት እየቀጠፈ፣ ለአካል ጉዳት እየዳረገ እንዲሁም ለከፍተኛ ንብረት ውድመት ምክንያት እየሆነ መጥቷል፡፡ ከመንገድ ትራፊክ አደጋ ተጎጂዎች መካከል 80 በመቶ የሚሆኑት እግረኞች እንደሆኑ የመንገድ ደህንነት የትራፊክ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ የትራፊክ ምልክቶችን አለማክበር፣ ደርቦ ማለፍ፣ ቅድሚያ አለመስጠት፣ የፍጥነት ወሰንን አለማክበር ዋነኛ የትራፊክ አደጋ መንስኤዎች ናቸው።

ክረምት ከዝናብ፣ ጭጋግ እና ጎርፍ ጋር ተያይዞ የትራፊክ አደጋ የሚበዛበት ወቅት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህን የትራፊክ አደጋ ለመከላከልም በርካታ በጎ ፍቃደኛ ወጣቶች በከተማዋ የመንገድ ደህንነት ትራፊክ ቁጥጥር የበጎ ፍቃድ ስራን እያስተናበሩ እንደነበሩ ይታወቃል፡፡

በአራዳ ክፍለ ከተማ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ማስተባበሪያ ቡድን መሪ ወይዘሮ ህያብ ህሉፍ በክፍለ ከተማው በቤት ግንባታ፣ በማዕድ ማጋራት፣ በልዩ ፍላጎት ድጋፍ፣ በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር፣ በአካባቢ ጽዳት፣ ማስዋብና እንክብካቤ፣ በጎርፍ አደጋ ስጋት መከላከል፣ በከተማ ግብርና፣ በህዝብ መዝናኛ ቦታዎች ማስተባበር፣ በጎነት በሆስፒታልና በጤና ጣቢያ መርሃ ግብር፣ የደም ልገሳ፣ የመንገድ ትራፊክ አገልግሎት ፕሮግራም እና በመሳሰሉት የበጎ ፍቃድ መርሃ ግብሮች ከ94 ሺህ በላይ በጎ ፍቃደኞች ተሳትፎ ማድረጋቸውን ገልጸዋል፡፡

በክፍለ ከተማው 546 ሚሊዮን 318 ሺህ 448 ብር ግምት ያለው ሃብት በማሰባሰብ ከ62 ሺህ በላይ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን ወይዘሮ ህያብ ጠቁመዋል፡፡ በመንገድ ትራፊክ ደህንነት አገልግሎት ላይ ብቻ 600 በጎ ፈቃደኞች ተሳትፎ ማድረጋቸውንም አክለው ተናግረዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ኮሚሽነር ወይዘሮ አስራት ንጉሴ በከተማዋ በ2017 የክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በመንገድ የትራፊክ ማስተናበር መርሃ ግብር 8 ሺህ 475 በጎ ፍቃደኞች መሳተፋቸውን አውስተው፣ እነዚህ በጎ ፍቃደኞች በሁሉም ክፍለ ከተማ በሚገኙ መንገዶች፣ አደባባዮች እና ጎዳናዎች ላይ የትራፊክ እንቅስቃሴ እንዲሳለጥ ያስተናብራሉ፡፡

እንደ ወይዘሮ አስራት ገለጻ የበጎ ፍቃድ ፕሮግራም 18 መርሃ ግብሮች ያሉት ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል የቤት ግንባታ፣ ማእድ ማጋራት፣ የትምህርት ማጠናከሪያ፣ የነፃ የህክምና አገልግሎት፣ የደም ልገሳ፣ በጎነት በሆስፒታል፣ የመንገድ ትራፊክ አገልግሎት፣ የህፃናት ድጋፍ፣ የልዩ ፍላጐት ድጋፍ፣ አረንጋዴ አሻራ ተሳትፎ፣ የአካባቢ ፅዳትና ማስዋብ፣ የጐርፍ ስጋትና መከላከል መርሃ ግብሮችና ሌሎች በርካታ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ስራዎች ማህበረሰቡን በማሳተፍ መሰራታቸውን ተናግረዋል፡፡

በእነዚህ መርሃ ግብሮች ከ 2 ነጥብ 4 ሚሊዮን በላይ በጎ ፈቃደኞች በድግግሞሽ ተሳትፎ ያደረጉ ሲሆን፣ በዚህም ከ 1 ሚሊዮን 25 ሺህ በላይ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ሆነዋል። ከተለያዩ የበጎ ፍቃድ መርሃ ግብሮችም ከበጎ ፍቃደኞች እና ባለሃብቶች 8 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር የሚገመት ሃብት መሰብሰቡን ወይዘሮ አስራት ገልጸዋል፡፡

**ክፍለ ከተማው 546 ሚሊዮን 318 ሺህ 448 ብር ግምት ያለው ሃብት በማሰባሰብ ከ62 ሺህ በላይ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል፤ በመንገድ ትራፊክ ደህንነት አገልግሎት ላይ ብቻ 600 በጎ ፈቃደኞች ተሳትፎ አድርገዋል**

አቶ ብርሃኑ አየነው መኮንን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክ/ከ ወረዳ 01 የይዞታ የካርታ ቁጥር 1/13/1900/02 የሴሪ ቁጥር 0250636 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ/ሰርተፍኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቸዋለው/ይዤዋለው/ የሚል ሰው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ /ሰርተፍኬት/ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 05 በ ሀየሎም ገብረትንሳኤ የሕደጎ የተመዘገበ ቤት--በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 ክልል ውስጥ በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000070502325 በሴሪ ቁጥር 0126595 የተመዘገበው የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጄ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በታሪኩ ፍቃዱ አሶሬ ስም የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000080115822 የሴሪ ቁጥሩ L 0102712 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋ በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ተለዋጭ ሰርተፊኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ኃይለማርያም ሀብተወልድ እና ወ/ሮ አስናቀች ሙሉጌታ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር 383 ካርታ ቁጥር 17/61/24653/00 ተመዝግቦ የሚገኘው በእጃቸው መገኘት የነበረበት ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት በ20 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ/ ተክሉ ገብረመድህን ወልደሚካኤል ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 14 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ን/ስ/1/7/25/148357/00 የሆነው ካርታ የሴሪ ቁጥሩ 1648241 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

እነ አመቴ ማሬ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ በካርታ ቁጥር 40-L4-6 ሆኖ የተመዘገበ ማህደራቸው ተፈልጎ ሊገኝ ስላልቻለ ይህንን ማህደር በዕዳ፣ በዋስትና ወይም በሌላ በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ካለ በ30 ቀን ውስጥ ኮ/ቀ/ክ/ከተማ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ካላሳወቀ ግን በምትኩ ማህደር አደራጅተን አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 05 በ ሀየሎም ገብረትንሳኤ ይህደጎ እና ፃድቃን በየነ ገብረኪዳን የተመዘገበ ቤት--በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 ክልል ውስጥ በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000070504000 በሴሪ ቁጥር 0126674 የተመዘገበው የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጄ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 09 ክልል ውስጥ በካርታ ቁጥር 053473 በሴሪ ቁጥር 152274 በአለማየሁ አዲሱ በዲቻ ስም የተመዘገበው የቤት የባለይዞታነት እና ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጄ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊት ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በወርቁ ውቤ ገዳሙ እና ይደነቁ መኩሪያ ገላው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 የሚገኘው በይዞታ ካርታ ቁጥር 01/316/9653/00 በሴሪ ቁጥሩ 069077 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው በሃይኒከን ብሩዌሪስ አክሲዮን ማህበር በልደታ ክ/ማ ወረዳ 03 በካርታ ቁጥር ዴ2/04/162/3122/008338/001236/004469/03 ሴሪ ቁጥር 099030 የቦታ ስፋት 1002 ካ.ሜ የተመዘገበ ይዞታ ካርታ ጠፋብኝ ብለው በቀን 03/01/2018 ዓ.ም በማመልከቻ የጠየቁ ስለሆነ፣ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳይ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ኦርጅናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ጌታው ዘነበ ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉ/ክ/ከተማ ወረዳ 06 ነዋሪ የሆኑት የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር 18/23/14301/00 የሴሪ ቁጥር 081597 በቀን 18/05/98 ዓ/ም ወጪ የተደረገ ካርታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት/ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለው/ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትክ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

## ከሰዎች ጋር ያለንን ግንኙነት ለማስተካከል የሚረዱ ሚስጥሮች

ጥሩ ጓደኝነትም ይሁን ትዳር፤ የስራ ግንኙነትም ይሁን የፍቅር፤ ከሰዎች ጋር የምንመሰርታቸው ግንኙነቶች በህይወታችን በጣም ጠቃሚዎች ናቸው።

ለእነዚህ ግንኙነቶች የሚረዱ ነገሮች፡-

### 1. ግጭት ሲፈጠር አለመደናገጥ

ጓደኝነት የሚጠነክረውና የሚያድገው በልዩነታችን በመሆኑ ግጭት ለግንኙነት መሰረት ሊሆን ይችላል። ግጭት ሲፈጠር በቀላሉ ለመፍታት መጀመሪያ ሌላኛው ሰው እየተሰማው ያለውን ነገር ለመረዳት መሞከርና እኛ ጥፋተኛ ከሆንን ኃላፊነት ለመውሰድ መዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡

### 2. ራስን መሆን

ቸኩለን ወደ አንድ ግንኙነት ከመግባታችን በፊት ለራሳችን ጊዜ መስጠትና ለሌላኛውም ሰው ቢሆን የብቸኝነት ጊዜ መስጠት ጠቃሚ ነው።

### 3. አብሮ መዝናናት

አንዳንድ አስፈላጊ ነገሮችን ለመግዛትና የተለያዩ ዝግጅቶችን ለመታደም ብቻ ሳይሆን እንዲሁ ጥሩ ጊዜ ማሳለፍ ግንኙነቱን ወደ ተሻለ ቦታ ይወስደዋል።

### 4. በግልጽ መነጋገር

ሃሳብን ግልጽ እና ቀላል በሆነ መልኩ መግለጽ አለመግባባትንና አላስፈላጊ ግጭቶችን ይቀንሳል።

### 5. ሁሉንም ነገር ከአንድ ሰው አለመጠበቅ

ከጓደኞችን ወይም የትዳር አጋራችን እንዲደረጉልን የምንፈልጋቸው ነገሮች ይኖራሉ፡፡ ከእነዚህ አንዱ የጠበቅነው ሲጎድል ችግር ውስጥ እንገባለን፡፡ ነገር ግን ሁሉንም ነገር ከዚያ ሰው ብቻ መጠበቅ ተገቢ አይደለም፡፡

### 6. ጥሩ ጊዜያትን መለስ እያሉ ማስታወስ

ሰዎች በየትኛውም ጊዜ ያሳለፉትን ጥሩ ትዝታ መለስ እያሉ ማስታወስና መነጋገር ከባዱን ጊዜ ለመርሳት ይጠቅማቸዋል።

### 7. እርዳታ ለመጠየቅ አለመፍራት

ከአንድ ሰው ጋር ጥብቅ የሆነ ግንኙነት እንዲኖረን የሚሰማንን ነገር ለመናገርና እርዳታቸውን ለመጠየቅ መፍራት የለብንም።

### 8. ደግነትና አድናቆትን ለሌሎች ማሳየት

ስለ አንድ ሰው እያሰቡ ከሆነ በስልክም ይሁን በአጭር የጽሑፍ መልዕክት ስሜትን መግለፅ፡፡ የመተሳሰብና የእምነት ስሜትን ይፈጥራል። በሰሩት ስራ ውጤታማ ሲሆኑም መደሰታችንን መግለጽና አድናቆትን መቸር ያስፈልጋል።

### 9. ትክክለኛውን ሰው ብቻ ለማግኘት አለመሞከር

አንድ ሰው ጥሩ የሚሆነው ትክክለኛ ስለሆነ ወይም የሚሳሳተው ትክክለኛ ስላልሆነ ሳይሆን ሰው በመሆኑ ነው። ስለዚህ የመሰረትነውን ግንኙነት ለማሳመር መሞከርና ጥሩ ጥሩውን ለመመልከት መሞከር አስፈላጊ ነው።

### 10. የሚያናግሩትን ሰው ስሜት መረዳት

ሰዎች እጅግ የሚያሳዝን ወይም የሚያስደስት ታሪክ እየነገሩን ስሜታቸውን በሀሳብ የለሸነት ሳንረዳ የምንከተለው ከሆነ ተአማኒነት ያሳጣል፡፡ መልካም ተግባቦት እንዲኖረን የተናጋሪውን ስሜት ወደ እኛም ዘልቆ እንዲገባ መፍቀድ መቻል አለብን፡፡

**ምንጭ፡-** Ethiopian news today and afrihealth TV የፌስቡክ ገፅ እንዲሁም Yerasbussiness.com የማህበራዊ ትስስር ገፅ

# የአፍሪካ ተሳትፎ በዓለም የእግር ኳስ ዋንጫ




ፎቶ- ከገፀ ድር

ለመጀመሪያ ጊዜ 48 ሀገራትን የሚያሳትፈው የ2026ቱ የፊፋ የዓለም ዋንጫ በቀጣይ ክረምት ይካሄዳል

> በአሜሪካ፣ በካናዳ እና በሜክሲኮ አስተናጋጅነት የሚካሄደውና ለመጀመሪያ ጊዜ 48 ሀገራትን የሚያሳትፈው የ2026ቱ የፊፋ የዓለም ዋንጫ በቀጣይ ክረምት ይካሄዳል። ለአፍሪካ የተሰጠው ውክልናም ወደ ዘጠኝ ሀገራት ከፍ ብሏል

**በሳህሉ ብርሃኑ**

ብዙ ሀብት የሚዘወርበት የእግር ኳስ ውድድር የሰው ልጅን ቀልብ መግዛት ከቻሉ ስፖርቶች ውስጥ ተጠቃሽ ነው፡፡ በየአራት ዓመቱ የሚካሄደው የዓለም ዋንጫ ደግሞ ከእነዚህ ተወዳጅ ውድድሮች መካከል ይገኝበታል፡፡ ከ95 ዓመት በፊት የተመሰረተው እና በአራት ዓመት አንዴ የሚካሄደው የዓለም ዋንጫ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ሁለት ጊዜ ካለመከናወኑ በቀር ከምስረታው ጀምሮ ለ22 ጊዜ ሲካሄድ ቆይቷል፡፡

በአሜሪካ፣ በካናዳ እና በሜክሲኮ አስተናጋጅነት የሚካሄደውና ለመጀመሪያ ጊዜ 48 ሀገራትን የሚያሳትፈው የ2026ቱ የፊፋ የዓለም ዋንጫ በቀጣይ ክረምት ይካሄዳል፡፡ በዚህ ማሻሻያ ምክንያት ለአፍሪካ የተሰጠው ውክልናም ወደ ዘጠኝ ሀገራት ከፍ ያለ ሲሆን የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽንም (ካፍ) 53 ሀገራትን በምድብ ከፋፍሎ ሲያወዳድር ቆይቷል፡፡ እስካሁን ለዓለም ዋንጫው ማለፋቸውን ካረጋገጡት የአፍሪካ ሀገራት መካከል ሞሮኮ፣ ቱኒዚያ፣ ግብጽ፣ አልጄሪያ፣ ጋና፣ ኬፐ ቨርዴ፣ ደቡብ አፍሪካና አይቮሪ ኮስት ሲሆኑ ቀሪ ሶስት ሀገራት ደግሞ በቀጣይ ተለይተው የሚታወቁ ይሆናል፡፡

በአትላንቲክ ውቂያኖስ ውስጥ ከሚገኙ ትንንሽ ደሴቶች አንዷ የሆነችው ኬፐ ቨርዴ በታሪኳ ለመጀመርያ ጊዜ በትልቁ የዓለም ዋንጫ መድረክ መሳተፏን አረጋግጣለች፡፡ 4 ሺህ ስኩየር ኪሎ ሜትር የቆዳ ስፋት ያላት ምዕራብ አፍሪካዊቷ ሀገር በ96 ዓመት የዓለም ዋንጫ ታሪክ በመድረኩ የተሳተፈች ትንሿ ሀገርም ሆናለች፡፡ 5 ሺህ ስኩየር ኪሎ ሜትር ስፋት ያላት ትሪንዳድ እና ቶቤጎ በ2006ቱ የጀርመን ዓለም ዋንጫ ተሳታፊ የነበረችበት በክብረ ወሰንነት ተይዞ የነበረ ቢሆንም አሁን በሌላ ትንሽ ሀገር ተተክታለች ይላል የአፍሪካ ኒውስ ዘገባ፡፡

በአፍሪካ ሀገራት የዓለም ዋንጫ ማጣሪያ ምድብ አራት ላይ የነበረችው ሀገር ካደረገቻቸው 10 ጨዋታዎች ሰባቱን አሸንፋ በሁለቱ ደግሞ ነጥብ ተጋርታ በ23 ነጥብ ምድቡን በበላይነት በማጠናቀቅ የዓለም ዋንጫ ተሳታፊነቷን አረጋግጣለች፡፡ ለሀገሪቱ ዜጎች የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክት ያስተላለፉት የዓለም አቀፉ እግር ኳስ ፌዴሬሽኖች ማህበር ፊፋ ፕሬዝደንት ጂያኒ ኢንፋንቲኖ "የሀገራችሁ ሰንደቅ አላማ በትልቁ መድረክ ከፍ ብላ የምትታይበት እና ብሔራዊ መዝሙራችሁ በዓለም የሚሰማበት ይሆናል" ብለዋል፡፡

ለስኬቷ ምስጢር የኬፐ ቨርዴ የዘር ሐረግ ያላቸውን እና በአውሮፓ የሚኖሩ ልጆቿን ማሰባሰቧ እንደሆነ የሚነገርላት ሀገሪቷ በእግር ኳሷ ላይ አተኩራ በመስራቷ 15 ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከአህጉሩ ትልቁን መድረክ ተሻግራ በዓለም ዋንጫ ተከስታለች፡፡ ኬፐ ቨርዴ በአፍሪካ ዋንጫ ለመጀመርያ ጊዜ የተሳተፈችው በ2013 የደቡብ አፍሪካ ዋንጫ ሲሆን፣ ሁለት ጊዜ ደግሞ ለሩብ ፍጻሜ የደረሰችበትን ውጤት ማስመዝገቧም ይታወሳል፡፡ የብሔራዊ ቡድኑ አሰልጣኝ የቀድሞው የኬፐ ቨርዴ ብሔራዊ ቡድን ተጫዋች ፔድሮ ሌይታኦ ብሪቶ በአምስት ዓመታት ቆይታው በሁሉም መንገድ የተዋጣለት ቡድን ገንብቶ አዲስ ታሪክ ጽፏል፡፡

የወቅቱ የአፍሪካ ዋንጫ አሸናፊ የሆነችው ሴኔጋል በተረጋጋ የአሰልጣኝነት አመራር (በአሊዩ ሲሴ) እና ለዓመታት በአንድ ላይ የተጫወቱ ልምድ ያላቸው ተጫዋቾች ስብስብ ነበራት። በተለይም እንደ ሳዲዮ ማኔ ያሉ ኮከብ ተጫዋቾች መኖራቸው ለቡድኑ ጥንካሬ ሰጥቷቸው ወደ ዓለም ዋንጫው ስለማምራታቸው የዘ ኔሽን ጋዜጣ ዘጋበ ያሳያል፡፡

የሞሮኮ ብሔራዊ ቡድን በዎሊድ ሬግራጉይ መሪነት ቡድኑ በፍጥነት አንድነትን ፈጥሮ ጠንካራ ብሔራዊ ቡድን እንደገነባ እየተነገረለት ይገኛል። በርካታ ተጫዋቾች በአውሮፓ ትላልቅ ሊጎች የሚጫወቱ መሆናቸውና በተለይም በግብ ጠባቂው (ያሲን ቡኑ) እና የመከላከል መስመር (አሽራፍ ሃኪሚ) ላይ ጠንካራ መሆናቸው ለታሪካዊ ስኬት አብቅቷቸዋል። የሬግራጉይ ቡድን በጠንካራ መከላከል ላይ የተመሰረተ (Solid Defensive Structure) እና ፈጣን የመልሶ ማጥቃት ስልት (Counter-Attacking Strategy) መጠቀሙን የሚያብራራው የዘ ኔሽን ጋዜጣ ፀሐፊው ዋለ ጋባዴቦ ነው፡፡

ምድብ ዘጠኝ ላይ የነበረችው ጋና ከ10 ጨዋታ 25 ነጥብ በመሰብሰብ ቀዳሚ ሆና አጠናቅቃለች። ለመጀመሪያ ጊዜ በ2006 የዓለም ዋንጫ የተሳተፈችው ጋና የ2026ቱ አምስተኛ ተሳትፎዋ ይሆናል። እንደ ካሜሩንና ጋና ያሉ ብሔራዊ ቡድኖች ደግሞ በአዳጊዎች ላይ አተኩረው በመስራት የዕድሜ ክልል ቡድኖችን ከወጣትነት ጀምሮ በአግባቡ ማሰልጠን፣ ኮከብ ተጫዋቾች ተፈጥረው ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርሱ እንደረዳቸው መረጃዎች ያሳያሉ።

የቱኒዚያ ብሔራዊ ቡድን በዓለም ዋንጫዎች ላይ በቋሚነት ከሚሳተፉ የአፍሪካ ሀገራት አንዷ ነች። በዘንድሮው ውድድር ላይ ባሳየችው ጠንካራ የማጣሪያ ጉዞ (በጥቂት ነጥቦች መሪ ሆና) ያለፉት ውድድሮች ላይ ያጣቻቸውን ጥቂት የጨዋታ ጊዜያትን በማረም ከምድብ ማለፍ ችላለች፡፡

እንደ ሞሐመድ ሳላህ፣ ሪያድ ማህሬዝ የመሳሰሉ ከዋክብትን የያዙት የግብጽ እና የአልጄሪያ ብሔራዊ ቡድኖች በዓለም ዋንጫው ብዙ ርቀት ይጓዛሉ ተብለው ተስፋ የተጣለባቸው ብሔራዊ ቡድኖች ናቸው፡፡

አፍሪካ በዓለም ዋንጫ መድረክ ላይ መሳተፍ የጀመረችው እ.ኤ.አ በ1934ቱ የዓለም ዋንጫ ግብጽን በመወከል ነበር። ከዚያ በኋላ ለረጅም ዓመታት በአህጉሩ እና በፊፋ መካከል የነበረው ውክልና አለመመጣጠን ምክንያት በውድድሩ ላይ የአፍሪካ ሀገራት ተሳትፎ በጣም አነስተኛ ነበር። እስከ 1970 ዓ.ም ድረስ አፍሪካ በዓለም ዋንጫ የምትወከለው በአንድ ብሔራዊ ቡድን ብቻ ነበር። ከ1982ቱ የዓለም ዋንጫ ጀምሮ ግን የውክልና ድርሻዋ ወደ ሁለት ቡድኖች ከፍ ብሎ ይህም እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ ቀጥሏል። በ1998ቱ ውድድር ደግሞ የአፍሪካ ተወካይ ሀገራት ቁጥር ወደ አምስት ከፍ ብሎ እስከ 2022ቱ የኳታሩ ዓለም ዋንጫ ድረስ ስለመቆየታቸው የስካይ ስፖርት መረጃ ያሳያል፡፡

ምንም እንኳን የአፍሪካ ሀገራት በዓለም ዋንጫ መድረክ ላይ መሳተፍ ከጀመሩ ረጅም ጊዜ ቢሆነውም፣ አህጉሪቱን ወክለው የተሳተፉት ቡድኖች ዋንጫውን ማንሳት ባይችሉም፣ የሚጠቀሱ ታሪካዊ ውጤቶችን አስመዝግበዋል።

የአፍሪካ ሀገራት በዓለም ዋንጫ የተመዘገበው ከፍተኛው ውጤት ሩብ ፍጻሜ (Quarter Finals) መድረስ ነው። ይህን ታሪካዊ ምዕራፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ያስመዘገበችው ካሜሩን በ1990ው የዓለም ዋንጫ ነበር። በሮጀር ሚላ መሪነት የአፍሪካን ክብር ከፍ ያደረገችው ካሜሩን የዓለምን ትኩረት ስባ ነበር።

የስካይ ስፖርት መረጃ እንደሚያሳው የሴኔጋል ብሔራዊ ቡድን በ2002ቱ የዓለም ዋንጫ ላይ በታላቅ ብቃት ተጫውታ ለሁለተኛ ጊዜ ሩብ ፍጻሜ የመድረስ ታሪክ ደግማለች። ሴኔጋል ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለም ዋንጫ ስትሳተፍ የዓለም ዋንጫ አሸናፊ የሆነችውን ፈረንሳይን በማሸነፍ ታሪክ በመስራት ነበር።

የጋና ብሔራዊ ቡድን እንደዚሁ በ2010 ደቡብ አፍሪካ የዓለም ዋንጫ ላይ አህጉሪቱን ወክላ ሩብ ፍጻሜ የደረሰች ሦስተኛ ሀገር ሆናለች። በተለይም ከኡራጓይ ጋር ባደረገችው የሩብ ፍጻሜ ጨዋታ በብዙዎች ዘንድ የማይረሳ ድራማዊ ፍልሚያ በማድረግ በአሳዛኝ ሁኔታ በፍጹም ቅጣት ምት ተሸንፋ ከውድድሩ መሰናበቷ ይታወሳል። በኳታር በተካሄደው የ2022 ዓለም ዋንጫ ላይ ሞሮኮ ባሳየችው ድንቅ ብቃትና አዲስ ታሪክ በመስራት ወደ ግማሽ ፍጻሜ (Semi-Finals) በመድረስ የአፍሪካን እግር ኳስ ታሪክ በወርቃማ ቀለም ጽፋ የመጀመሪያዋ ግማሽ ፍፃሜ የደረሰች ሀገር ሆናለች። ይሁንና የዓለም ዋንጫ ውድድር ላይ አህጉረ አፍሪካ በእስካሁኑ ሂደት ያስመዘገበችው ውጤት ከሩብ ፍጻሜ የተሻገረ አይደለም፡፡

የዘ ኔሽን ጋዜጣ ገፀ ድር መረጃ እንደሚያሳየው ካሜሩን፣ ሞሮኮ፣ ናይጄሪያ፣ ጋና፣ ቱኒዚያ እና አልጄሪያ አህጉሪቱን ወክለው በዓለም ዋንጫው ተደጋጋሚ ተሳትፎ ያደረጉ ብሔራዊ ቡድኖች ናቸው፡፡ በ2022ቱ የኳታር ዓለም ዋንጫ ላይ አፍሪካን ወክለው የተሳተፉት አምስት ሀገራት ሴኔጋል፣ ሞሮኮ፣ ጋና፣ ካሜሩን እና ቱኒዚያ መሆናቸው ይታወሳል።